የአጻጻፍ ክህሎት

ለወረዳ ዳኞች እና ዐቃብያነ-ህግ ሥልጠና
የተዘጋጀ ሞውጁል

አዘጋጅ፡-
ማርቆስ በቀለ

ጎዳር 2003 ዓ.ም
ባህር ዳር

ማውጫ

1. መግቢያ……..1
2. የፍትሃብሄርአቤቱታማመልከቻማዘጋጀት……2
   2.1. የፍትሃብሄርአቤቱታማመልከቻማለትምንማለትነው?……..2
   2.2. የፍትሃብሄርአቤቱታጽሁፍምንምንነገሮችንይይዛል?……2
   2.3. በፍትሃብሄርአቤቱታጽሁፍላይየሚታዩችግሮች……7
3. የፍትሃብሄርመከላከያመልስምንምንነገሮችንይይዛል?……..7
   3.1. በፍትሃብሄርመልስጽሁፍላይየሚታዩችግሮች……10
4. የይግባኝማመልከቻምንምንነገሮችንይይዛል?……..10
5. የወንጀልክስማመልከቻማዘጋጀት……11
   5.1. ቅድመየወንወጀልክስዝግጅት……..11
   5.2. የወንጀልክስማመልከቻአጠቃላይይዘት……..13
   5.3. በወንጀልክስሂደትየሚያጋጥሙችግሮች……16
6. በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 38(ሐ)
   መሰረትየሚሰጥየተጨማሪምርመራትዕዛዝአጻጻፍ……17
7. በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 41
   መሰረትመሪትዕዛዝእንዲሰጥየሚጠየቅበትጽሁፍአጻጻፍ……20
8. በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 42
   መሰረትክስየማይቀርብመሆኑንየሚገልፅውሳኔአጻጻፍ……22
9. የየዕለትየችሎትውሎአጻጻፍ……31
   9.1. በየዕለትየችሎትውሎአጻጻፍላይየሚታዩችግሮች……31

10. ምስክርየመስማትሂደትአጻጻፍ……32
10.1. ምስክርበመስማትሂደትአጻጻፍላይየሚታዩችግሮች……32
11. ፍርድናውሳኔመጻፍ……33
11.1. የፍርድናውሳኔዓላማዎች……34
11.2. የፍርድናውሳኔቅርጽናይዘት……35
11.3. የሀገራችንየውሳኔአጻጻፍቅርጽናይዘት……36
11.4. የሀገራችንፍርድአጻጻፍአንዳንድችግሮች……38
11.4.1. የፍትሃብሄርፍርድናውሳኔአጻጻፍ……38
11.4.2. የወንጀልጉዳይፍርድናውሳኔአጻጻፍ……41
11.5. የፍርድናውሳኔአጻጻፍበፍርድቤቶችደረጃ……43
11.5.1. የመጀመሪያደረጃ ፍ/ቤትፍርድናውሳኔአጻጻፍ……43
11.5.2. ይግባኝሰሚፍርድቤት……48
12. በፍርድቤቶቻችንበሚሰጡውሳኔዎችላይየሚታዩችግሮች……51
13. የውሳኔአጻጻፍእናሥነ-ምግባር……56
14. ጥሩየውሳኔአጻጻፍዘይቤ……58
ዋቢ ጽሁፎች……65

1. መግቢያ

ሰው ማህበራዊ ከሚባሉት እንስሳዎች መካከል አንዱ ነው። ይህ ማህበራዊ እንስሳነቱም ከሌሎች መሰሎቹ ጋር በየዕለቱ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ግንኙነት እንዲፈጥር ያደርገዋል። በግንኙነቱም ውስጥ በተለያዩ ምክንያቶች አለመግባባቶች ሊፈጠሩ ይችላሉ። እነዚህ አለመግባባቶች በባህላዊ መንገድ በሽምግልናና ግልግል የሚፈቱ ሲሆን በዘመናዊ መንገድ ደግሞ በፍ/ቤቶች አማካኝነት እልባት እንዲያገኙ ይደረጋሉ።

አለመግባባቶችን በዘመናዊ መንገድ በፍ/ቤቶች እንዲፈቱ ለማድረግ በዘመናዊ መልክ የተዘጋጁ ህጎች መኖራቸው የግድ ይላል። እነዚህን ህጎች በአግባቡ ተርጉሞ ፍትሃዊ ዳኝነት ለመስጠት የህግ ትምህርት ያላቸው ሰዎች አስፈላጊዎች ናቸው። ህጎችን በታሰበውና በተፈለገው መንገድ ተርጉሞ ፍትሃዊ ዳኝነት ለመስጠት በህግ ት/ቤቶች ገብቶ ተምሮ መውጣት ዋነኛውና መተኪያ የሌለው ግብዓት ቢሆንም ይህ በህግ ት/ቤቶች የሚሰጠው ትምህርት በጽንሰ-ሀሳብ ላይ ብቻ ያተኮረ በመሆኑ በፍ/ቤቶች ውስጥ ህጎች በተግባር እንዴት እየተሰራባቸው እንደሆነ ለማየት የሚያስችል ዕድል

ስለዚህ ይህንን ክፍተት ለመሙላት ከተግባራዊ ሥራዎች ጋር በሚያስተቃውቁ የህግ ባለሙያዎች ማሰልጠኛ ማዕከላት ውስጥ ገብቶ መሰልጠን ወደ ተግባራዊ ሥራው ለመግባት አስፈላጊና መተኪያ የማይገኝለት ወሳኝ መሳሪያ ነው። በእነዚህ ተግባራዊ ሥራዎችን በሚያስተዋውቁት የህግ ባለሙያዎች ማሰልጠኛ ማዕከላት ከሚሰጡት ተግባር ተኮር ሥልጠናዎች ውስጥ አንዱ የአፃፃፍ ክህሎት ሥልጠና ነው። ይህ ሞጁልም የተዘጋጀው ይህንኑ የአፃፃፍ ክህሎት ሥልጠና ለመስጠት በመሆኑ በዚህ ስልጠና ሰልጣኞች ስለ ፍትሃ ብሄር አቤቱታና መልስ አፃፃፍ፣ በዐ/ህግ በኩል ስለሚዘጋጁ የተለያዩ ዕሁፎች አጻጻፍ (ማለትም ስለ ወንጀል ክስ አፃፃፍ፣ ስለተጨማሪ ምርመራ ትዕዛዝ አፃፃፍ፣ ስለመሪ ትዕዛዝ አፃፃፍ እና ስለክስ አልመሰርትም ውሳኔ አፃፃፍ)፣ በፍ/ቤቶች በሚደረጉ የዕለት ከዕለት ተግባራት ስለሚከናወኑ የችሎት ውሎ አፃፃፍ፣ ስለ ምስክር የመስማት ሂደት አጻጻፍ እና ስለውሳኔ አፃፃፍ ግንዛቤ ያገኛሉ።

ይህንን የአፃፃፍ ክህሎት ሥልጠና ጽሁፍ ለማዘጋጀት መሰረት የሆኑት ነገሮች የፍትሃ ብሄርና የወንጀል ሥነ-ሥርዓት ህጎች፣ የመስሪያ ቤቶች የደብዳቤ አፃፃፍ ሥርዓቶች እና ተቀባይነት ያገኙ የፍ/ቤትና የዐ/ህግ መስሪያ ቤት የአፃፃፍ ልምዶች መሆናቸውን ልብ ልንል ይገባል።

2. <u>የፍትሃብሄር አቤቱታ ማመልከቻ ማዘጋጀት</u>

2.1. <u>የፍትሃ ብሄር አቤቱታ ማመልከቻ ማለት ምን ማለት ነው?</u>

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 80 ላይ እንደተገለፀው የአቤቱታ ፅሁፍ ማለት፡-

- ከሳሽ የሚጠይቀውን ሁሉ ዘርዝሮ የሚገልፅበት ፅሁፍ፣
- ተከሳሽ የሚሰጠው የመከላከያ ፅሁፍ፣
- የተከሳሽ ከሳሽ የሚያቀርበው የክስ ፅሁፍ፣
- ይግባኝ ማቅረቢያ ፅሁፍ፣
- በሌላ ዓይነት ተፅፎ ለፍ/ቤት የሚቀርብ የክስ መነሻ ወይም ለዚሁ የሚሰጠውን መልስ የሚመለከት ማናቸውም የፅሁፍ ማመልከቻ ማለት እንደሆነ ተደንግጓል፡፡

ስለዚህ የአቤቱታ ጽሁፍ ማለት ሰዎች የገጠማቸውን ማናቸውም ዓይነት በፍ/ቤት እልባት ማግኘት የሚገባቸውን ጉዳዮች መፍትሄ ለማስገኘት በማሰብ ጉዳያቸውን በጽሁፍ አስፍረው ይዘው ለፍ/ቤት የሚያቀርቡበት ማናቸውም ዓይነት የጽሁፍ ማመልከቻ ማለት ነው፡፡

2.2. <u>የፍትሃ ብሄር አቤቱታ ጽሁፍ ምን ምን ነገሮችን ይይዛል?</u>

የፍትሃ ብሄር አቤቱታ ማመልከቻ ሲዘጋጅ ቴክኒካዊና ህጋዊ ነገሮችን አሟልቶ የያዘ መሆን አለበት፡፡

i. <u>ቴክኒካዊ ነገሮች /Technical Requirements/</u>

- ፅሁፉ በእጅ ወይም በታይፕ ወይም በኮምፒውተር ሊፃፍ ይችላል። **(የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 80(2))**
- በተቻለ መጠን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህጉ አንደኛ ሰንጠረዝ ላይ በተቀመጠው መልኩ መዘጋጀት አለበት።
- አመልካቹ መብቱን የሚጠቅበትን ምክንያት ብቻ በአጭሩ /only material fact of a case in a concise way/ የያዘ መሆን አለበት። **(የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 80(2))**
  - የህግ ድንጋጌዎችን መጥቀስ አስፈላጊ አይደለም።
  - አላስፈላጊ ነገሮች መጨመር የለባቸውም።
  - ማስረጃን የሚመለከቱ ጉዳዮች መካተት የለባቸውም፤ ምክንያቱም ማስረጃ ራሱን ችሎ ለብቻው የሚቀመጥ ስለሆነ
- የቀረበው የአቤቱታ ቃል እውነት መሆኑ መረጋገጥ አለበት። **(በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 92) - ይህ በአቤቱታው ላይ የተገለፀው በሙሉ እውነት መሆኑን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 92 መሰረት አረጋግጣለሁ።**
- በአቤቱታ አቅራቢው መፈረም አለበት። **(ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 93)**
- ከክስ ማመልከቻው ጋር ተያይዘው የሚቀርቡ ፅሁፎችና መግለጫዎች ይኖራሉ። **(በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 137፣ 223፣ 256)**
  - የምስክሮችን ስም ዝርዝር ከነአድራሻቸው የያዘ ወረቀት **(በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 223(1)(ሀ))**
  - የፅሁፍ ወይም የሰነድ ማስረጃ ያለ ከሆነ - **በእጁ የማይገኝ ከሆነ የሚገኝበትን ሥፍራና በማን እጅ እንደሚገኝ መግለፅ (በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 223(1)(ሀ))**
  - የሚያቀርበው ምስክር ወይም የፅሁፍ ሰነድ የሌለው ሲሆን ይህንን ገልፆ ማረጋገጥ **(በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 223(1)(ሐ))**
  - ክሱ በተፋጠነ ሥነ-ሥርዓት የሚታይ ከሆነ ከላይ ከተጠቀሱት ከክስ ማመልከቻው ጋር ተያይዘው ከሚቀርቡት ፅሁፎችና መግለጫዎች በተጨማሪ የክስ አቤቱታው በቃለ-መሀላ (affidavit) ተደግፎ ይቀርባል**(በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 284(1)(ሐ))**፤ ቃለ-መሀላው፡-
    - የቀረበው አቤቱታ እውነት መሆኑን፣
    - የተጠየቀውን ገንዘብ እውነተኛነትና

- ተከሳሹ ለቀረበው ክስ ምንም ዓይነት ማስተባበያ ሊያቀርብ የማይችል መሆኑን የሚገልፅ ሆኖ መዘጋጀት አለበት፡፡

➢ ቴክኒካዊ ነገሮች የሚመረመሩት በፍ/ቤቱ ሬጅስትራር ወይም የመዝገብ ቤት ሹም አማካኝነት ነው፡፡ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ነገሮች ካልተሟሉ የፍ/ቤቱ ሬጅስትራር ወይም የመዝገብ ቤት ሹም የቀረበው የክስ አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብሎ መመለስ አለበት፡፡ **(የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 229)**

ii. <u>ህጋዊ ነገሮች /Legal Requirements/</u>

➢ የሚረጋገጥ በችሎቱ ዳኛ አማካኝነት ነው፡፡ **(በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 231)**

➢ ህጋዊ ነገሮች የሚባሉት፡-

ሀ) ለክሱ ምክንያት የሆኑ ነገሮች መኖር አለመኖር **(ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 231(1)(ሀ) እና 222(1)(ረ))**

❖ ለክሱ ምክንያት የሆኑት ነገሮች ግልፅ በሆነ ሁኔታ በክሱ ማመልከቻ ውስጥ መቀመጥ አለባቸው፡፡

ለ) ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ያለው መሆን አለመሆኑ **(ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 231(1)(ለ))**

➢ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ነገሮች ካልተሟሉ ፍ/ቤቱ የቀረበለትን የክስ አቤቱታ አልቀበልም የሚልበትን ምክንያት በመግለፅ ተቀባይነት የለውም ብሎ ሊመልሰው ይችላል፡፡ **(የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 231)**

በአጠቃላይ በማናቸውም የክስ ፅሁፍ ላይ ሊኖሩ የሚገባቸው ነገሮች፡-

ሀ) <u>መግለጫ /Caption/</u>

➢ ክሱ የተፃፈበትን ቀን

➢ ክሱ የሚቀርብለትን ፍ/ቤት ሥምና አድራሻ

➢ የከሳሽን ስም፣ ልዩ መግለጫውን፣ የሚኖርበትን ቦታ

➢ የተከሳሽን ስም፣ ልዩ መግለጫውን፣ የሚኖርበትን ቦታና መጥሪያው የሚሰጥበትን አድራሻ

- የክሱን አርዕስት
- ከሳሽ ወይም ተከሳሽ በህግ ችሎታ የሌለው ከሆነ ይህ መገለፅ አለበት፡፡
- ከሳሹ ክስ የሚያቀርበው በጠበቃነት፣ በነገረ-ፈጅነት፣ ወይም በወኪልነት ከሆነ ክሱን ለማቀረብ ያለውን ሥልጣን መግለፅ አለበት፡፡

ለ) <u>ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ተቀብሎ ለማየት ሥልጣን ያለው መሆኑ መገለፅ አለበት /Jurisdiction/</u>

- ብሄራዊ የዳኝነት ሥልጣን
- የሥረ-ነገር የዳኝነት ሥልጣን
- አካባቢያዊ የዳኝነት ሥልጣን

ሐ) <u>የክሱ ዝርዝር ሁኔታ በአጭሩ መገለፅ አለበት /Cause of action/</u>

- ለክሱ ምክንያት የሆኑትን ነገሮች
- ለክሱ ምክንያት የሆኑት ነገሮች የተፈጠሩበትን ጊዜና ሥፍራ
- ተከሳሹ ለክሱ ምክንያት በሆነው ነገር ውስጥ ተጠሪ የሚሆንበትን ምክንያት ወይም በአላፊነት የሚጠየቅበትን ሁኔታ
- ለክሱ ምክንያት የሆነው ነገር ግምት (እንደአስፈላጊነቱ)

መ) <u>የተጠየቀው ዳኝነት ምን እንደሆነ መግለፅ /Relief/</u>

- ከሳሹ በሚያቀርበው የክስ ማመልከቻ ላይ በተለይ፣ ወይም በምትክ፣ ወይም በተለዋጭ የሚጠይቀውን ዳኝነት መግለፅ አለበት፡፡ (የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 224(1))
- ክሱ በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ከሆነ በክሱ ማመልከቻ ላይ ንብረቱን ለይቶ ለማወቅ የሚያስችሉት ምልክቶች መገለፅ አለባቸው፡፡(የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 225(2))
  - አዋሳኞቹ
  - የመዝገብ ቁጥር ወዘተ...
- ክሱ የሚቀርበው በገንዘብ የሆነ እንደሆነ ከሳሹ የሚጠይቀውን የገንዘብ መጠን በማመልከቻው ላይ መግለፅ አለበት፡፡(የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 226(1))
- ክሱ የሚቀርብበት ነገር የገንዘቡ ልክ ያልታወቀ እንደሆነ በሚቀርበው የክስ ማመልከቻ ላይ የገንዘቡ ግምት መቀመጥ አለበት፡፡ (የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 226(2))

- ክሱ የሚቀርበው የገንዘቡ ልክ በታወቀ ነገር የሆነ እንደሆነ በሚቀርበው የክስ ማመልከቻ ላይ የነገሩ ትክክለኛ ዋጋ መቀመጥ አለበት፡፡ (የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 226(3))

<u>ምሳሌ</u>

ቀጥሎ ያለውን ፍሬ-ነገር መሰረት በማድረግ ክስ መስርቱ፡፡

<u>ፍሬ ነገሩ</u>

- አቶ ከበደ ዓለማየሁ ታርጋ ቁጥሩ አ.ማ 00507 የሆነ ባጃጅ ተሽከርካሪ ባለቤት ናቸው፡፡
- ይህችን ባጃጅ የአብክመ የህግ ማሰልጠኛ ማዕከል ለሰራተኞቹ ሰርቪስ እንድትሰጥ በቀን ብር 100.00 /አንድ መቶ ብር/ ተከራይቷታል፡፡
- መስከረም 30 ቀን 2003 ዓ.ም ባጃጇ ለሰራተኞች በውሉ መሰረት ሰርቪስ ለመስጠት ወደ ማሰልጠኛ ማዕከሉ በመጓዝ ላይ ሳለች የጎን ቁጥሩ አማ 00037 የሆነ አይሱዙ መኪና ባጃጇን በመግጨት አደጋ አድርሶባታል፡፡
- በዚህ አደጋ ምክንያት ባጃጇ ያለሥራ ለአስር ቀናት ለጥገና በመቆየቷ፡-
  - ለጋራዥ ብር 3000.00 /ሶስት ሺህ ብር/
  - ለሰራተኛ ደመወዝ ብር 300.00 /ሶስት መቶ ብር/ - ለአስር ቀናት በቀን ብር 30.00 /ሰላሳ ብር/ ሂሳብ
  - ባጃጁ ቢሰራ ኖሮ በቀን ያገኝ የነበረው ብር 100.00 /አንድ መቶ ብር/ በአስር ቀናት ተባዝቶ ይገኝ የነበረውን ብር 1000.00 /አንድ ሺህ ብር/
    - ⇒ በድምሩ ብር 4300.00 /አራት ሺህ ሶስት መቶ ብር/ የጉዳት ካሳ

<u>ከሳሹ በማስረጃነት</u>

- የባጃጁን ሊብሬ
- ከሥልጠና ማዕከሉ ጋር ስምምነት ያደረጉበትን የውል ሰነድ
- አደጋው የደረሰ በአቶ ተሾመ ይሁኔ አይሱዙ መኪና ምክንያት መሆኑን የሚያስረዳ የቴክኒክ ማስረጃ
- አደጋው ሲፈፀም የተመለከቱ የሶስት ምስክሮችን ስም ዝርዝር
- ገንዘብ የተከፈለባቸው ልዩ ልዩ ደረሰኞች አቅርቧል፡፡

ጥቅምት 12 ቀን 2003 ዓ.ም

ለባህር ዳር ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት

ባህር ዳር

ከሳሽ...አቶ ከበደ ዓለማየሁ፣ አድራሻ ባህር ዳር ከተማ ቀበሌ 13 የቤት ቁጥር 523
ተከሳሽ...አቶ ተሾመ ይሁኔ፣ አድራሻ ባህር ዳር ከተማ ቀበሌ 04 የቤት ቁጥር 211

የክሱ አርዕስት፡- በከውል ውጭ አላፊነት ምክንያት ለደረሰ ጉዳት የካሳ ጥያቄ ነው።

ሀ. በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 222 መሰረት የቀረበ አቤቱታ ነው።
ለ. ፍ/ቤቱ አቤቱታውን ተቀብሎ ለማየት ሥልጣን አለው።

የአቤቱታው ምክንያት በአጭሩ

መስከረም 30 ቀን 2003 ዓ.ም ከቀኑ 6፡00 ሰዓት ላይ ታርጋ ቁጥሯ አ.ማ. 00507 የሆነች ባጃጅ ተሽከርካሪዬ ለአብክመ የህግ ማሰልጠኛ ማዕከል ሰራተኞች ሰርቪስ ለመስጠት ወደ ማሰልጠኛ ማዕከሉ በመንገዝ ላይ ሳለች ከአብክመ ገጠር መንገዶች ባለስልጣን መ/ቤት ፊት ለፊት ካለው አደባባይ ላይ የጎን ቁጥሩ አ.ማ. 00037 የሆነ የተከሳሹ አይሱዙ መኪና ባጃጇን ቀድሞ ለማለፍ ሲሞክር በመግጨት ጉዳት አድርሶባታል።

ባጃጇ በደረሰባት ጉዳት ምክንያት :-

1. *ያለ ሥራ ለጥገና ለአስር ቀናት የቆመች ሲሆን ባጃጇን ለማስጠገን ለጋራዥ ብር 3000.00 (ሶስት ሺህ ብር)፣*
2. *በቀን 30.00 (ሰላሳ ብር) ሂሳብ ለአስር ቀናት ለባጃጇ ሾፌር ደመወዝ የከፈልኩት ብር 300.00 (ሶስት መቶ ብር)፣ እና*
3. *ከአብክመ የህግ ማሰልጠኛ ማዕከል ጋር የሰርቪስ አገልግሎት ለመስጠት በነበረኝ ውል መሰረት በቀን አገኘው የነበረ ብር 100.00 (አንድ መቶ ብር) በአስር ቀናት ተባዝቶ ባጃጇ ባለመስርቷ ምክንያት የቀረብኝ ብር 1000.00 (አንድ ሺህ)*

⇒ *በድምሩ ብር 4300.00 (አራት ሺህ ሶስት መቶ ብር) ጉዳት ደርሶብኛል።*

ከሳሽ ከተከሳሽ የምጠይቀው፡-

1. *ባጃጇ በደረሰባት ጉዳት ምክንያት የደረሰብኝን የጉዳት ካሳ ብር 4300.00 (አራት ሺህ ሶስት መቶ ብር)፣*
2. *ለአቤቱታ ማስፃፊያ ያወጣሁት ብር 300.00 (ሶስት መቶ ብር)*

⇒ *በድምሩ ብር 4600.00 (አራት ሺህ ስድስት መቶ ብር) ጉዳት ደርሶብኛል።*

በዚህም መሰረት ከላይ በዝርዝር በማስፈር ለገለፅኩት ለደረሰብኝ ከውል ውጭ ኃላፊነት ጉዳት ከህጋዊ ወለድ ጋር ታስቦ ተከሳሹ እንዲክሰኝ እንዲወሰንልኝ ስል ለተከበረው ፍ/ቤቱ አመለክታለሁ።

ከዚህ በላይ የተገለፀው በሙሉ እውነት መሆኑን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 92 መሰረት አረጋግጣለሁ።

አመልካች
የማይነበብ ፊርማ
(የጣት አሻራ)
አቶ ከበደ ዓለማየሁ

2.3. <u>በፍትሃ ብሄር አቤቱታ ፅሁፍ ላይ የሚታዩ ችግሮች</u>

የፍትሃ ብሄር አቤቱታ ጽሁፍ ሲዘጋጅ ከላይ የተገለፁትን ሁኔታዎች ባሟላ መልኩ መሆን ሲገባው በአብዛኛው ከእነዚህ ነገሮች በማፈንገጥ ስለሚፃፉ በጽሁፎቹ ውስጥ ችግሮች ጎልተው ይታያሉ። ከሚታዩት ችግሮች ጥቂቶቹ፡-

- አላስፈላጊ ነገሮችን ማካተት
  - ፍ/ቤቱ የሚልከውን መጥሪያና ትዕዛዝ ለተከሳሹ ማድረስ እችላለሁ
  - ከሳሽ ተከሳሽ የህግ ችሎታ አለን
  - ክሱን የምከታተለው ራሴ ነኝ
  - ከሳሽ ክሱን የምከታተለው በጠበቃ ነው፤ ስለተከሳሽ ግን የማውቀው ነገር የለም ወዘተ...

- ክሱን ማንዛዛት
- ሥልጣን ለሌለው ፍ/ቤት ክስን ማቅረብ
- የተጠየቀው ዳኝነት ምን እንደሆነ በግልፅ አለማስቀመጥ
- ዳኞች በክሱ ውስጥ የህግ ድንጋጌ አላካተትክም በማለት ክሱን አሻሽሎ እንዲመጣ ለተከሳሽ መመለስ
- ብዙ ጊዜ በእጅ ተፅፎ የሚቀርብ የክስ ማመልከቻ ለማንበብ አስቸጋሪ መሆን
- የማስረጃ ዝርዝርን ከክሱ ፅሁፍ ጋር በአንድ ላይ ማዘጋጀት

3. <u>የፍትሃ ብሄር መከላከያ መልስ ምን ምን ነገሮችን ይይዛል?</u>

ሀ) <u>መግለጫ</u>

- መልሱ የተፃፈበት ቀን
- መልሱ የሚቀርብለትን ፍ/ቤት ሥምና አድራሻ (**የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ** 234(1)(ሀ))
- የክሱን መዝገብ ቁጥር (**የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ** 234(1)(ለ))
- የከሳሽን ስም
- የተከሳሽን ስም

ለ) <u>የመከላከያ መልስ</u>

- የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ (እንደአስፈላጊነቱ)
  - ክሱ በቀደምትነት በሌላ ፍ/ቤት እየታየ ነው። (**የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ** 7 እና 244(1)(ሐ))
  - ክሱን ያቀረበው ሰው በህግ ችሎታ የለውም። (**የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ** 34)
  - በክሱ ውስጥ የሚያገባቸው ወገኖች ሳይገቡ ቀርተዋል። (**የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ** 39(2))
  - የማያገባቸው ወገኖች በክሱ ተካፋይ ሆነዋል። (**የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ** 216(3)ና (4) እና 244(1)(መ))
  - ከሳሽ ከዚህ በፊት በከሰሰው ክስ ላይ ሊከስበት ሲችል ሆን ብሎ ያስቀረው ሀብት ስለሆነ አሁን በዚህ ጉዳይ ክስ ሊያቀርብበት አይችልም። (**የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ** 220)

- ክሱ ተጣምሮ የቀረበ ያላግባብ ነው፡፡ (የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 7)
- ፍ/ቤቱ ነገሩን ለመስማት ሥልጣን የለውም፡፡ (የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 244(2)(ሀ))
- ክስ የቀረበበት ጉዳይ አስቀድሞ በፍ/ቤት የተወሰነ ነው፡፡ (የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 244(1)(ለ))
- ክሱ በይርጋ የታገደ ነው፡፡ (የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 244(1)(ሠ))
- ክሱ የቀረበበት ጉዳይ በሽምግልና ታይቶ በስምምነት የተፈፀመ ነው ወይም ለእርቅ የተቀጠረ ነው፡፡ (የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 244(1)(ረ))
- ክስ የቀረበበት ሀብት ግምቱ በዝቷል፡፡ (የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 250)
- የውል ሰነዱ ህጋዊነትን የጠበቀ አይደለም፡፡ ወዘተ...

➢ ለቀረበው ክስ መከላከያ የሚሆን መልስ

- ክስ የቀረበበት ሀብት የለብኝም፡፡
- ውል የለኝም፡፡
- ውሉን መፈፀም ያለበት እሱ እንጅ እኔ አይደለሁም፡፡
- ከዚህ በፊት ያበደርኩት ይህን ያህል ገንዘብ እሱ ላይ ስላለ ይቻቻልል ወ.ዘ.ተ ሊሆን ይችላል፡፡
- በዚህ ጊዜ፡-
  - ⇒ የመከላከያ መልሱ ሲዘጋጅ በክሱ ማመልከቻ ውስጥ ከተጠቀሱት ነገሮች ውጭ የሆኑ አዲስ ነገሮች እንዳይነሱ ጥንቃቄ በማድረግ መዘጋጀት አለበት፡፡
  - ⇒ በክሱ ማመልከቻ ላይ ለተገለፁትና ለሚካዱት ነገሮች ሁሉ በግልፅና በዝርዝር የሚያስተባብል መልስ መሰጠት አለበት፡፡ ምክንያቱም በግልፅ ያልተካደ ጉዳይ እንደታመነ ስለሚቆጠር
  - ⇒ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ እና የይቻቻል መልስ የሚሰጥ ከሆነ ይህንን አስተካክሎ መግለፅ አስፈላጊ ነው፡፡

<u>ምሳሌ</u>፡-

እነዚህን በተከሳሹ (በአቶ ተሾመ ይሁኔ) የተነሱትን የመልስ ፍሬ-ነገሮች መሰረት በማድረግ መልስ ፃፉ፡፡

➢ አደጋው በእርሱ መኪና አማካኝነት መድረሱን አምኗል፤ ሆኖም በመከራከሪያነት፡-

- ለባጃጁ ማስጠገኛ ወጣ የተባለው ወጭ የተጋነነ ነው፤

- ❖ በከሳሽ (በአቶ ከበደ ዓለማየሁ) የቀረበው የውል ሰነድ ህጋዊነትን የጠበቀ አይደለም፤
- ❖ አደጋው ከመድረሱ አንድ ሳምንት በፊት መኪናዬ ባልታወቀ ሰው ተሰርቆ ስለነበር ለደረሰው ጉዳት ጥፋትና ኃላፊነት የለብኝም የሚሉ ነጥቦችን አንስቷል፡፡

➢ በማስረጃነትም፡-

- ❖ ተከሳሹ መኪናው ካቆመበት ቦታ የጠፋ መሆኑን ለ4ኛ ፖሊስ ጽ/ቤት ያመለከተ መሆኑን የሚገልፅ ደብዳቤ
- ❖ የመኪናውን ሊብሬ አያይዞ አቅርቧል፡፡

የፍ/ብ/መ/ቁ----------
ቀን----------

ለባህር ዳር ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት
<u>ባህር ዳር</u>

ከሳሽ...አቶ ከበደ ዓለማየሁ፣ አድራሻ ባህር ዳር ከተማ ቀበሌ 13 የቤት ቁጥር 523
ተከሳሽ...አቶ ተሾመ ይሁኔ፣ አድራሻ ባህር ዳር ከተማ ቀበሌ 04 የቤት ቁጥር 211

<u>ከሳሽ በ12/02/2003 ዓ.ም ጽፎ ላቀረው ክስ ከተከሳሽ የተሰጠ የመቃወሚያና የፍሬ-ነገር መልስ</u>

ሀ) <u>የተከሳሽ አቤቱታ በአጭሩ</u>

ከሳሽ የተከሳሽ አይሱዙ መኪና ባጃጅን በመግጨት ጉዳት ያደረሰባት በመሆኑ ባጃጇን ለማስጠገን፣ ለባጃጇ ሾፌር ደመወዝ የከፈልኩት፣ ባጃጇ ለጥገና ያለሥራ በመቆሟ ምክንያት የቀረብኝ ገቢና ሌሎች ልዩ ልዩ ወጭወችን በመጨመር በድምሩ ብር 4600.00 (አራት ሺህ ስድስት መቶ ብር) ጉዳት የደረሰብኝ ስለሆነ ይህ የደረሰብኝ ጉዳት ከህጋዊ የባንክ ወለድ ጋር ታስቦ ተከሳሹ እንዲከፍለኝ እንዲደረግልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ለ) <u>የመቃወሚያ መልስ</u>

1. ***ለማስጠገኛ ወጣ የተባለው ወጭ የተጋነነ ስለሆነ በከሳሽ የቀረበውን የማስጠገኛ ወጭ እቃወማለሁ፤***
2. ***ከሳሽ ከአብክመ የህግ ማሰልጠኛ ማዕከል ጋር የሰርቪስ አገልግሎት ለመስጠት ከማዕከሉ ጋር ውል አለኝ በማለት በማስረጃነት አያይዞ ያቀረበው የውል ሰነድ ህጋዊነትን የጠበቀ ባለመሆኑ የውሉን ሰነድ የምቃወመው በመሆኑ ፍ/ቤቱ ወደ ዋናው ጉዳይ ገብቶ ከማከራከሩ በፊት ይህንን የውል ሰነድ ህጋዊነት የለውም በማለት ውድቅ እንዲያደርግልኝ እጠይቃለሁ፡፡***

ሐ) <u>የፍሬ-ነገር መልስ</u>

እነዚህ የጠቀስኪቸው መቃወሚያዎች እንደተጠበቁ ሆነው ወደ ዋናው ፍሬ ነገር በመግባት ለቀረበብኝ ክስ የመከላከያ መልሴን ሳቀርብ ምንም እንኳ ክሳሹ በአቤቱታው እንደገለፀው በባጃጂ ላይ የደረሰው ጉዳት በተከሳሽ አይሱዙ መኪና መሆኑ ባይካድም አደጋው ከመድረሱ አንድ ሳምንት በፊት መኪናዬ ባልታወቀ ሰው ተሰርቆ ስለነበር ለደረሰው ጉዳት ተጠያቂ መሆን ያለበት ጉዳቱ በደረሰበት ወቅት መኪናውን ሰርቆ የነበረው ሰው እንጅ ተከሳሽ ለደረሰው ጉዳት ጥፋትና ኃላፊነት ስለሌለብኝ ተጠያቂ ልሆን አይገባኝም በማለት መልሴን አቀርባለሁ::
ይህ መልስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 92 መሰረት በእውነት የቀረበ መሆኑን አረጋግጣለሁ::

መልስ ሰጪ

አቶ ተሾመ ይሁኔ

3.1. <u>በፍትሃ ብሄር መልስ ፅሁፍ ላይ የሚታዩ ችግሮች</u>

- የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያን ብቻ በመልሱ ላይ በመግለፅ ለቀረበው ክስ የመከላከያ መልስ አለመስጠት
- የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያን እና የመከላከያ መልስን አደበላልቆ ማቅረብ
- ክሱ በሚሰማበት የመጀመሪያ ቀን መነሳት የነበረባቸውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች በመከላከያ መልሱ ላይ ሳያቀርቡ በሌላ ጊዜ በቃል ማንሳት
  - ይርጋን የተመለከቱ ጉዳዮች /Period of limitation/
  - የመጨረሻ ውሳኔ ያገኙ ጉዳዮች /Resjudicata/
  - በግልግልና በሽምግልና ያለቁ ጉዳዮች /Compromise and arbitration/
  - ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ተቀብሎ ለማየት ሥልጣን የሌለው መሆኑን /Jurisdiction/- በተለይ፡-
    - ብሄራዊ የዳኝነት ሥልጣን /Judicial jurisdiction/
    - አካባቢያዊ የዳኝነት ሥልጣን /Local jurisdiction/
- በክሱ ማመልከቻ ላይ ለተገለፁትና ለሚካዱት ነገሮች ሁሉ በግልፅና በዝርዝር የሚያስተባብል መልስ አለመስጠት
- ብዙ ጊዜ በእጅ ተፅፎ የሚቀርብ መልስ ለማንበብ አስቸጋሪ መሆን

4. <u>የይግባኝ ማመልከቻ ምን ምን ነገሮችን ይይዛል?</u> (የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 327)

- ይግባኙ የተባፈበትን ቀን
- ይግባኝ የቀረበበትን ፍ/ቤት ሥምና የሚያስችልበትን ቦታ
- ይግባኝ የተባለበትን ፍርድ
  - የሰጠው ፍ/ቤት ሥም
  - ፍርዱ የተወሰነበትን ቀን
  - የመዝገቡ ቁጥር
- የመልስ ሰጭውን አድራሻ
- ለይግባኙ ምክንያት የሆኑትን ነገሮች ዝርዝር
- በይግባኙ እንዲታረም የሚፈለገውን ዝርዝር
- የሚጠየቀውን ዳኝነት ዓይነት
- ይግባኝ ባዩ ይግባኙን የሚመሰርተው ፍርዱ በተሰጠበት መዝገብ ላይ ብቻ ከሆነ ይህንኑ በይግባኝ ማመልከቻው ላይ መግለፅ አለበት
- ተጨማሪ ማስረጃ ለማቅረብ እንዲፈቀድለት የሚጠይቅ ሲሆን፡-
  - እንዲታይለት የሚጠይቀውን የማስረጃ ዝርዝር እና/ወይም
  - እንዲሰሙለት የሚፈልጋቸውን ምስክሮች ስም
  - ማስረጃው ወይም ምስክሮች በመጀመሪያው ክርክር ላይ ሳይታይለት ወይም ሳይሰሙለት የቀሩበትን ምክንያት
  - ተጨማሪ ማስረጃ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ሊታይልኝ ይገባል የሚልበትን ምክንያት በዝርዝር የሚገልፅ ሌላ ፅሁፍ ከይግባኝ ማመልከቻው ጋር አያይዞ ያቀርባል፡፡

5. <u>የወንጀል ክስ ማመልከቻ ማዘጋጀት</u>

በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 37 መሰረት የፖሊስ የምርመራ መዝገብ የደረሰው ዐ/ህግ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 38 መሰረት፡-

- ክስ አዘጋጅቶ ለፍ/ቤት ሊያቀርብ ይችላል፤ ወይም
- ተጨማሪ ምርመራ እንዲደረግ ፖሊስን ሊያዝዝ ይችላል፤ ወይም
- ክስ አልመሰርትም ብሎ በመወሰን መዝገቡን ሊዘጋ ይችላል፡፡

5.1. <u>ቅድመ የወንጀል ክስ ዝግጅት</u>

የፖ/ሊስ የምርመራ መዝገብ የደረሰው ዐ/ህግ ክስ አዘጋጅቶ ለፍ/ቤት ከማቅረቡ በፊት፡-

- በፖ/ሊስ ምርመራ የተጣራበት ጉዳይ የወንጀል ተግባር መሆን አለመሆኑን ማረጋገጥ (ወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 23)
  - የህግ ፍሬ ነገር /Legal Element/
  - የድርጊት ፍሬ ነገር /Material Element/ እና
  - የሀሳብ ፍሬ ነገር /Mental Element/
- በፖ/ሊስ ምርመራ ተጣርቶ የቀረበው ጉዳይ የምክንያትና የውጤት ግንኙነት ያለው መሆኑን ማረጋገጥ (ወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 24)
- ተጠርጣሪው የቀድሞ የጥፋተኝነት ሪከርድ ያለበት ወይም የሌለበት መሆኑን ማረጋገጥ (ወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 114)
- ከፖ/ሊስ የተላከው የምርመራ መዝገብ ተጠርጣሪውን ጥፋተኛ ለማሰኘት በቂ መሆን አለመሆኑን ማረጋገጥ (ወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 42(1)(ሀ))
- ተጠርጣሪውን ለማግኘት የሚቻል ወይም የማይቻል መሆኑን ማረጋገጥ (ወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 42(1)(ለ))
- ተጠርጣሪው ያልተያዘ ከሆነ ክሱ በሌለበት የሚታይ ወይም የማይታይ መሆኑን ማረጋገጥ (ወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 42(1)(ለ))
- ክሱን ለማቅረብ በይርጋ የታገደ ወይም ያልታገደ መሆኑን ማረጋገጥ (ወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 42(1)(ሐ))
- ተጠርጣሪው በይቅርታ ወይም በምህረት የተለቀቀ ወይም ያልተለቀቀ መሆኑን ማጣራት (ወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 42(1)(ሐ))
- ጉዳዩን ለማየት የሥረ-ነገርና የአካባቢ የዳኝነት ሥልጣን ያለው የትኛው ፍ/ቤት እንደሆነ መለየት፤ ምክንያቱም ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ከሌለው የክሱን ማመልከቻ አልቀበልም ብሎ ይመልሰዋል (ወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 110)
- ሌላ ተመሳሳይ ክስ በሌላ ፍ/ቤት መኖር አለመኖሩን ማጣራት (ወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ130(2)(ሀ))
- ጉዳዩ ቀደም ሲል በሌላ ፍ/ቤት ውሳኔ የተሰጠበት ወይም ያልተሰጠበት መሆኑን ማረጋገጥ፣ ምክንያቱም፡-
  - ማንኛውም ሰው በወንጀል ህግና ሥነ-ስርዓት መሰረት ተከሶ የመጨረሻ በሆነ ውሳኔ ጥፋተኛነቱ በተረጋገጠበት ወይም በነፃ

በተለቀቀበበት ወንጀል እንደገና አይከሰስም ወይም አይቀጣም **(የአፌድሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 23)**

- ማንም ሰው በህግ መሰረት የመጨረሻ በሆነ ውሳኔ ጥፋተኛነቱ ተረጋግጦ ከዚህ ቀደም በተቀጣበት ወይም ሌላ ህጋዊ ርምጃ በተወሰደበት ወይም በነፃ በተለቀቀበት ወንጀል እንደገና አይከሰስም ወይም አይቀጣም **(የአፌድሪ የወንጀል ህግ አንቀፅ 2(5))**

- ክሱ ተነጥሎ አለመቅረቡ በተከሳሽ ላይ ጉዳት የሚያስከትል ወይም የማያስከትል መሆኑን ማጣራት **(ወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ130(2)(መ))**
  - በፖሊስ ተጣርቶ የቀረበው የምርመራ መዝገብ የሚያሳየው ድርጊቱ የተፈፀመ በብዙ ሰዎች መሆኑን ቢሆንና አንዱ ተከሳሽ ለብቻው ከሌሎች ተከሳሾች ተነጥሎ ክሱ ባይታይለትና አብሮ ከሌሎች ተከሳሾች ጋር ክሱ መታየቱ የሚጎዳው ሆኖ ከተገኘ

- ተጠርጣሪው ምርመራ የተጣራበት በአንድ ወንጀል ነው ወይስ ከአንድ በላይ በሆነ ወንጀል የሚለውን ጉዳይ ማጣራት **(ወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ112)**

- ከቀረበው የምርመራ መዝገብ ዓይን ሲታይ ክሱ ራሱን ችሎ የሚቀርብ ነው ወይስ በአማራጭ ቢቀርብ ነው የተሻለ የሚለውን በመመመርመር ውሳኔ ላይ መድረስ **(ወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ113)**

- ክስ ለማቅረብ ፈቃድ ማግኘት አስፈላጊ መሆን አለመሆኑን ማረጋገጥ ተገቢ ይሆናል፤ ምክንቱም፡-
  - ማንኛውም የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት አባል ከባድ ወንጀል ሲፈፅም እጅ ከፍንጅ ካልተያዘ በስተቀር ያለ ም/ቤቱ ፈቃድ አይያዝም፤ አይከሰስም፡፡ **(የኢፌድሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 54(6))**
  - አካለ መጠን ባላደረሰ ወጣት ላይ የቀረበው ክስ ከአስር ዓመት በላይ በሆነ ፅኑ እስራት ወይም በሞት የሚያስቀጣ በሆነ ጊዜ ዐ/ህጉ የክስ ማመልከቻውን አዘጋጅቶ እንዲያቀርብ ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ መስጠት አለበት፡፡ **(ወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 172(3))**

5.2. <u>የወንጀል ክስ ማመልከቻ አጠቃላይ ይዘት</u>

ዐ/ህግ የፖሊስ የምርመራ መዝገብ ወይም የቀዳሚ ምርመራ አድራጊ ፍ/ቤት መዝገብ ከደረሰው በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የሚያስከስስ ሆኖ ካገኘው በ15 ቀን ጊዜ ውስጥ ተገቢውን ክስ አዘጋጅቶ ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት ማቅረብ አለበት፡፡ **(የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ** 109(1))

በአቃቢ ህግ የሚዘጋጀው የወንጀል ክስ ማመልከቻ ቀጥሎ ያሉትን ነገሮች መያዝ አለበት፡፡

- ክሱ ወጭ የሆነበትን ፕሮቶኮል ቁጥር
- ክሱ ወጭ የሆነበትን ቀን
- ክሱ የሚቀርብለትን ፍ/ቤት ሥምና አድራሻ
- የወረዳውን ፍ/ጽ/ቤት መዝገብ ቁጥር
- ምርመራውን ያጣራውን ፖሊስ ጽ/ቤት ወንጀል ምርመራ መዝገብ ቁጥር
- ክሱ የሚቀርብለትን ፍ/ቤት የወንጀል መዝገብ ቁጥር
- የከሳሹን ማንነት (ዐ/ህግ ወይም የግል ከሳሽ)
  - ❖ በመርህ ደረጃ በማናቸውም ጉዳይ ላይ ፍርድ እንዲሰጥና ቅጣት እንዲወሰን ለማድረግ የወንጀል ክስ የሚቀርበው በዐቃቤ ህግ ነው፡፡
  - ❖ በልዩ ሁኔታ ግን በህግ ተደንግጎ ከተገኘ የወንጀል ክስ ከዐቃቤ ህግ ውጭ በሆነ አካል ሊቀርብ ይችላል፡፡

    <u>ለምሳሌ</u>፡-

    ⇒ በግል አቤቱታ የሚቀርብን ክስ ዐ/ህግ በቂ የሆነ ማስረጃ የለም በማለት ክስ አልመሰርትም ካለ የግል ከሳሽ ከዐ/ህጉ ፈቃድ ጠይቆ የወንጀል ክስ ሊመሰርት ይችላል፡፡ **(የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ** 44(1))፣

    ⇒ የደንብ መተላለፍ ወንጀል በተፈፀመ ጊዜ የግል ከሳሽ የሆነ ሰው ተከሳሹ እንዲጠራ ፍ/ቤቱ መጥሪያ እንዲሰጠው ሊያመለክት ይችላል፡፡ 167(1))
- የተከሳሹን ስም፣ ዕታ፣ ዕድሜ እና አድራሻ
- የተጣሰውን የወንጀል ህግ አንቀፅ
- የወንጀሉን ዝርዝር፡-

- ❖ ወንጀሉ የተፈፀመበትን ጊዜና ቦታ
- ❖ የተበዳይን ማንነት
- ❖ ወንጀል የተፈፀመበትን ንብረት ወይም መብት
- ❖ የወንጀሉን አፈፃፀም ሁኔታ ከህጉ ጋር በማገናዘብ

⇒ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ወንጀሎች የተፈፀሙ ከሆነ 1ኛ፣ 2ኛ፣3ኛ... ክስ እየተባለ በርዕስ ተለይቶ መገለፅ አለበት፡፡

⇒ የተጣሰው የህግ አንቀፅ የትኛው እንደሆነ ለመወሰን አሻሚ በሚሆንበት ጊዜ ዐ/ህጉ በይበልጥ ተጥሷል ብሎ የሚያምንበት ድንጋጌ በመጥቀስ ክስ ካዘጋጀ በኋላ በተጨማሪም ሌላውን አማራጭ የህግ አንቀፅ በመጥቀስ ተተኪ ክስ ማቅረብ ይችላል፡፡ (ወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ113)

<u>ለምሳሌ</u>፡-

- ▪ ተከሳሹ የፈፀመው ወንጀል የስርቆት ነው ወይስ የመሸሸግ የሚለው ብዙ ጊዜ አጠራጣሪ ሲሆን እንመለከታለን፡፡ በዚህን ጊዜ ተከሳሹ ይበልጥ በማስረጃ ይረጋገጥበታል የሚባለው ወንጀል የስርቆቱ ከሆነ በዋነኝነት በስርቆት ወንጀል እንዲከሰስ ከተደረገ በኋላ በተጨማሪ በማስረጃ ሊረጋግጥ ይችላል በተባለው የመሸሸግ ወንጀል በአማራጭነት እንዲከሰስ ይደረጋል፡፡

➢ የማስረጃ ዝርዝር

- ❖ የሰው ማስረጃ ዝርዝር ከነአድራሻቸው
  - ▪ የዓይን ምስክር
  - ▪ አካባቢያዊ ምስክር
  - ▪ የስሚ ስሚ ምስክር ተብሎ መገለፅ አለበት፡፡
- ❖ የፅሁፍ/የሰነድ ማስረጃ፣
- ❖ የኤግዚቢት ማስረጃ

➢ ተከሳሹ ያለበትን ሁኔታ የሚያሳይ መግለጫ

- ❖ ተከሳሹ በፖ/ሊስ ወይም በፍ/ቤት በዋስ ተለቋል ወይም
- ❖ በማረሚ ቤት ይገኛል ወይም

- ❖ በፖሊስ ተይዞ ይቀርባል
- ❖ ራሱን ሰውሯል ወዘተ

➢ ክሱን ያዘጋጀው ዐ/ህግ ሥምና ፊርማ

➢ ክሱን የመሰረተው ፍ/ጽ/ቤት ወይም መምሪያ ማህተም ማረፍ አለበት

ምሳሌ፡-

ቁጥር----------

ቀን----------

ለባህር ዳር ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት

ባህር ዳር

የባህር ዳር ከተማ ወረዳ ፍ/ጽ/ቤት መ/ቁ----------

የባህር ዳር ከተማ ወረዳ ፖ/ጽ/ቤት ወ/ም/መ/ቁ----------

የባህር ዳር ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት የወ/መ/ቁ----------

ከሳሽ...ዐ/ህግ

ተከሳሽ...አቶ ዓለማየሁ ውዱ፣ ዖታ...ወንድ፣ ዕድሜ...28፣ አድራሻ...ባህር ዳር ከተማ፣ ቀበሌ 15

ወንጀሉ

የኢፌድሪ የወንጀል ህግ አንቀፅ 669(3)(ለ)ን በመተላለፍ የተፈፀመ የከባድ ስርቆት ወንጀል ነው::

የወንጀሉ ዝርዝር

ተከሳሹ መስከረም 25 ቀን 2003 ዓ.ም በግምት ከሌሊቱ 8:00 ሰዓት ሲሆን ጨለማን ተገን በማድርግ በባህር ዳር ከተማ ቀበሌ 04 የሚገኘውን የአቶ በለው ተሰማን መኖሪያ ቤት መስኮት ሰብሮ በመግባት አንድ ቶሽባ ላፕ ቶፕ ኮምፒውተርና አንድ ባለ 21 ኢንች ሳምሰንግ ባለቀለም ቴሌቪዥን በመስረቁ በፈፀመው የከባድ ስርቆት ወንጀል ተከሷል::

<u>*የማስረጃ ዝርዝር*</u>

ሀ. የፅሁፍ/የሰነድ/ ማስረጃ

1. *ቴሌቪዝኑ በነበረበት ቦታ ላይ ወድቆ የተገኘ የአቶ ዓለማየሁ ውዱ የቀበሌ መታወቂያ*
2. *በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 27(2) መሰረት ተከሳሹ በባህር ዳር ከተማ ወረዳ ፖሊስ ጽ/ቤት ወንጀል ምርመራ ክፍል ቀርቦ የሰጠውን የእምነት ቃል የያዘ ወረቀት*
3. *ኮምፒውተሩና ቴሌቪዥኑ የተገዙበት የደረሰኝ ወረቀቶች*

ለ. የኤግዚቢት ማስረጃ

ከተከሳሹ እጅ የተያዙ

1. *አንድ ቶሽባ ላፕ ቶፕ ኮምፒውተር*
2. *አንድ ባለ 21 ኢንች ሳምሰንግ ባለቀለም ቴሌቪዥን*

<u>*መግለጫ /ተከሳሹ ያለበት ሁኔታ*</u>

ተከሳሹ በፍ/ቤት በዋስ ተለቋል::

ከበደ ተሰማ

የባህር ዳር ከተማ ወረዳ ዐ/ህግ

5.3. <u>በወንጀል ክስ ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮች</u>

- ለክሱ አግባብነት ያለው የህግ አንቀፅ ለይቶ አለመጥቀስ

- በቂ ማስረጃ በሌለው ጉዳይ ክስ ማዘጋጀት
- መከሰስ የማይገባቸውን ሰዎች በክሱ ውስጥ ማካተት
- መከሰስ የሚገባቸውን ሰዎች በክሱ አለማካተት
- በተከሳሹ ላይ ከአንድ በላይ ክስ ማቅረብ ሲገባ አንድ ክስ ብቻ ማቅረብ
- ከአንድ በላይ ክስ በቀረበ ጊዜም የትኛው ማስረጃ የትኛውን ክስ እንደሚያስረዳ ለይቶ በግልፅ አለማመልከት
- የተከሳሽንም ሆነ የምስክሮችን አድራሻ በትክክል አለመመዝገብ
- የታይፕ ግድፈቶችን ሳያርሙ የክሱን ማመልከቻ ወደ ፍ/ቤት መውሰድ
- በክስ ማመልከቻው ላይ ዐ/ህጉ ሳይፈርምበት ወይም የመ/ቤቱ ማህተም ሳይደረግበት ክሱን ወደ ፍ/ቤት መውሰድ
- ወንጀሉ የተፈፀመበትን ጊዜና ቦታ በክስ ማመልከቻው ላይ አለመግለፅ
- በይርጋ የታገዱ ጉዳዮች ላይ ክስ መመስረት
- የግል ተበዳይና ተከሳሹ በሰጡት ቃል ላይ ብቻ ተመስርቶ ክስ መመስረት
- አግባብነት ያለውን አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ በትክክል ለይቶ አለማወቅ
- የተሻሩ የህግ ድንጋጌዎችን ጠቅሶ ክስ መመስረት
- ተጠርጣሪውን ***ተጠርጣሪው*** እያሉ ከመግለፅ ይልቅ ***ወንጀለኛው*** እያሉ መጥራት **(የህገ-መንግስቱን አንቀጽ20(3) የሚፃረር ስለሆነ)**
- ኤግዚቢት ባላቸው ጉዳዮች ላይ ኤግዚቢት መኖሩን በክሱ ቻርጅ ላይ አለማመልከት
- የምስክሮችን ቃል መሰረት አድርጎ ክስ ከማዘጋጀት ይልቅ ፖሊስ በምርመራው መዝገብ መቅድም ላይ የጠቀሰውን የወንጀል ዓይነት ጠቅሶ ክስ ማዘጋጀት
- የክስ ማመልከቻዎች ሲዘጋጁ የቃላት አሰካካቸውና የዐ/ነገር አወራረዳቸው ለአንባቢ በቀላሉ የማይገቡና ገላጭነት የጎደላቸው መሆን
- ብዙ ጊዜ ክሱ በእጅ ፅሁፍ የተዘጋጀ ከሆነ ለማንበብ አስቸጋሪ መሆን

6. <u>በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 38(ሐ) መሰርት የሚሰጥ የተጨማሪ ምርመራ ትዕዛዝ አፃፃፍ</u>

የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 38(ሐ) ተጨማሪ ትዕዛዝ የሚሰጥ መሆኑን ከሚገልፅ በቀር ይዘቱ እና ቅርፁ ምን መምሰል እንዳለበት በህጉ ላይ የተቀመጠ ነገር የለም፡፡ በሥነ-

ሥርዓት ህጉ ላይ ተያይዞ የሚገኝው ሰንጠረዥም ቢሆን ይህንን የሚያሰተናግድ ፎርም የለውም፡፡ሆኖም ግን በልማድ የሚታየው፣ የዳበረው ተቀባይነት ያገኘው የዐ/ህግ የተጨማሪ ምርመራ ትዕዛዝ የሚከተሉትን ነጥቦች ይዞ እናገኘዋለን፡፡

- የትዕዛዝ ጥያቄው ወጭ የሆነበት የኘሮቶኮል ቁጥርና ቀን፣
- ተጨማሪ ምርመራ እንዲያደርግ ትዕዛዝ የተሰጠውን መ/ቤት ስም፣
- ትዕዛዙን የሰጠውን መ/ቤት የመዝገብ ቁጥር፣
- የወንጀል ምርመራውን ያጣራው ፖሊስ ጽ/ቤት የመዝገብ ቁጥር፣
- ጉዳዩ፡- **በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 38(ሐ) መሰረት ተጨማሪ ምራመራ እንዲደረግ ስለማዘዝ፣**
- ተጨማሪ ምርመራ እንዲደረግ ያስፈለገበትን ምክንያት በበቂ ሁኔታ የሚተነትን ፅሁፍ፣
- መፈክር **(ከሰላምታ ጋር፣ ፍትህ ለሁሉም... ወዘተ)**
- ተጨማሪ ምርመራ እንዲደርግ ትዕዛዝ የሰጠው ዐ/ሕግ ስምና ፊርማ

<u>ለምሳሌ</u>፡-

<u>ተከሳሽ</u>፡- አቶ ወንድይፍራው ተሾመ

<u>የምርመራ መዝገቡ ፍሬ ነገር፣</u>

- ተከሳሹ የተከሰሰበት በ25/01/2003 ዓ.ም ከቀኑ 10፡00 ሰዓት ሲሆን ባህር ዳር ከተማ ቀበሌ 13 ልዩ ስሙ ድባንቄ ተብሎ ከሚጠራው ሥፍራ ከጫካ ውስጥ አድፍጦ በመጠበቅ ሟች አቶ ዓለማየሁ ሊጋባ የተባለው ለቅሶ ውሎ ወደ መኖሪያ ቤቱ ሲመለስ ተከሳሹ ሟቹን አስፈራርቶ በማስቆም በያዘው ክላሽን ኮኘ ጠብመንጃ ሁለት ጥይት ተኩሶ በአንደኛው ጥይት ቀኝ ጉኑን በመምታት ገድሎታል የሚል ነው፡፡

<u>የተከሣሾች ቃል ፣</u>

- ተከሳሹ ባህር ዳር ከተማ ... ፖሊስ ወንጀል ምርመራ ክፍል ቀርቦ በሰጠው የተከሣሽነት ቃል የተከሰስኩበትን ወንጀል አልፈፀምኩም ጥፋተኛም አይደለሁም ብሏል፡፡

<u>ማ ስ ረ ጃ</u>

- በተከሳሹ ላይ የቀረበውን ክስ ያስረዳሉ ተብለው ከቀረቡት ሶስት ምስክሮች መካከል 1ኛው ምስክር ሲያስረዳ ከላይ በተጠቀሰው ጊዜና ቦታ ታላቅ ወንድሜ የሆነው ሟች ከፊታችን እየሄደ እኛ ኋላ ኋላውን በመከተል ላይ እንዳለን ተከሳሹ ከተደበቀበት ጫካ በመውጣት በያዘው ክላሽን ኮኘ ጠብመንጃ አንድ

ጥይት ተኩሶ የቀኝ ጐኑን መቶት ሲወድቅለት የደስደስ አንድ ጥይት ወደ ሰማይ ተኩሶ ወደ ጫካው ውስጥ ሲሄድልን እኛም ወደ አየር ኃይል ካምፕ አቅጣጫ በመሐድ ጩኸት አሰምተን ሰው ሲሰበሰብልን አስከሬኑን አስነስተን ወደ መንደራችን ይዘነው ሄድን ሲል መስክሯል፡፡ የዚህን ምስክር ቃል መሰረት በማድረግ ተጨማሪ ምርመራ እንዲደረግ ትዕዛዝ ፃፉ፡፡

ቁጥር----------

ቀን----------

ለባህር ዳር ከተማ ... ፖሊስ ጽ/ቤት

<u>ባህር ዳር</u>

የዐ/ህ/መ/ቁ----------

የፖ/ወ/ም/መ/ቁ----------

ጉዳዩ፡- <u>በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 38(ሐ) መሰረት ተጨማሪ ምራመራ እንዲደረግ ስለማዘዝ</u>

አቶ ወንድይፍራው ተሾመ በተጠረጠረበት የሰው መግደል ወንጀል የተጣራበትን የምርመራ መዝገብ በቁጥር ፖ/ወ/ም 50/20306/03 በቀን 22/02/2003 ዓ.ም በተፃፈ ሸኝ ደብዳቤ አማካኝነት ልካችሁልን ደርሶን ተመልክተነዋል፡፡

ከምርመራ መዝገቡ ለመረዳት እንደቻልነው ተጠርጣሪው በ25/01/2003 ዓ.ም ከቀኑ 10:00 ሰዓት ሲሆን ባህርዳር ከተማ ቀበሌ 13 ልዩ ስሙ ድባንቄ ተብሎ ከሚጠራው ሥፍራ ከጫካ ውስጥ አድፍጦ በመጠበቅ ሟች አቶ ዓለማየሁ ሊጋባ ለቅሶ ውሎ ወደ መኗሪያ ቤቱ ሲመለስ ተጠርጣሪው ሟችን አስፈራርቶ በማስቆም በያዘው ክላሽንኮቭ ጠመንጃ ሁለት ጥይት ተኩሶ በአንደኛው ጥይት ቀኝ ጎኑን በመምታት ገሎታል ተብሎ በመጠርጠሩ በፖሊስ የተከናወነ የወንጀል ምርመራ ውጤት ነው፡፡

የምርመራ መዝገቡ እንደሚገልፀው ተጠርጣሪው በሰጠው ቃል የተከሰሰኩበትን ወንጀል አልፈፀምኩም፤ ጥፋተኛም አይደለሁም በማለት ድረጊቱን ክዷል፤ ሆኖም ግን ጉዳዩን ያስረዳሉ ተብለው ከተጠቀሱት የዓይን ምስክሮች ውስጥ በአንደኝነት የተመዘገበው ምስክር ሲያስረዳ ከላይ በተጠቀሰው ጊዜና ቦታ ታላቅ ወንድሜ የሆነው ሟች ከፊታችን እየሄደ እኛም ከኋላው እየተከተልነው እያለ ተጠርጣሪው ከተደበቀበት ቦታ በመውጣት ሟችን አስፈራርቶ በማስቆም በያዘው ክላሽንኮቭ ጠመንጃ አንድ ጥይት ተኩሶ የቀኝ ጎኑን መትቶት ሲወድቅ የደስ ደስ አንድ ጥይት ወደ ሰማይ ተኩሶ በጫካው ውስጥ ሲሄድልን እኛም ወደ አየር ኃይል ካምፕ አቅጣጫ በመሄድ ጩኸት አሰምተን ሰው ሲሰበሰብ አስከሬኑን አስነስተን ወደ መንደራችን ይዘነው ሄድን በማለት መስክሯል።

ከዚህ ምስክር ቃል ለመረዳት እንደቻልነው በተለያየ ጊዜ እንደገለፀው ምስክሩ ብቻውን አለመሆኑን የሚገልፁ ... ሟች ከፊታችን እየሄደ፤ እኛም ከኋላው እየተከተልነው ... በጫካው ውስጥ ሲሄድልን እኛም ወደ ... ጩኸት አሰምተን ... አስከሬኑን አስነስተን ወደ መንደራችን ይዘነው ሄድን።... የሚሉ ብዙነትን የሚገልፁ የተለያዩ ሀረጎችን ጠቅሷል፤ ይህ ማለት ደግሞ ሟች በተገደለበት ሰዓት ድርጊቱን ከአንደኛው ምስክር ጋር አብረው የተመለከቱ ሌሎች ሰዎች ነበሩ ማለት ነው።

ስለዚህ ክሳችንን በተጠናከረ መልኩ አዘጋጅተን ክስ ለመመስረት ያመቸን ዘንድ የእነዚህ ሰዎች በምስክርነት መካተት ወሳኝ ጉዳይ በመሆኑ እነዚህን ከአንደኛው ምስክር ጋር አብረው የነበሩትን ቀሪ ሰዎች አስቀርባችሁ ስለድርጊቱ የሚያውቁትን የምስክርነት ቃል እንዲሰጡ ታደርጉ ዘንድ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 38(ሐ) መሰረት እየገለፅን ከዚህ በፊት የላካችሁልንን 17 ገጽ የምርመራ መዝገብ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን መልሰን የላክንላችሁ መሆኑን እንገልፃለን።

"ከሠላምታ ጋር"

ሉሌ ተሰማ

ዐ/ህግ

<u>የመወያያ ጥያቄ</u>

<u>ቀጥሎ ያለውን በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 138(ሐ) መሰረት የተሰጠ የተጨማሪ ምርመራ ትዕዛዝ አንብቡና ያለበትን ችግር አውጡ።</u>

ቁጥር

81/ተ372/90

ቀን

11/01/91

የወረዳ 18 ፖ/ሊስ ጣቢያ

አዲስ አበባ፣

የዐ/ህግ መ/ቁ ተ _ 372/90

የወ/18 ፖ/ወ/መ/ቁ 1462/90

ቶፊቅ መሀመድ በተከሰሰበት ወንጀል የተጣራው የምርመራ መዝገብ በቁጥር ወ18/ፖ/03/12035/90 በ17/11/90 ዓ.ም በተፃፈ ሸኝ ደብዳቤ አማካኝነት ደርሶን ተመልክተነዋ።

ከምርመራው መዝገብ ለመረዳት እንደቻልነው ተከሳሹ ካልተያዘው ግብረአበሩ ጋር በመሆን ሀምሌ 14 ቀን 1988 ዓ.ም ከቀኑ በግምት 11 ሰዓት ተኩል ሲሆን በወረዳ 18 ቀበሌ 06 ክልል ውስጥ ልዩ ቦታው ሴንጅ ዮሴፍ ት/ቤት አጠገብ ባለአንድ ብርና ባለሁለት ብር ሎተሪ ይዞ መጥቶ ሎተሪ ልግዛ ብሎኝ የራሱን ማውጫ ጊዜ ያለፈበትን ከሎተሪው ጋር የማይገናኝ ማውጫ አውጥቶ 3000 ሶስት ሺህ ብር ደርሶኛል በማለት 50 ብር አታሎ ተቀብሎኛል በማለት የቀረበ ክስ ነው።

ይህንን ክስ ለማስረዳት ከከሳሽ ቃል በስተቀር የቀረበ ምንም ማስረጃ የለም። በመሆኑም ለማስረጃነት ይረዳን ዘንድ ከሳሽ በሰጠው ቃል ተከሳሹ አታሎኝ ሮጦ ሊያመልጥ ሲል በትራፊክ ፖ/ሊስ ተባባሪነት ተይዟል ብሏል። ስለዚህ ይህ በከሳሹ የተጠቀሰው ተከሳሽን አባሮ ያዘ የተባለው የትራፊክ ፖ/ሊስ ስለጉዳዩ የሚያውቀውን የምስክርነት ቃሉን እንዲሰጥ እንዲደረግ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 38(ሐ) መሰረት የምርመራ መዝገቡን በውስጡ 10 ገጽ እንደያዘ መልሰን የላክንላችሁ መሆኑን እንገልፃለን።

"ከሰላምታ ጋር"

7. **በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 41 መሰረት መሪ ትዕዛዝ እንዲሰጥ የሚጠየቅበት ፅሁፍ አፃፃፍ**

እንደተጨማሪ ትዕዛዝ ሁሉ የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 41 ክስ ለማቅረብ አጠራጣሪ ሁኔታ በሚያጋጥምበት ጊዜ ዐ/ህጉ መሪ ትዕዛዝ እንዲሰጠው የሚጠይቅ መሆኑን ከሚገልፅ በቀር ይዘቱ እና ቅርፁ ምን መምሰል እንዳለበት በህጉ ላይ የተቀመጠ ነገር የለም። በሥነ-ሥርዓት ህጉ ላይ ተያይዞ የሚገኘው ሰንጠረዥም ቢሆን ይህንን የሚያሰተናግድ ፎርም የለውም። ሆኖም ግን በልማድ የሚታየውና የዳበረው የመሪ ትዕዛዝ ጥያቄ የሚከተሉትን ነጥቦች ይዞ እናገኘዋለን።

- የመሪ ትዕዛዝ ጥያቄው ወጭ የሆነበት የኘሮቶኮል ቁጥር፣
- የመሪ ትዕዛዝ ጥያቄው ወጭ የሆነበት ቀን፣
- መሪ ትዕዛዝ እንዲሰጥ ጥያቄ የቀረበለት መ/ቤት ስም፣
- መሪ ትዕዛዙን የጠየቀው መ/ቤት የመዝገብ ቁጥር፣
- የወንጀል ምርመራውን ያጣራው ፖሊስ የመዝገብ ቁጥር፣
- ጉዳዩ፡- **በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 41 መሰረት መሪ ትዕዛዝ እንዲሰጠን ስለመጠየቅ፣**
- የመሪ ትዕዛዝ ጥያቄ ያስፈለገበትን ምክንያት በበቂ ሁኔታ የሚተነትን ፅሁፍ፣
- መፈክር **(ከሰላምታ ጋር፣ ፍትህ ለሁሉም... ወዘተ)**፣
- የዐ/ሕግ ስምና ፊርማ፣

<u>ምሳሌ</u>፡-

አቶ ሽመልስ ዓለማየሁ አንድ ማካሮቭ ሽጉጥ ከመሰል 5 ጥይቶች ጋር በመያዝ ገበያ ውስጥ ከነጋዴዎች ጋር ሲነጋገር ተይዟል። ይህ ያልተካደ ሲሆን በሰው ምስክር ተረጋግጧል። የንግግሩ ይዘት አልታወቀም።ድርጊቱ ያለፈቃድ የተፈፀመ ቢሆንም አቶ ሽመልስ ዓለማየሁ መሳሪያውን የያዝኩት ራሴን ለመጠበቅ እንጂ ለንግድ አይደለም በማለት ተከራክሯል። የቀረበው ማስረጃ በየትኛው አግባብ መከሰስ እንዳለበት ያጠራጠረ በመሆኑ እና ጉዳዩስ መቅረብ ያለበት በወ/መ/ህ/ቁጥር 809 መሠረት ከሆነ ሥልጣን ያለው ፍ/ቤት የወረዳ ነው ወይስ ማህበራዊ ፍ/ቤት በሚለው ላይ መሪ ትዕዛዝ ጠይቅበት።

ቁጥር----------

ቀን----------

ለ---------- ዞን ፍትህ መምሪያ

የዐ/ህግ መ/ቁ----------

የፖ/ወ/ም/መ/ቁ----------

ጉዳዩ፡- <u>በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 41 መሰረት መሪ ትዕዛዝ እንዲሰጠን ስለመጠየቅ፣</u>

አቶ ሸመልስ ዓለማየሁ አንድ ማካሮቭ ሽጉጥ ከመሰል አምስት ጥይቶች ጋር በመያዝ ገብያ ውስጥ ከነጋዴዎች ጋር ቆሞ ሲነጋገር በመያዙ ፖሊስ ምርመራውን ሲያካሂድ ሽጉጡን ከመሰል አምስት ጥይቶች ጋር ገብያ ውስጥ ይዞ መገኘቱን ተጠርጣሪው ራሱ ያመነ ከመሆኑ በተጨማሪ በአምስት የዓይን ምስክሮች ተረጋግጧል፤ ይሁን እንጅ ተጠርጣሪው ከነጋዴዎች ጋር ያደርግ የነበረው ንግግር ይዘቱ ምን እንደሆነ ለማወቅ አልተቻለም። ተጠርጣሪውም ቢሆን ሽጉጡን የያዝኩት ራሴን ለመጠበቅ እንጅ ለንግድ አይደለም በማለት ለፖሊስ ቃሉን የሰጠ መሆኑን ከፖሊስ የምርመራ መዝገብ ለመረዳት ችለናል።

ሆኖም ግን በተጠርጣሪው ላይ የወንጀል ክስ አዘጋጅተን ክስ ለመመስረት ሁለት ወሳኝ ጉዳዮች የበላይ አካልን ውሳኔ የሚሹ በመሆናቸው በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 41 መሰረት መሪ ትዕዛዝ ከመሰጠታችን በፊት ተከሳሹን ለመክሰስ አልቻልንም።

እነዚህም አጠራጣሪ ጉዳዮች፡-

1. ተጠርጣሪው ሽጉጡን ከመሰል አምስት ጥይቶች ጋር በመያዝ ገብያ ውስጥ ከነጋዴዎች ጋር ቆሞ ሲነጋገር በፖሊስ የተያዘ ቢሆንም የተጠርጣሪው የዕምነት ቃልም ሆነ የምስክሮች ቃል የሚያስረዳው መሳሪያውን ይዞ መገኘቱን እንጅ ከነጋዴዎች ጋር ያደርግ የነበረው ንግግር ይዘት ምን እንደሆነ አልታወቀም፤ በዚህም መሰረት ተጠርጣሪውን በኢፌዴሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 481(1)(ሀ) መሰረት ፈቃድ ሳይኖረው ወይም ለህግ ተቃራኒ በሆነ መንገድ የጦር መሳሪያና ጥይት ሲሸጥ ተገኝቷል ብለን በጦር መሳሪያ መነገድ ወንጀል እንዳንከሰው የሽጉጡንም ሆነ የጥይቶችን ሽያጭ ሲፈፀም የተመለከተ ሰው ካለመኖሩ በተጨማሪ ከነጋዴዎች ጋር ቁሞ ሲነጋገር የተያዘ ከመሆኑ ውጭ ንግግሩ የሽጉጡንና የጥይቶችን ሽያጭና ግዥ የተመለከተ ይሁን ወይም ሌላ ይዘቱ ምን እንደነበረ ሊያስረዳ የሚችል ሰው ወይም ሌላ ማስረጃ ማግኘት አልተቻለም። በሌላ በኩል ደግሞ ተጠርጣሪውን በኢፌዴሪ የወንጀል ህግ አንቀፅ 809 መሰረት እንዲይዝ ያልተፈቀደለትን የጦር መሳሪያ በመያዝ ህዝብ

በሚገኝበት ሥፍራ ተገኝቷል ብለን የተከለከለ የጦር መሳሪያ በመያዝ የደንብ መተላለፍ ክስ እንዳንከሰው ተጠርጣሪው መሳሪያውን ዝም ብሎ ይዞ የተገኘ ሳይሆን ሽጉጡን ከጥይቶች ጋር በመያዝ የንግግሩ ይዘት ምን እንደሆነ ባይታወቅም ከነጋዴዎች ጋር ሲነጋገር በፖሊስ ተይዟል፤ በዚህም የተነሳ ተጠርጣሪውን በየትኛው የወንጀል ህግ አንቀጽ መክሰስ እንዳለብን ለመወሰን ተቸግረናል።

2. ከላይ በ1ኛ ተራ ቁጥር ሥር ለጠየቅነው ጉዳይ ተጠርጣሪው መከሰስ ያለበት በኢፌዴሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 809 መሰረት የተከለከለ የጦር መሳሪያ ይዞ በመገኘት የደንብ መተላለፍ ክስ ነው የሚል ውሳኔ የሚሰጠን ከሆነ ደግሞ ጉዳዩን ለማየት የሥረ-ነገር የዳኝነት ሥልጣን ያለው የቀበሌ ማኅበራዊ ፍ/ቤት ነው ወይስ የወረዳ ፍ/ቤት የሚለው ጥያቄም ውሳኔ የሚሻ ጉዳይ ነው። ይህንን ልንል የቻልንበት ዋናው ምክንያት የተሸሻለው የአማራ ክልል የቀበሌ ማኅበራዊ ፍ/ቤቶች ማቋቋሚያና ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 151/2000 አንቀጽ 13 ሥር የማኅበራዊ ፍ/ቤቶች በወንጀል የሥረ-ነገር ሥልጣናቸው ለማየት ይችላሉ ተብለው ከተዘረዘሩት የደንብ መተላለፍ ወንጀሎች ውስጥ አብዛኞቹ በኢፌዴሪ የወንጀል ህግ 8ኛ መጽሀፍ ሥር የተካተቱት የደንብ መተላለፍ ወንጀሎች ተዘርዝረው የተቀመጡ ሲሆን ሳይዘረዘሩ ከቀሩት ጥቂት አንቀጾች ውስጥ አንዱ አንቀጽ 809 ነው። ይህንን ሁኔታ ዝም ብለን በግርድፉ ስናየው ሥልጣኑ የማኅበራዊ ፍ/ቤቶች ሳይሆን የወረዳ ፍ/ቤት ይመስላል፤ ነገር ግን የአዋጁን አንቀጽ 13 መግቢያ ስናይ ደግሞ በኢፌዴሪ የወንጀል ህግ 8ኛ መጽሀፍ ሥር የተካተቱትና በአዋጁ አንቀጽ 13 ሥር የተመለከቱት የደንብ መተላለፍ ክሶችን ለማየት ሥልጣን ያለው ማኅበራዊ ፍ/ቤት እንደሆነ ይገልፃል። ከዚህ አባባል ተነስተን «...የወንጀል ህግ 8ኛ መጽሀፍ ሥር የተካተቱትና...» የሚለውን አባባል ስናየው በአዋጅ ቁጥር 151/2000 አንቀጽ13 ሥር ከተዘረዘሩት በተጨማሪ ሌሎች በወንጀል ህጉ 8ኛ መጽሀፍ ሥር ያሉ የደንብ መተላለፍ ክሶችን የሚመለከቱ አንቀጾችም በቀበሌ ማኅበራዊ ፍ/ቤቶች የሥረ-ነገር ሥልጣን ሥር እንዲወድቁ ተደርጎ የተደነገገ ይመስላል፤ በዚህም የተነሳ ጉዳዩን ለማየት የሥረ-ነገር ሥልጣን ያለው አካል የቀበሌ ማኅበራዊ ፍ/ቤት ነው ወይስ የወረዳ ፍ/ቤት የሚለውን ጥያቄ ለመመለስና ለመወሰን ተቸግረናል።

ስለዚህ ከላይ በዝርዝር በገለፅናቸው ሁለት አጠራጣሪ ጉዳዮች ላይ ተገቢ ነው የምትሉትን ውሳኔ ወስናችሁ አስፈላጊውን መረ ትዕዛዝ ትሰጡን ዘንድ እየጠየቅን መረ ትዕዛዙን ለመስጠት እንዲመቻችሁ በማለት 07 ገጽ የፖሊስ የምርመራ መዝገብ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላክንላችሁ መሆናችንን እንገልፃለን::

«ከሰላምታ ጋር»

ከበደ ማሞ

የወረዳው ዐ/ህግ

<u>የመወያያ ጥያቄ</u>

አቶ " ለ " በሰው መግደል ወንጀል ተጠርጥሮ 40 ገጽ የፖሊስ የምርመራ ውጤት ደርሶሃል:: ተጠርጣሪው ወንጀሉ በተፈፀመበት ጊዜ የአእምሮ ህመምተኛ ነበርኩ በማለት ክርክር አቅርቧል:: ይህንንም ለማስረዳት የሐኪም ማስረጃ አቅርቧል:: ይሁን እንጂ ጉዳዩን ስታጠናው

ሀ. ተጠርጣሪው የአእምሮ ህመምተኛ በመሆኑ ክሱ በወ/መ/ሥ/ሥ/ቁጥር 42/1/ሀ/ መሠረት

መዘጋት አለበት ወይም

ለ. ተጠርጣሪው የሐኪም ማስረጃ ቢያቀርብም ወንጀሉ በተፈፀመበት ጊዜ ህመምተኛ የነበረ

መሆኑ ማስረጃው ስለማያስረዳ በግፍ ሰው መግደል ወንጀል መከሰስ አለበት:: የሚሉ

ሁለት አማራጮች ውስጥ ትገባና ለውሣኔ ትቸገራለህ:: በጉዳዩ ላይ የዞን መምሪያው

ዐ/ሕግ መረ ትዕዛዝ እንዲሰጥህ የምርመራ መዝገቡን በመላክ ጥያቄውን አቅርብ::

8. <u>በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 42 መሰረት ክስ የማይቀርብ መሆኑን የሚገልፅ ውሳኔ አፃፃፍ</u>

ዐ/ሕግ የፖ/ሊስ የምርመራ መዝገብ እንደደረሰው የምርመራ መዝገቡ ክስ ለመመስረት የሚያስችል ነገር የሌለው መሆኑን ሲረዳው የክስ አልመሰርትም ውሳኔ ይሰጣል፡፡ ዐ/ህጉ የአያስከስስም ውሳኔ ሊሰጥ የሚችለው፡-

- ተከሳሹን ለማስቀጣት በቂ የሆነ ማስረጃ የሌለ ከሆነ
- ተከሳሹን ለማግኘት የማይቻልና ተከሳሹም በሌለበት ክሱ ሊሰማ የማይቻል ከሆነ፤ ተከሳሹ በሌለበት ክስ ተሰምቶ ውሳኔ የሚሰጥባቸው ጉዳዮች፡-
  - ከአስራ ሁለት ዓመት በማያንስ ፅኑ እስራት የሚያሳስር ወንጀል የሰራ (**የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ** 161(2)(ሀ))
  - በመንግስት የኢኮኖሚና የገንዘብ ጥቅሞች ላይ የተደነገጉ ልዩ ህጎችን የመጣስ ወንወጀሎችን የፈፀመ (**የኢፌዴሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ** 343)
  - በወርቅ፣ በጥሬ ገንዘብ እና በውጭ አገር ገንዘብ በህገ-ወጥ መንገድ የነገደ (**የኢፌዴሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ** 346)
  - በከበሩ ማዕድናት ህገ-ወጥ በሆነ መንገድ መነገድ (**የኢፌዴሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ** 347)
  - በመንግስት ገንዘብ አስተማማኝነት ላይ የሚደረግ የገንዘብ ድርጊት (**የኢፌዴሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ** 348)
  - ህገ-ወጥ በሆነ መንገድ የመንግስትን ቀረጥ ወይም ግብር የመክፈል እምቢተኛነት (**የኢፌዴሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ** 349)
  - ግብር እንዳይከፈል ማነሳሳት (**የኢፌዴሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ** 350)
  - በመንግስት ገቢ ምንጮች ላይ ጉዳት ማድረስ (**የኢፌዴሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ** 351)
  - ኬላ መስበር (**የኢፌዴሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ** 352)
  - በአገር ኢኮኖሚና በመንግስት ግብር ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች (**የኢፌዴሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ** 353)
  - የተከሰሰው ሰው የውጭ አገር ጥገኛ በመሆኑና ጥገኛ ያደረገው አገር አሳልፎ ያልሰጠው እንደሆን (**የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ** 161(3))
  - በደንብ መተላለፍ ወንጀል (**የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ** 168 **እና** 170(4))

- ክሱን ለማቅረብ በይርጋ የታገደ ከሆነ (**የኢፌዴሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ ከ216-222**)
- ለተፈፀመው ወንጀል ምህረት ወይም ይቅርታ ተሰጥቶ ከሆነ (**የኢፌዴሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ ከ229-230**)

ይህ የክስ አይመሰረትም ውሳኔ በህጉ መሠረት ውሳኔ ነው፡፡ በዚህም መሰረት የክስ አይመሰረትም ውሳኔ በሥነ-ሥርዓት ህጉ ሶስተኛ ሰንጠረዥ ላይ በሰፈረው ዓይነት መዘጋጀት ያለበት ሆኖ በይዘቱም፣

- ደብዳቤው ወጭ የሆነበትን የፕሮቶኮል ቁጥርና ቀን
- ምርመራውን ያጣራው ፖሊስ ጽ/ቤት ስምና አድራሻ /ውሳኔውን በአድራሻ እንዲያውቀው የሚፈለገውን ፖሊስ ጽ/ቤት ስምና አድራሻ
- ውሳኔውን የሰጠው ዐ/ህግ መ/ቤት የመዝገብ ቁጥር
- የወንጀል ምርመራውን ያጣራው ፖሊስ ጽ/ቤት የመዝገብ ቁጥር
- ጉዳዩ፡- **በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 42(1)(ሀ) መሰረት ክስ የማይቀርብ መሆኑን ስለመግለፅ፣**
- የክሱን ፍሬ ነገር በአጭሩ
- ተጠርጣሪው የሰጠው የዕምነት ክህደት ቃል
- የቀረበው ማስረጃ ዝርዝር ይዘት
- የተሰጠው ህጋዊ አስተያየትና ውሳኔ
- ውሳኔውን የሰጠው ዐ/ህግ ሥምና ፊርማ
- ግልባጭ
  - ለሚመለከተው ዞን ፍትህ መምሪያ
  - ለተበዳዮች
  - ለተከሳሾች

<u>ምሳሌ</u>፡-

አቶ ከበደ ዓለማየሁ እና አቶ ውዱ ዘላለም ከደሴ ወደ አዲስ አበባ በአውቶቡስ ጥር 3 ቀን 2000 ዓ.ም እየተጓዙ እያለ ደብረሲና ላይ በተደረገ ፍትሻ ከተቀመጡበት ወንበር ሥር ንብረትነቱ የቤተክርስቲያን የሆነ ጽላትና ጥንታዊ የሐይማኖት መጽሐፍ ይገኛል፡፡ ንብረቱ ሲገኝ በጣም ከመደነገጣቸው የተነሳ መናገር አቅቷቸዋል፡፡ አዲስ አበባ ከሚገኝ ነጋዴ ጋር በሞባይል ስልክ በተደጋጋሚ ይገኛኙ እንደበር በተሳፋሪ ተመስክሯል፡፡ ደብረሲና ላይ ለምሳ መኪናው እንዳይቆም አዲስ አበባ የፍ/ቤት ቀጠሮ ያላቸው መሆኑን በመግለጽ ሲቃወሙም ነበር፡፡ ሁለቱም ግለሰቦች የተቀመጡበት ወንበር ሶስት ሰው

የሚይዝ ቢሆንም ሶስተኛ ሰው እንዳይቀመጥበት ለማድረግ ሶስተኛ ትኬት በመቁረጥ ሁለቱ ሰዎች ብቻ የተጓዙበት መሆኑን የአውቶቡሱ ትኬት ቆራጭ መስክሯል፡፡

- ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን ፍሬ ነገሮች ተመልክታችሁ እንዲሁም የማስረጃውን ክብደት በመመዘን የክስ አይመሰረትም ውሣኔ ስጡ፡፡

ቁጥር----------

ቀን----------

ለጣርማ በር ወረዳ ፖሊስ ጽ/ቤት

<u>ደብረ ሲና</u>

የዐ/ህግ መዝገብ ቁጥር------

የፖ/ወ/ም/ መዝገብ ቁጥር----

ጉዳዩ፡- <u>በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 42(1)(ሀ) መሰረት ክስ የማይቀርብ መሆኑን ስለመግለፅ፣</u>

አቶ ከበደ ዓለማየሁ እና አቶ ውዱ ዘላለም በተጠረጠሩበት የከባድ ስርቆት ወንጀል የጣርማ በር ወረዳ ፖሊስ ጽ/ቤት ጉዳዩን ያጣራበትን የምርመራ መዝገብ በቁጥር ወም 251/1237/1862 በቀን 03/06/2000 ዓ.ም ለተፃፈ የመሸኛ ደብዳቤ ጋር ልኮልን ደርሶን መርምረነዋል፡፡

<u>የክሱ ፍሬ ነገር በአጭሩ</u>

ተጠርጣሪዎች ጥር 3 ቀን 2000 ዓ.ም ከደሴ ወደ አዲስ አበባ በመሄድ ላይ በነበረ የሰሌዳ ቁጥሩ አ.አ 005327 የሆነ ካቻማሊ አውቶቡስ ተሳፍረው በመንዝ ላይ እያሉ ደብረ ሲና ከተማ ላይ በተደረገ ፍተሻ ከተቀመጡበት ወንበር ሥር ንብረትነቱ የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የሆነ አንድ ጽላትና አንድ ጥንታዊ የኃይማኖት መጽሀፍ በመገኘቱ በተገኘው ንብረት ላይ የስርቆት ወንጀል ፈፅመዋል በሚል ነው፡፡

<u>የተጠርጣሪዎች ቃል</u>

ተጠርጣሪዎች በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 27(2) መሰረት ጣርማ በር ወረዳ ፖሊስ ጽ/ቤት ወንጀል ምርመራ ክፍል ቀርበው በሰጡት የዕምነት ክህደት ቃል የተጠረጠርንበትን የሰርቆት ወንጀል አልፈፀምንም፤ ጥፋተኞችም አይደለንም ብለዋል።

<u>የቀረበው ማስረጃ</u>

በተጠርጣሪዎች ላይ የቀረበውን ክስ ያስረዳሉ ተብለው የቀረቡት የሰው ምስክሮች፦

1. አቶ ማተቤ ዓለሙ
2. ወ/ሮ ዘውድነሽ ይልማ
3. ወ/ሮ ሀመልማል ገብሩ
4. አቶ አብነት ዘሪሁን
5. አቶ መንበሩ አየለ
6. አቶ ይስማው ከበደ ናቸው።

1ኛ፣ 2ኛ እና 3ኛ ምስክሮች ሲያስረዱ ከላይ በተጠቀሰው አውቶቡስ ውስጥ ተሳፍረን ተጠርጣሪዎች ከተቀመጡበት ወንበር ቀጥሎ ካለው ሶስት ሰው ከሚይዘው ወንበር ላይ ተቀምጠን ስንጓዝ ተጠርጣሪዎች አዲስ አበባ ከሚገኝ ስሙንና ማንነቱን ከማናውቀው ሰው ጋር ተራ በተራ የሞባይል ስልክ እየተቀባበሉ በተደጋጋሚ ይነጋገሩ የነበረ መሆኑን ሰምተናል፤ በተጨማሪም ለፍተሻ ደብረ ሲና ከተማ ከወረድን በኋላ ፈታሽ ፖሊሶች ከወንበር ሥር ፅላትና መጽሀፍ አገኘን ብለው ይዘው ሲመጡ ከተጠርጣሪዎች ፊት ላይ ከፍተኛ ድንጋጤ የተመለከትን ከመሆኑ በተጨማሪ ከመደንገጣቸው የተነሳ መናገር አቅታቸው ነበር በማለት መስክረዋል።

4ኛ እና 5ኛ ምስክሮች ሲያስረዱ ደግሞ መኪናው ደብረ ሲና ከተማ ላይ ለምሳ እንዲቆምልን ሾፌሩን ስንጠይቀው ሁለቱ ግለሰቦች አዲስ አበባ የፍ/ቤት ቀጠሮ ያላቸው መሆኑን በመግለፅ መኪናው መቆም የሌለበት መሆኑን ሲቃወሙ ነበር በማለት መስክረዋል።

6ኛው ምስክር ደግሞ እኔ የመኪናው ትኬት ቆራጭ ነኝ፤ ተሳፋሪዎች መኪናው ውስጥ ከገቡ በኋላ ትኬት ለመቁረጥ በየወንበሮች እየተዘዋወርኩ ተጠርጣሪዎች ከተቀመጡበት ወንበር ላይ ስደርስ 2ኛው ተከሳሽ የሶስት ሰው የትኬት ዋጋ ከፈለኝ። እኔም እናንተ ዕኮ ሁለት ናችሁ፤ አንተ ግን የሰጠኸኝ የሶስት ሰው የትኬት ዋጋ ነው ስለው አይ ሆን ብየ

ነው፤ የምንጓዘው ረጅም መንገድ ስለሆነና ከፍተኛ የሆነ ሙቀትም ስላለ ለወንበሩ የሶስት ሰው የትኬት ዋጋ ከፍለን ሁለታችን ብቻ ተዝናንተን መጓዝ እንዳለብን ከጓደኛዬ ጋር ተስማምተን ያደረግነው ነው በማለት ምላሽ ሰጥቶኛል፤ በመንገድም ሁለት ሶስት ቦታ ላይ መኪናው እየቆመ አዳዲስ ተሳፋሪዎችን ስንጭን ተሳፋሪዎቹ የአንድ ሰው ቦታ ያለ መሆኑን በማየት ለመቀመጥ ወደ ተጠርጣሪዎቹ ወንበር ሲሄዱ የተያዘ ወንበር መሆኑን በመግለፅ ሲመልሷቸው አይቻለሁ ብሎ መስክሯል።

ከሰው ምስክሮች በተጨማሪ በፍተሻው ወቅት የተገኙት አንድ ጽላትና አንድ ጥንታዊ የኃይማኖት መጽሀፍ በኤግዚቢት ማስረጃነት የቀረቡ መሆኑን ከፖሊስ ከተላከልን የምርመራ መዝገብ ለመረዳት ችለናል።

<u>ህጋዊ አስተያየትና ውሳኔ</u>

ተጠርጣሪዎች ከሌሎች ተሳፋሪዎች ጋር በመሆን በአውቶቡስ ተሳፍረው ከደሴ ወደ አዲስ አበባ በመንገዝ ላይ ሳሉ ደብረ ሲና ከተማ ላይ በተደረገ ፍተሻ ከተቀመጡበት ወንበር ሥር አንድ ጽላትና አንድ ጥንታዊ የኃይማኖት መጽሀፍ የተገኘ በመሆኑ በሰርቆት ወንጀል ተጠርጥረው የጣርማ በር ወረዳ ፖሊስ ጽ/ቤት ወንጀል ምርመራ ክፍል ምርመራውን ሲያካሂድ ተጠርጣሪዎችን የዕምነት ክህደት ቃላቸውን በጠየቃቸው መሰረት ወንጀሉን አለመፈፀማቸውንና ጥፋተኛም አለመሆናቸውን በመግለፅ ቃላቸውን ሰጥተዋል።

ፖሊስም ጉዳዩን ያስረዳሉ ያላቸውን ሰዎች የምስክርነት ቃል ሲቀበል ተጠርጣሪዎች ንብረቱ ከተቀመጡበት ወንበር ሥር ሲገኝ በጣም ከመደንገጣቸው የተነሳ መናገር አቅታቸው እንደነበር፣ አዲስ አበባ ከሚገኝ ሰው ጋር በሞባይል ስልክ በተደጋጋሚ ይገናኙ እንደነበር፣ የፍ/ቤት ቀጠሮ እንዳላቸው በመግለፅ አውቶቡሱ ለምሳ ደብረ ሲና ላይ እንዳይቆም ሲቃወሙ እንደነበርና ሁለቱም ግለሰቦች የተቀመጡበት ወንበር ሶስት ሰው የሚይዝ ቢሆንም ሶስተኛ ሰው አብሯቸው እንዳይቀመጥ ያደረጉ መሆናቸውን ምስክሮች አስረድተዋል።

እኔም የቀረበውን የፖሊስ የምርመራ መዝገብ መሰረት በማድረግ ተጠርጣሪዎች ፈፀሙት የተባለው ድርጊት በወንጀል ህግ የሚያስጠይቅ ነው ወይስ አይደለም? ነው ከተባለ ተጠርጣሪዎችን በሰርቆት ወንጀል ተጠያቂ ለማድረግ የቀረበው ማስረጃ ብቃት

አለው ወይ? የሚሉ ጥያቄዎችን በማንሳት ጉዳዩን አግባብ ካለው የህግ ድንጋጌ ጋር በማዛመድ ስመረምረው ተፈፀመ የተባለው ወንጀል ህጋዊ፣ ግዙፋዊና ሞራላዊ ፍሬ-ነገሮችን አሟልቶ የያዘ ነው፤ ይህ ደግሞ በኢፌዴሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 23(2) መሰረት አንድ ወንጀል ወንጀል ለመባል ወንጀሉን የሚያቋቁሙት ህጋዊ፣ ግዙፋዊና ሞራላዊ ፍሬ-ነገሮችን በአንድነት አሟልቶ ሲገኝ ስለሆነ ተጠርጣሪዎች ፈፀሙት የተባለው ድርጊት በወንጀል ህግ የሚያስጠይቅ ነው::

ድርጊቱ በወንጀል ህግ የሚያስጠይቅ በመሆኑ የተነሳ ተጠርጠሪዎችን በስርቆት ወንጀል ተጠያቂ ለማድረግ የቀረበው ማስረጃ ብቃት አለው ወይ የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ያመች ዘንድ የሰው ምስክሮች ጣርማ በር ወረዳ ፖሊስ ጽ/ቤት ወንጀል ምርመራ ክፍል ቀርበው የሰጡትን የምስክርነት ቃል ስመረምረው 1ኛ፣ 2ኛ እና 3ኛ ምስክሮች የሰጡት ቃል ተጠርጣሪዎች በሞባይል ስልክ ሌላ ቦታ ከሚገኝ ሰው ጋር ይነጋገሩ ነበር የሚል ነው:: እኔም በህዝብ ማመላለሻ አውቶቡስ ውስጥ ሰዎች ተሳፍረው በሚጓዙበት ጊዜ በሞባይል ስልክ ሌላ ቦታ ከሚገኙ ሰዎች ጋር ግንኙነት ማድረግ አንድ ሰው ስርቆት ፈፅሟል ለማለት በቂ ማስረጃ ይሆናል ወይ ብየ ሳጠናው በተለመደው አኳኋን በመኪና እየተጓዙ ከሌላ ሰው ጋር በሞባይል ስልክ ንግግር ማድረግ አንድ ሰው ወንጀል ፈፅሟል ለማለት ምንም ዓይነት ማስረጃ ሊሆን አይችልም፤ ማስረጃ እንዲሆን ከተፈለገ ተጠርጣሪዎች በሞባይል ስልክ ያደርጉት የነበረው ንግግር በወንበሩ ሥር ከተገኘው ጽላትና መጽሀፍ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው መሆን አለበት:: ይህ ደግሞ ንግግሩን ሰምተናል ባሉት ምስክሮች አልተረጋገጠም፤ በተጨማሪም ከተጠርጣሪዎች ፊት ላይ ከፍተኛ ድንጋጤ ታይቷል፤ መናገርም አቅቷቸው ነበር የሚለውን የምስክርነት ቃል ስመረምረው ማንም ሰው ተቀምጦበት ከነበረው ወንበር ሥር ዕቃ ተደብቆ ተገኝብህ ቢባል አንተ ነህ የደበቅኸው ልባል እችላለሁ ከሚል ጥርጣሬ ተነስቶ የመደንገጥና የመርበትበት ባህሪይ ሊታይበት የሚችል መሆኑን ከተለምዷዊ ሁኔታ የምንረዳው ነገር ነው እንጅ አንድ ሰው ከተቀመጠበት ወንበር ሥር ዕቃ ተደብቆ በመገኘቱ ሲደናገጥና መናገር ሲያቅተው ቢታይ ተደብቆ የተገኘውን ዕቃ ሰርቋል ለማለት በቂ ማስረጃ ይሆናል የሚል ዕምነት የለኝም::

4ኛ እና 5ኛ ምስክሮች የሰጡት የምስክርነት ቃል ተጠርጣሪዎች አዲስ አበባ የፍ/ቤት ቀጠሮ እንዳለባቸው በመግለፅ አውቶቡሱ ለምሳ ደብረ ሲና ከተማ እንዳይቆም ሲቃወሙ እንደነበር የሚገልፅ ነው:: ይህንን የምስክርነት ቃል ሳጠናው ብዙ ጊዜ ሰዎች መድረስ

የሚፈልጉበት ቀጠሮ ሲኖራቸው በቀጠሮው ቦታ በሰዓቱ ለመድረስ በማሰብ የተሳፈሩበት መኪና የትም ቦታ እንዳይቆም ሹፌሩን ሲወተውቱና ተሳፋሪዎችንም ሲቃወሙ ይታያሉ። እነዚህ ተጠርጣሪዎችም የፍ/ቤት ቀጠሮ እንዳላቸው በመግለፅ የመኪናውን መቆም መቃወማቸው ወንጀሉን ፈፅመዋል ለማለት በቂ ምክንያት ነው የሚል እምነት የለኝም፤ እንዲውም ፖሊስ ጉዳዩን ለማጣራት ባደረገው ጥረት ተጠርጣሪዎች ቀጠሮ አለን ካሉት ፍ/ቤት ድረስ በመሄድ ባረጋገጠው መሰረት ተጠርጣሪዎች በዕለቱ የፍ/ቤት ቀጠሮ የነበራቸው መሆኑን እንዳረጋገጠ ከፖሊስ ከተላከልን የምርመራ መዝገብ ተረድቻለሁ።

ሶስት ሰው በሚይዘው ወንበር ላይ የሶስት ሰው የጉዞ ዋጋ በመክፈል ሁለቱ ሰዎች ብቻ የተጓዙበት መሆኑን የአውቶቡሱ ትኬት ቆራጭ የሆኑት 6ኛው ምስክር የምስክርነት ቃላቸውን ሰጥተዋል። ምንም እንኳ ድርጊቱ ከተለመደው ሁኔታ ወጣ ያለ ቢሆንም ተጠርጣሪዎች ፈፅመውታል ከተባለው ወንጀል ጋር ግን ምንም ዓይነት ግንኙነት የሌለው በመሆኑ ለዚህ ጉዳይ ማስረጃ ይሆናል የሚል ዕምነት የለኝም።

በፍተሻው ወቅት የተገኙት አንድ ጽላትና አንድ ጥንታዊ የኃይማኖት መጽሀፍ በኤግዚቢትነት የተያዙ ቢሆንም እነዚህ ንብረቶች በተጠርጣሪዎች የተሰረቁ ለመሆናቸው የሚጠቁም አንዳችም ማስረጃ የለም፤ ምክንያቱም ንብረቶቹ ተጠርጣሪዎች ተቀምጠውበት በነበረው ወንበር ሥር ተገኙ እንጅ በተጠርጣሪዎች እጅ ወይም የነሱ የግል ንብረት በሆነ ዕቃ ውስጥ አልተገኙም፤ ስለዚህ ንብረቶቹ ተጠርጣሪዎቹ ተቀምጠውበት በነበረው ወንበር ሥር መገኘታቸው ብቻውን በቂ ማስረጃ ሆኖ ተከሳሾችን ተጠያቂ ያደርጋል የሚል ዕምነት የለኝም።

በተጨማሪም የወንጀል ህጉ አንቀጽ 665(1) እንደሚደነግገው አንድ ሰው የስርቆት ወንጀል ፈፅሟል ለመባል ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው የማይገባ ብልፅግና ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ የሌላ ሰው የሆነውን ተንቀሳቃሽ ንብረት አንስቶ መውሰድ ወይም በቀጥታ የራሱ ንብረት ማድረግ ወይም በተዘዋዋሪ ከራሱ ንብረት ጋር እንዲቀላቀል ማድረግ አለበት ይላል፤ ነገር ግን ከላይ በዝርዝር ያየናቸው ማስረጃዎች በሙሉ ተጠርጣሪዎች ንብረቶችን የራሳቸው ወይም የሌላ ሰው ለማድረግ በማሰብ ንብረቶችን አንስተው መውሰዳቸውን ወይም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከራሳቸው ንብረት ጋር የቀላቀሏቸው ስለመሆኑ የሚያስረዱ ሆነው አላገኘኋቸውም።

ስለዚህ ከላይ በተዘረዘሩት ምክንያቶች የተነሳ በተጠርጣሪዎች ላይ ለቀረበው የስርቆት ወንጀል የቀረበውን ማስረጃና የወንጀል ህግ ድንጋጌ መሰረት በማድረግ ክስ ለመመስረት የማያስችል ሆኖ ስላገኘሁት በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 42(1)(ሀ) መሰረት የክስ አላቀርብም ውሳኔ የሰጠሁ መሆኔን እየገለፅኩ ከዚህ በፊት የላካችሁልንን 20 ገጽ የፖሊስ የምርመራ መዝገብ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዤ የላክሁላችሁ ሲሆን የሰሜን ሸዋ ዞን ፍትህ መምሪያና ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው ወገኖች በግልባጭ እንዲያውቁት ያደረግሁ መሆኔን እገልፃለሁ::

«ከሰላምታ ጋር»

ከበደ ወዳጆ

የወረዳው ዐ/ህግ

<u>ግልባጭ</u>

- *ለሰሜን ሸዋ ዞን ፍትህ መምሪያ*

  <u>ደብረ ብርሃን</u>
- *ለአቶ ከበደ ዓለማየሁ*
- *ለአቶ ውዱ ዘላለም*

  <u>ባሉበት</u>

<u>የመወያያ ጥያቄ</u>

1. **ቀጥሎ ያለውን የክስ ፍሬ ነገር፣ የተከሳሾች ቃል እና ማስረጃ መሰረት አድርጋችሁ የክስ አያስመሰርትም ውሳኔ ጻፉ::**

<u>ተከሳሾች፣</u>

1ኛ ተከሳሽ.....ከማል ሰዒድ

2ኛ ተከሳሽ.....አስማረ ዮሀንስ

<u>የክሱ ፍሬ ነገር ፣</u>

1ኛው ተከሣሽ የ.....ወረዳ ገጠር ልማት ጽ/ቤት ኃላፊ 2ኛው ተከሣሽ ደግሞ የዚሁ ወረዳ አቅም ግንባታ ጽ/ቤት ኃላፊ ሆነው ሲሠሩ መጋቢት 05 ቀን 2002 ዓ/ም በገጠር ልማት ጽ/ቤት ንብረት ክፍል የተቀመጠ 100 ኩንታል ሲሚንቶ በ1ኛው ተከሣሽ ፈቃጅነት 2ኛው ተከሣሽ ተረክቦ በትውስት የወሰደ ስለሆነ ሥልጣናቸውን በማይገባ ቦታ ተጠቅመዋል የሚል ነው::

<u>የተከሣሾች ቃል ፣</u>

ሁለቱም ተከሣሾች ለመርማሪ ፖ/ሊስ የሰጡት የተከሣሽነት ቃል ፍሬ ሃሳብ በወረዳው ውስጥ የሚሠራው የ.....1ኛ ደረጃ ት/ቤት ግንባታ በስሚንቶ እጥረት ምክንያት ሊቆም ስለሆነ ከግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት በንብረት ክፍል የተቀመጠውን 100 ኩንታል ሲሚንቶ በትውስት እንዲወጣ አድርገን ሥራውን ካስቀጠልን በኋላ በዚሁ የበጀት ዓመት ተመልሶ እንዲተካ አድርገናል የሚል ነው፡፡

<u>ማ ስ ረ ጃ</u>

ክሱን በማስረጃ ለማረጋገጥ ወ/ሮ ዓለሚቱ ይርሳው የተባሉ የወረዳው ገጠር ልማት ጽ/ቤት ዕቃ ግምጃ ቤት ሠራተኛ ቀርበው ቃላቸውን ሰጥተዋል፡፡ የሰጡት ቃል ፍሬ ሃሳብም የምሠራበት መ/ቤት በ2003 የበጀት ዓመት ለሰብል ልማት ዴስክ ከገዛውና ከንብረት ክፍል ከነበረው ስሜንቶ ውስጥ 100 ኩንታል እያንዳንዱ 398 ብር የሚያዋጣ በጠቅላላው የብር 39800 ግምት ያለው ስሚንቶ 2ኛው ተከሣሽ የትውስት ፎርም ሞልቶ በማቅረብ 1ኛው ተከሣሽም ፈቅዶለት ወስዷል፡፡ ስሚንቶውን የወሰደው ለት/ቤት ማሠሪያ ብሎ ሲሆን ለየትኛው ት/ቤት እንደሆነ ግን አላውቅም የሚል ነው፡፡

በጹሑፍ ማስረጃ ረገድም መጋቢት 05 ቀን 2002 ዓ/ም የተፃፈ የ.....ወረዳ ግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት የትውስት ዕቃ ወጭ ማድረጊያ ቅጽ የቀረበ ሲሆን 2ኛው ተከሣሽ 100 ኩንታል ሲሚንቶ በትውስት መወሰዱንና ነሀሴ 30 ቀን 2002 ዓ/ም ለመመለስ ግዴታ መግባቱን ያስረዳል፡፡

መስከረም 09 ቀን 2003 ዓ/ም ከወረዳው ግብርና ገጠር ልማት ጽ/ቤት በመ/ቤቱ አስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት ኃላፊ ተፈርሞ የወጣው 1 ገጽ ደብዳቤ ደግሞ 2ኛው ተከሣሽ በትውስት ወስዶት የነበረው 100 ኩንታል ስሚንቶ ነሀሴ 30 ቀን 2002 ዓ.ም ተመልሶ ገቢ መሆኑን የሚያስረዳ ነው፡፡

በ3ኛ ደረጃ ከ.....ወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት መስከረም 11 ቀን 2003 ዓ.ም ለወረዳው ፖ/ሊስ ጽ/ቤት የተፃፈ 1 ገጽ ደብዳቤ ቀርቧል፡፡ ፍሬ ሐሳቡም መጋቢት 05 ቀን 2002 ዓ/ም በ2ኛ ተከሣሽ ፊርማ ከገጠር ልማት ዋና ጽ/ቤት በትውስት ተወስዶ የነበረው 100 ኩንታል ስሚንቶ ሥራን ለማፋጠን በሚል በትውስት

ከተወሰደ በኋላ ሙሉ በሙሉ ለ.....1ኛ ደረጃ ት/ቤት መስሪያ ውሏል የሚል ነው፡፡

2. ቀጥሎ የተሰጠውን የክስ አያስመሰርትም ውሳኔ አንብቡና እንደገና አስተካክላችሁ ጻፉ፡፡

ቁጥር

አ/80/ፍ/ት 2502/1957/96

ቀን 02/09/96

ለአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ፖሊስ መምሪያ

አዲስ አበባ

የወ/ሕ/መ/ቁ/ 1957/96

የፖ/ም/መ/ቁ/ 2078/96

ተከሳሽ ብርሃኑ ባየህ አበበ በተከሰሰበት ጉዳይ የተጣራው የምርመራ መዝገብ በቁጥር ወመ30/1861/16628 በሚያዝያ 20 ቀን 1996 ዓ.ም በተፃፈ መሸኛ አማካኝነት ደርሶን መርምረነዋል፡፡

የክሱ ፍሬ ነገር ባጭሩ

ተከሳሹ በሚያዝያ 13 ቀን 1996 ዓ.ም ለሚያዝያ 14 አጥቢያ በአ/ቃ/ክ/ከ/ቀ/ 10 ገብርኤል ፀበል በተባለው ልዩ ቦታ የከሳሽ ብሩክ ሰፈሬ ንብረት የሆነ 5 ቆርቆሮ ወስዷል የሚል ነው፡፡

የተከሳሽ ቃል

ተከሳሹ ለቀረበው የስርቆት ወንጀል ድርጊቱን አልፈፀምኩም በማለት ቃል ሰጥቷል፡፡

የቀረበው ማስረጃ ይዘት

1ኛ/ ወ/ር ጌቱ ቶላ፣ 2ኛ/ ወ/ር ኤፍሬም ገዛኸኝ መኩሪያ፣ 3ኛ/ ፍቃዱ በየነ ነገዎ፣ 4ኛ/አስራት ታደሰ ወ/ሩፋኤል ሲሆኑ፣ 1ኛ እና 2ኛ ምስክሮች ተከሳሹ ከሌሊቱ 10፡00 ሰዓት ቆርቆሮ ይዞ ሲሄድ አይተነው የማን ነው ስንለው ሶስት ቆርቆሮ በ90 ብር ገዝቼ የራሴ ነው አለን ስንቆጥረው ግን አምስት ቆርቆሮ ነው ሲሉ 3ኛ እና 4ኛ ምስክሮች በተከሳሹ እጅ የተገኘው ቆርቆሮ የከሳሽ መሆኑን እናውቃለን በማለት መስክረዋል፡፡

<u>ህጋዊ አስተያየትና ውሳኔ</u>

የቀረበው አራት የሰው ማስረጃ ሲሆን ተከሳሹ ስርቆት ሲፈፅም አየሁ ያለ ምስክር የለም 3ኛ እና 4ኛ ምስክሮች ንብረቱ የከሳሽ መሆኑን እናውቃለን ቢሉም በተከሳሽ እጅ በምን ዓይነት ሁኔታ እንደገባ ወይም በወንጀል በመፈፀም ምክንያት የገባ መሆኑን አላስረዱም፡፡ ስለሆነም በተከሳሽ ላይ ክስ ለማቅረብ አልተቻለም፡፡

ስለዚህ የምርመራ መዝገቡን በውስጡ 12 ገጽ እንደያዘ ተመላሽ ያደረግን ሲሆን፣ ከፍ ብለን ለመግለፅ እንደሞከርነው በተከሳሽ ላይ ለቀረበው የስርቆት ወንጀል የቀረበው ማስረጃ እንደ ክሱ አስረድቶ ባለመገኘቱ ክስ ለማቅረብ ባለመቻሉ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 42(1)(ሀ) መሰረት የክስ አናቀርብም ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

“ከሰላምታ ጋር”

የአቃቂ

ምድብ የፍትህ ሚኒስቴር

ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊ

ግልባጭ፣

ለአዲስ አበባ አስ/የፍ/ሚ/ር ተ/ጽ/ቤት

<u>አዲስ አበባ</u>

9. <u>የየዕለት የችሎት ውሎ አፃፃፍ</u>

ፍ/ቤቶች የየዕለት ሥራቸውን ሲያከነውኑ ሁሌም በእያንዳንዱ መዝገብ ላይ አዘውትረውና በተደጋጋሚ የሚያከናውኑት የተለመደና ተቀባይነት ያገኘ የችሎት ውሎ አፃፃፍ የሚይዛቸው ነገሮች፡-

- የመዝገቡ ገፅ፣
- የመዝገቡ ቁጥር (የፍ/ብሄር ወይም የወንጀል)፣
- የችሎቱ ቀን፣
- ያስቻለው/ሉት ዳኛ/ኞች ስም፣
    - የችሎቱ ሰብሳቢ ዳኛ መጀመሪያ
    - የቀኝ ዳኛ በሁለተኛነት
    - የግራ ዳኛ በሶስተኛነት ይመዘገባሉ፡፡
- የከሳሹ ስም (ቀረበ/ቡ ወይም አልቀረበም/ቡም)፣
- የተከሳሹ ስም (ቀረበ/ቡ ወይም አልቀረበም/ቡም)፣
- ስለመዝገቡ አጠቃላይ ሁኔታ፣
    - መዝገቡ አዲስ ከሆነ መዝገቡ ተከፍቶ ለችሎት ሊቀርብ የቻለበትን ምክንያት
    - መዝገቡ የቀጠሮ መዝገብ ከሆነ ተቀጥሮ ያደረበት ምክንያት ምን እንደሆነ በመፃፍ ይጀመራል፡፡
    - በመቀጠልም ባለፈው መዝገቡ ሲቀጠር ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ መፈፀም አለመፈፀሙ ይመዘገባል፡፡
    - ካልተፈፀመ ተለዋጭ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡
    - ከተፈፀመ ወደ ቀጣዩ ሥራ ይሄዳል፡፡

        <u>ለምሳሌ</u>፡-

        ⇒ ምስክር መስማት

        ⇒ ለተጨማሪ ምርመራ ቀጠሮ መስጠት

- ትዕዛዝ

9.1. <u>በየዕለት የችሎት ውሎ አፃፃፍ ላይ የሚታዩ ችግሮች</u>

- የመዝገቡን ገፅ አለመግፍ
- የመዝገቡን ቁጥር ዐለመግፍ
- የችሎቱን ቀን አለመግፍ
- ከሳሽ ተከሳሽ ስለመቅረብ አለመቅረባቸው አለመመዝገብ (በተለይ በመጀመሪያው የቀጠሮ ቀን
- የዳኞች የእጅ ፅሁፍ አለመነበብ
- የሚሰፍረው ፅሁፍ ምን ለማለት እንደተፈለገ ግልፅ አለመሆን

10.<u>ምስክር የመስማት ሂደት አጻጻፍ</u>

በሥነ-ሥርዓት ህጎች ላይ በግልፅ እንደተቀመጠው ምስክር በሚሰማበት ጊዜ በመጀመሪያ መጠየቅ ያለበት ዋና ጥያቄ ሲሆን ይህ ዋና ጥያቄ የሚጠየቀው ምስክሩን በጠራው ተከራካሪ ወገን ነው፡፡ ከዋና ጥያቄ ቀጥሎ የሚጠየቀው ጥያቄ ደግሞ መስቀለኛ ጥያቄ ነው፡፡ መስቀለኛ ጥያቄ የሚጠየቀው እየተመሰከረበት ባለው ተከራካሪ ወገን ሲሆን ይህ ሰው ጥያቄውን የሚጠይቀው በዋና ጥያቄ የተመሰከረበትን ጉዳይ ውድቅ ወይም ፈራሽ ለማድረግ ነው፡፡ ከመስቀለኛ ጥያቄ ቀጥሎ የሚጠየቀው ጥያቄ ደግሞ ድጋሚ ጥያቄ ነው፡፡ ድጋሚ ጥያቄ የሚጠየቀው ምስክሩን በጠራው ወይም እያስመሰከረ ባለው ተከራካሪ ወገን ሲሆን ይህ ተከራካሪ ወገን ድጋሚ ጥያቄውን የሚጠይቀው በዋና ጥያቄ አስመስክሮት የነበረው ጉዳይ በመስቀለኛ ጥያቄ ሲፈርስበት ይህ የፈረሰው የምስክርነት ቃል እንደገና ህይወት እንዲኖረው ለማድረግ ነው፡፡

ስለዚህ አንድ ዳኛ የምስክሮችን ቃል በሚመዘግብበት ጊዜ እንዲጽፍ የሚጠበቅበት ጉዳይ በተከራካሪ ወገኖች ለምስክሩ የተነሱትን ጥያቄዎች ሳይሆን ለተጠየቁት ጥያቄዎች በምስክሩ የተሰጡት የምስክርነት ቃሎች ብቻ መሆን አለበት፤ ምክንያቱም ውሳኔ ለመስጠት የሚጠቅመው ጉዳይ በምስክር መስማት ሥነ-ሥርዓት ጊዜ ተከራካሪ ወገኖች የጠየቁት ጥያቄ ሳይሆን ምስክሩ የሰጠው ቃል ስለሆነ ነው፡፡ እነዚህ የምስክሩ ቃሎች በሚመዘገቡበት ወቅት ግን በየትኛው ጥያቄ ሥር (ማለትም በዋና፣ በመስቀለኛ እና በድጋሚ ጥያቄ ሥር) የትኛው የምስክርነት ቃል እንደተሰጠ መመዝገብ አስፈላጊ ነው፡፡ ምክንያቱም በዋና ጥያቄ እንዴት እንደተመሰከረ፣ በመስቀለኛ ጥያቄ የፈረሰ ከሆነ

እንዴት እንደፈረሰ ያልፈረሰ ከሆነ እንዴት እንዳልፈረሰ እና በድጋሚ ጥያቄ ህይወት እንዲዘራበት ተደርጎ ከሆነ እንዴት እንደተጠገነ ሳይጠገን የቀረ ከሆነም እንዴት እንዳልተጠገነ የሚያሳየን ጉዳይ ስለሆነ ነው።

አንዳንዴ ምስክሩን በጠራው ወገን ዋና ጥያቄ ከተጠየቀ በኋላ እየተመሰከረበት ባለው ተከራካሪ ወገን መስቀለኛ ጥያቄ የለኝም ተብሎ ሳይጠየቅ ሊቀር ይችላል፤ ወይም መስቀለኛ ጥያቄ ተጠይቆ ምስክሩን የጠራው ተከራካሪ ወገን የለኝም በማለቱ ድጋሚ ጥያቄ ሳይጠየቅ ሊቀር ይችላል። እንዲህ በሚሆንበት ጊዜ ፍ/ቤቱ ለተከራካሪ ወገኖች ዕድሉን እንደሰጣቸው ነገር ግን እነሱ በራሳቸው ጊዜ በዕድሉ ያልተጠቀሙ መሆኑን ለማሳየት እንደ ሁኔታው መስቀለኛ እና/ወይም ድጋሚ ጥያቄ ተብሎ ርዕሱ ተጽፎ በኃኑ ወይም በሥሩ "የለም" ተብሎ ያልተጠየቀ መሆኑን በሚገልፅ መልኩ መጻፍ አለበት።

10.1 <u>ምስክር በመስማት ሂደት አጻጻፍ ላይ የሚታዩ ችግሮች</u>

በሁሉም ፍ/ቤቶች በሚከናወነው የምስክር አሰማም ሂደት ላይ ከዋና መስቀለኛና ድጋሚ ጥያቄ በተጨማሪ የፍ/ቤቱ የማጣሪያ ጥያቄ በአራተኛነት ከድጋሚ ጥያቄ ቀጥሎ ሊመዘገብ ይስተዋላል። ነገር ግን የፍ/ቤቱ የማጣሪያ ጥያቄ አራተኛ የምስክር አሰማም ሥነ-ሥርዓትና ከድጋሚ ጥያቄ ቀጥሎ ብቻ የሚጠየቅ ሳይሆን በሥነ-ሥርዓት ህጎች በግልፅ እንደተቀመጠው ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት አስፈላጊ መስሎ ሲታየው ፍ/ቤቱ በማንኛውም ጊዜ ምስክሩን ማናቸውንም ጥያቄ ሊጠይቅ የሚችልበት አግባብ ነው። ይህ ማለት ደግሞ ፍ/ቤቱ አስፈላጊ መስሎ ሲታየው በዋና ጥያቄ ወይም በመስቀለኛ ጥያቄ ወይም በድጋሚ ጥያቄ ወይም በሶስቱም ጊዜ ምስክሩ ከሚሰጠው ምላሽ በመነሳት ግልፅ ያልሆኑ ጉዳዮችን ግልፅ ለማድረግ የሚጠየቅ፣ ራሱን የቻለ ጥያቄ ሳይሆን በተከራካሪ ወገኖች በሚጠየቁ ሌሎች ጥያቄዎች ላይ የተንጠለጠለ የፍ/ቤቱ የማጣሪያ ጥያቄ ነው። ስለዚህ ከህጉ ድንጋጌና ሀሳብ ውጭ በሆነ መልኩ እንደ አራተኛ የምስክር መስማት ሥነ-ሥርዓት መቀመጡ ሊቀር ይገባል።

በመቅረፀ-ድምፅ የተሰሙ የምስክርነት ቃሎች ከመቅረፀ-ድምፅ ወደ ወረቀት ተገልብጠው በሚጻፉበት ጊዜ ምንም እንኳ ምስክሩ በቀጥታ የተናገረው ቃል እንዲቀመጥ ለማድረግ መሞከሩ ጥሩ ቢሆንም ጸሀፊዎች በሚጽፉበት ጊዜ የፊደላት ግድፈቶች፣ የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ችግሮች እና ሌሎች ቋንቋ ነክ ችግሮች ጎልተው የሚታዩ በመሆኑ

በቀላሉ አንብቦ ለመረዳት የማይቻል ስለሚሆን እንዲህ ዓይነት ችግሮች ሊቀረፉ ይገባቸዋል።

11.<u>ፍርድና ውሳኔ መፃፍ</u>

አንድ ጉዳዩ የመጨረሻ እልባት የሚያገኘው ግራ ቀኙ ባልተግባቡት የፍሬ ነገር ክርክር፣ የህግ ክርክር ወይም የፍሬ ነገር እና የህግ ክርክር ላይ እልባት በመስጠት ይሆናል። የሚሰጡ እልባቶችም /መደምደሚያዎች/ ፍርድ፣ ውሳኔ፣ ብይን፣ ትዕዛዝ በመባል ይታወቃሉ። በኢፌዲሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 37 ላይ ስለፍትህ የማግኘት መብት ሲደነገግ በፍርድ ማለቅ ባለበት ጉዳይ ላይ ማንኛውም ሰው ፍርድ ወይም ውሳኔ የማግኘት መብት እንዳለው ተደንግጓል። ሕገ መንግሥቱ ከአንቀፅ 80 በኋላም የዳኝነት አካላት ስለሚሰጡት ውሳኔና በውሳኔው ላይ ስለሚቀርብ የሰበር ስልጣን ዝርዝር አስቀምጧል።

የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህጉ ፍርድ፣ ውሳኔና ትዕዛዝ ለሚሉት ቃላት ትርጉም ይሰጣል። በሌላ በኩል በህጉ ላይ ***ብይን*** የሚለውን ቃል የሚጠቀም ሲሆን ለዚህ ቃል ግን ትርጉም አይሰጥም። ሆኖም ግን ከአጠቃቀሙ ለመረዳት እንደሚቻለው ግን ብይን ማለት ከሳሽና ተከሳሽ በዋነኝነት በሚከራከሩበት ጉዳይ ላይ ለከሳሽ መብትን የሚሰጥ በተከሳሽ ላይ ግዴታን የሚጥል ውሳኔ ሳይሆን ከዚህ መለስ ባሉ ጉዳዮች ላይ የሚሰጥ ውሳኔ ነው።

<u>ለምሳሌ</u>፡-

- ጊዜያዊ አገልግሎት ባለው ትዕዛዝ /Interlocutory Decisions/ ላይ የይግባኝ ጥያቄ በሚቀርብበት ጊዜ ለዚህ ጥያቄ ውሳኔ የሚሰጠው በብይን ነው። **(የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 320(3))**
  - የቀነ ቀጠሮ ውሳኔ
  - ዳኝነት ሳይከፈል በነፃ ለመክሰስ እንዲፈቀድ በሚቀርብ ጥያቄ የሚሰጥ ውሳኔ
  - በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ የሚሰጥ ውሳኔ

ከትርጉሞቹ በግልፅ መረዳት የሚቻለው ግን ፍርድ የሁሉም /ማለትም የውሳኔ፣ የብይንና የትዕዛዝ/ መሠረት መሆኑን ነው። ትዕዛዝ እና ብይን ጉዳዩ ፍርድ ቤት

ከቀረበበት ቀን አንስቶ በየቀጠሮው የሚሰጡ ሲሆን ውሳኔ እና ፍርድ ግን በስተመጨረሻ የሚሰጡ ናቸው።

በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 180 ላይ ጉዳዩ ወይም ነገሩ እንዳለቀ ፍርድ ወዲያውኑ ወይም በአጭር ቀነ ቀጠሮ መሰጠት እንዳለበት ሲደነግግ የሚሰጠው ፍርድም በፅሁፍ መሆን እንዳለበት እና በዳኛ /ዳኞች/ ተፈርሞበት ለተከራካሪ ወገኖች መነበብ እንዳለበት ተደንግጓል። በወ/መ/ሥ/ሥ/ህጉ ውስጥ ተመሳሳይ አገላለፅ ባይገኝም በቁጥር 194 ላይ ፍርድ ግራ ቀኙ ወገኖች የመጨረሻ ንግግራቸውን ካደረጉ በኋላ የሚሰጥ መሆኑ ይደነግጋል።

የፍትሀዊ የችሎት ሂደት እና የፍትሃዊ ውሳኔ ማሰሪያውና መገለጫው ትክክለኛ የሆነ የውሳኔ አፃፃፍ ነው። ስለሆነም ትክክለኛ የሆነ የውሳኔ አፃፃፍ በጥቅሉ ማህበራዊ እና ሲቪክ ዓላማዎችንም ለማሳካት ይጠቅማል ማለት ነው። ይህንን ጥቅል አላማ ለማሳካት እና ተቀባይነት ያለው ውሣኔ ለመስጠት ውሳኔ ሰጭው በመጀመሪያ ደረጃ የውሳኔው ዓላማ ምንድን ነው ብሎ መጠየቅ ይኖበታል።

11.1. <u>የፍርድና ውሳኔ ዓላማዎች</u>

ፍርድና ውሳኔ የተለያዩ ዓላማዎችን ለማሣካት ይጠቅማል።

- **በበላይ ውሳኔ ሰጭ /ይግባኝ ሰሚ/ አካል ምክንያቶቹ በግልፅ እንዲመረመሩ ለማስቻል ነው።**
  - የበላይ ፍርድ ቤቶች በተለይ ትኩረታቸው በህግ ስህተት ላይ ይሆናል። ስለሆነም በፍሬ ነገር ላይ የተሰጠን ውሳኔ እና ትችት የመከለስ እድሉ እየጠበበ የሚመጣ መሆኑን በመረዳት በተለይ የበታች ፍ/ቤቶች ውሳኔ ሲሰጡ ፍሬ ነገርን በአግባቡ መተንተን ይገባቸዋል።
- **ከህዝብ ጋር መገናኛ መሆኑ**
  - ውሳኔ በመጀመሪያ ደረጃ በህግ የሰለጠኑ ባለሙያዎችን ወይም በግንባር የቀረቡ ተከራካሪዎችን መሠረት አድርጐ የሚፃፍ ቢሆንም ውሳኔ ለሚመለከተው ሰው ሁሉ እንዲሁም ለህዝቡ እንደሚደርስ ማሰብ ተገቢ ነው።
  - ስለሆነም ውሳኔ ሲፃፍ ማንኛውም ሰው /<u>Layman</u>/ በቀላሉ አንብቦ ውሳኔው ለምን እንደተፃፈ ሊረዳው የሚችል መሆኑን ማረጋገጥ ተገቢ ነው።

- ❖ ምክንያቱም ሌሎች ባለሙያዎች እንደሚያደርጉት ዳኞች እያንዳንዱን ውሳኔ በትንታኔ ለማስረዳት ሬዲዩ ወይም ቴሊቭዝን ወይም ጋዜጣን አይጠቀሙም፡፡
- ❖ ማብራሪያ ወይም ትንታኔ የሚፈልጉ ሰዎችም በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ በምን ምክንያት እንደተሰጠ ለዳኞች የስልክ፣ የፋክስ፣ የደብዳቤ ወይም የኢሜል መልዕክት በመላክ ማብራሪያ መጠየቅ አይጠበቅባቸውም፡፡
- ❖ ይህን ችግር ለመቅረፍ ደግሞ ግልፅ፣ አጭር እና ውሳኔው ለምን እንደተሰጠ እና መባል ያለበትን ነገር ሁሉ የያዘ ውሳኔ ከህብረተሰቡ ጋር በቀላሉ ለመግባባት የሚያስችል ነው፡፡
- ❖ በዚህም መሰረት ከጉዳዩ ውስጥ አስፈላጊ የሆነውን ፍሬ ነገር እና ህግ አስፈላጊ ካልሆነው በመለየት እነዚህ ጥያቄዎች በማይነሱበት አግባብ ምላሽ የሚሰጥ ውሳኔ መፃፍ ያስፈልጋል፡፡

- ➢ **እያንዳንዱ ተከራካሪ ወገን ውሳኔው እንዴት እና ለምን እንደተሰጠ በግልፅ ማወቅ ስላለበት**
  - ❖ ተከራካሪ ወገን እውነቱን እያወቀው በክርክር ሲረታ ቅሬታ የሚሰማው መሆኑ ተፈጥራዊ ነው ለማለት ይቻላል፡፡
  - ❖ ይህንን የውስጥ ስሜት እና ቅሬታ ሊያስቀር የሚችለው ጉዳይ ደግሞ በውሳኔው ላይ የሚሰፍረው ምክንያት፡-
    - ⇒ ተከራካሪ ወገኖች በአግባቡ የተሰሙ፣
    - ⇒ ማስረጃቸው በአግባቡ ግምት ውስጥ የገባና ፍርድ ቤቱ የተረዳው
    - ⇒ እንዲሁም ማንኛውንም ፈራጅ ህሊና ያለውን ሰው ፍ/ቤቱ ከደረሰበት መደምደሚያ በቀር ሌላ አማራጭ የሌለው መሆኑን ሲያሳምን ነው፡፡
  - ❖ ይህንን ዓላማ ለመፈፀምም አንዳንድ ጊዜ እንደሚታየው ዳኞች አሻሚ ቃላትንና ሃሳቦችን መጠቀም የለባቸውም፡፡
  - ❖ ይህ ዓላማ በተለይ በህግ ባለሙያ ያልተወከሉ ሰዎች በሚከራከሩበት ጊዜ አለዚያም ጉዳያቸው በሌሉበት የታዩ ሰዎች ባሉበት ጊዜ ውሳኔውን አንብበው /አስነብበው/ ከመረዳት በቀር ሌላ አማራጭ የሌላቸው በመሆኑ በተለየ ሊተኮርበት ይገባል፡፡

- ❖ ውሳኔ ግልፅ እና የተተነተነ በሆነ ቁጥር ተከራካሪ ወገኖች ውሳኔውን በአጭር ጊዜ ውስጥ ለማስፈፀም ብቻ ሳይሆን ከውሳኔ በኋላ ጉዳያቸውን በድርድር ጭምር ለመፍታት ያላቸውን እድል የሚያሰፋ ነው።
- ❖ ግልፅነት የጎደለውና እና ያልተተነተነ ውሳኔ ከሆነ ግን በተገላቢጦሽ ሁለቱንም ተከራካሪ ወገኖች በይግባኝ እንዲከራከሩና የበለጠ ወጪ እንዲያወጡ የሚጋብዝ ነው።
- ❖ ስለዚህ እያንዳንዱ ተከራካሪ ወገን ውሳኔው እንዴትና ለምን እነደተሰጠ በግልፅ ሊያውቀው በሚችል መልኩ ውሳኔው መፃፍ አለበት።

- ➢ **ውሳኔው ግልፅ ሃሳብ መያዝና ይህንንም በተመሣሣይ መልኩ በግልፅ ማስፈር አለበት።**
  - ❖ በተለያዩ ፍ/ቤቶች በርካታ ደካማ የውሳኔ አፃፃፎች እና እጅግ ለማንበብ አሰልቺ የሆኑ ፍርዶችም ይታያሉ።
  - ❖ ብዙ ጊዜ ተከሳሹ ለጥፋቱ በማስጠንቀቂያ ተቀጥቶ ከሚሰናበተው በላይ የውሳኔው አንባቢ የሆነ ሰው በጊዜው፣ በትዕግስቱ እና በጉልበት የሚቀጣው የሚበልጥባቸው ውሳኔዎች በርካታ ናቸው።
  - ❖ ይህን መሰሉን ችግር ለመቅረፍ ውሳኔ ሰጪ አካል በሃሳቡ ግልፅ፣ በአፃፃፉ ሳቢ እና ሃሳቡ ለታዳሚው በቀላሉ ተደራሽ መሆን ይገባዋል።

11.2. <u>የውሣኔ ቅርጽና ይዘት</u>

ሰው ስንል መጠኑ፣ ቀለሙ ... ይለያይ እንጅ ከራስ ጀምሮ እስከ እግር ጥፍር በሀሳባችን የሚታየን ቅርፅ ይኖራል። ውሳኔም ስንል በተመሣሣይ መልኩ ሊታየን የሚገባ ቅርፅ ይኖራል። በዚህም መሰረት ውሳኔን ቅርፅ የሚያስይዘው፡-

- ➢ **የመጀመሪያው ነጥብ የፍሬ ነገር ጭብጥ ነው።**
  - ❖ የፍሬ ነገር ጭብጥ ስንል ተከራካሪ ወገኖች ያነሷቸውን ነጥቦች በሙሉ ሳይሆን አግባብነት ያላቸውን እንዲሁም ተከራካሪዎች ያልተማመኑባቸው ነገሮች ለማለት ነው።

- ዳኞች የፍሬ ነገርን ጭብጥ ከያዙ በኋላ ወደ መደምደሚያ መመራት ያለባቸው በህግ እና በህግ ብቻ ስለሆነ ይህ በተለይ ተለይቶ መቀመጥ /መመልከት/ አለበት፡፡
- ከጉዳዩ ጋር ከማይገናኝ ፍሬ ነገር ላይ እና የሚያስማሙ ነገሮች ላይ ማተኮር ውሣኔን ሳቢ አያደርገውም፡፡
- ስለዚህ ውሳኔ የሚጽፍ ዳኛ ተከራካሪዎችን ያለያዩአቸውን ፍሬ ነገሮች በተለይ በውሳኔው ውስጥ የግድ ማስቀመጥ ይኖርበታል፡፡

➢ **ሁለተኛው ነጥብ ህግ ነው፡፡**

- ዳኞች እያንዳንዱን ጉዳይ በህግ እንደዳኙ ማመላከት ብቻ ሳይሆን ህጉንም መጥቀስ አለባቸው፤ ምክንያቱም በኢ.ፌ.ድ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 79 ላይ በግልፅ እንደሰፈረው ዳኞች የሚመሩት በህግ ብቻ ነው፡፡
- ለጉዳዩ እልባት ለመስጠት አስገዳጅ የሆነ ውሳኔ መጠቀስ ያለበት ከሆነም የውሳኔውን ቁጥር እና አስገዳጅ ያደረገውን ህግ በተመሣሣይ መልኩ መጥቀስ አለባቸው፡፡ (**አዋጅ ቁጥር 494/97**)

➢ **ሶስተኛው ነጥብ ለሚወሰነው ውሳኔ ምክንያት መስጠት ነው፡፡**

- ህጉ ለተያዘው ፍሬ ነገር እልባት ለመስጠት በአግባቡ የሚፈፀም መሆኑን ማሳየትና ምክንያት መስጠት አለበት፡፡

➢ **አራተኛው ነጥብ ህጉ አግባብ ያለው መሆኑ ከተለየ በኋላ ወደ መደምደሚያው ማምረት ነው፡፡**

- መደምደሚያ በተለይ «**ስለሆነም**»፣ «**በዚህም መሰረት**» በሚሉ እና በመሳሳሉት ቃላት መጀመር አለበት እንጅ «**ቢሆንም**» እና በመሳሰሉት አሉታን በሚያሳዩ አያያዥ ቃላት የሚታጠፍ መሆን የለበትም፡፡

➢ **በመጨረሻም እንደ ወጭና ኪሳራ የመሳሰሉ አስተዳደራዊ ጉዳዮች ይፃፉ፡፡**

በአጠቃላይ አንድ ውሳኔ በቅርፅ ፍሬ-ነገር፣ ጭብጥ፣ ህግ፣ ምክንያት፣ ድምዳሜ እና ወጭና ኪሳራ መያዙን ማረጋገጥ ይገባል፡፡ ውሳኔውን ይፋ ከማድረግ በፊት በክለሳ መልክ የውሳኔውን ቅርፅ መመልከቱ ይጠቅማል፡፡

11.3. <u>የሀገራችን የውሳኔ አፃፃፍ ቅርፅና ዘይቤ</u>

እንደሚታወቀው በሀገራችን በኢፌዲሪ ህገ-መንግስት መሠረት ከተቋቋሙት የመንግስት አካላት ውስጥ ፍ/ቤት አንዱ ነው፡፡ በፌዴራልም ሆነ በክልል በየትኛውም ደረጃ

የተቋቋሙ ፍርድ ቤቶች ህግ የማውጣት ስልጣን አልተሰጣቸውም። ይልቁንም በወጡ ህጐች ብቻ እየተመሩ የዳኝነት /ህግ የመተርጐም/ ተግባር ብቻ እንዲፈፅሙ ነው የሚጠበቀው። በዚህም መሰረት በህግ ሥርዓታችን የዳኛ ሚና የሚሆነው ህግንና ፍሬ ነገርን በማገናኘት ውሳኔ ላይ መድረስ ነው።

ህብረተሰባችን የዳበረ ባህላዊ የሙግት መፍቻ በርካታ መንገዶች እንዳሉትም ሁሉ ክርክሩን ለዳኝነት አካል አቅርቦ ውሳኔ የመጠየቅ ተመሳሳይ ልምድም አለው። በዚህም ምክንያት በፍርድ ቤቶቻችን በየዓመቱ በሺዎች የሚቆጠሩ ጉዳዮች ይቀርባሉ። የጉዳዮች መብዛት ደግሞ የውሳኔዎች አፃፃፍ አማራጭ ፖሊሲዎችንና ዝርዝር ፍሬ ነገሮችን ያላካተቱ እና አጭር እንዲሆኑ አንድ ምክንያት ሆኖ እናገኘዋለን። የሆነው ሆኖ ዳኞች ውሳኔ ሲሰጡ አቤቱታዎችን፣ ማስረጃዎችን፣ ፍሬ ነገሮችን፣ የቃል ክርክሮችን የመስማት እና የመመርመር ግዴታና ኃላፊነት ያለባቸው በመሆኑ የፍ/ቤቶቻችን ውሳኔ አፃፃፍም እነዚህን ጉዳዮች ያካተተ መሆን ይገባዋል።

በእርግጥ ጉዳዩ ወደ መጨረሻ ፍ/ቤት ሲደርስ በሰበር የሚመረመረው የህግ ጥያቄ ብቻ ሲኖር ቢሆንም በይግባኝ ሰሚነት የሚቀመጡ ዳኞቻችንም ቢሆኑ ከኮመን ሎው ሀገራት በተለየ መልኩ በስር ፍ/ቤት የታየን የህግ እና የፍሬ ነገር ክርክርን ይመለከታሉ። የበላይ ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤት ያነሳውን የህግም ሆነ የፍሬ ነገር ክርክር የመመርመር ስልጣን ስላለውም በወ/መ/ህ/ስ/ሰቁ 190 ላይ የስር ፍ/ቤት የመዝገቡን ግልባጭ /እንዳስፈላጊነቱም ሙሉ መዝገቡን/ ለበላይ ፍ/ቤት መላክ እንዳለበት ሲደነግግ በተመሳሳይ መልኩ የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 327 ይግባኝ የተባለለት የፍርድ ግልባጭ ብቻ ሳይሆን የመዝገብ ግልባጭም ለበላይ ፍ/ቤት መላክ እንዳለበት ይደንግጋል። ይግባኝ ባይም በይግባኝ ማመልከቻው ላይ ሊታረምለት የሚፈልገውን ህግ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ነገሮችንም መዘርዘር ይችላል።

በሥነ-ሥርዓት ህጐች ላይ በግልፅ እንደተመለከተውም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በራሱ ተነሳሽነት ወይም በተከራካሪ ወገን ጥያቄ ለትክክለኛ ፍርድ ይጠቅማል ያለውን ተጨማሪ ማስረጃ ተቀብሎም መመርመር ይችላል። ስለሆነም ከሰበር በቀር በሌላ ችሎት እና ደረጃ የሚገኙ የሀገራችን ዳኞች እንደ ኮመን ሎው ሀገራት ሳይሆን ፍሬ ነገርንም ሆነ ህግ መርምረው የመወሰን ኃላፊነት ያለባቸውና የውሳኔያቸው ቅርፅም ይህንን ያቀፈ መሆኑኑ ማረጋገጥ ይገባቸዋል። ይሁን እንጅ የበላይ ፍርድ ቤት በበታች ፍ/ቤት የፍሬ

ነገር እና የህግ ትንተና ከተስማማ ዝርዝር ነገር ሳይፅፍ አስተያየቱን በአጭሩ ማስቀመጥ ብቻ ይበቃዋል፡፡

በሀገራችን የዳኝነት ስርዓት ውስጥ **ችሎት** በአንድ፣ በሦስት ፣በአምስት ወይም ከዛ በላይ በሆኑ ዳኞች ሊሰየምና ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ቁጥራቸው ከአንድ በላይ የሆኑ ዳኞች ውሳኔ በሚሰጡበት ጊዜ እያንዳንዱ ዳኛ ውሳኔ እንዲፅፍ አይጠበቅም፡፡ ነገር ግን ከሁሉም ዳኞች የሚጠበቀው በውሳኔው ላይ ቀን ፅፈው እንዲፈረሙበት ነው፡፡ **(የወ/መ/ህ/ስ/ስ.ቁ 149(1) እና የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 181)**

በአንድ ውሳኔ ላይ ከአንድ በላይ የሆኑ ዳኞች ረቂቂ /ፅሁፍ/ ሊያዘጋጁ የሚችሉት የተለየ የውሳኔ ሃሳብ ያላቸው እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ እያንዳንዱ ዳኛ ውሳኔውን እንዲፅፍ የሚፈቅዱ የህግ ስርዓቶች /ኮመን ሎው ሀገሮች/ እንዳሉ እንዲሁም በውሳኔ የተለየ ሃሳብ እንዳይሰፍር የሚከለክሉ ሀገሮች ያሉ ቢሆንም የሀገራችን የህግ ስርዓት ውሳኔ በአንድ ዳኛ ብቻ እንዲፃፍ የተለየ ሃሳብም ካለ እንዲሰፍር ይፈቅዳል፡፡ በዚህም መሰረት በልዩነት ሃሳቡን ያሰረፈ ዳኛ በአብዛኛው ሃሳብ ላይ አይፈርምም፡፡ የልዩነት ሃሳብን ማስፈር፡-

- ፍ/ቤቶች ምን ያህል ነፃ ሆነው ለመስራታቸው አንድ አመላካች ነገር ነው፡፡
- በሌላ በኩል ለተችዎች፣ ለህብረተሰቡም ሆነ ለበላይ ፍ/ቤት የሥር ፍ/ቤት ውሳኔውን በሰጠበት ወቅት የነበሩትን አማራጮች ለማመልከት ያስችለዋል፡፡
- የልዩነቱ መስፈር በፍ/ቤት ሊታዩ የሚችሉ የተለያዩ ሃሳቦችን በመመዘንና የተሻለውን ለመምረጥ ያስችላል፡፡
- በልምድ እንደሚታየውም በልዩነት የተወሰነ ውሳኔ በጉዳዩ ላይ ዘርዝር ያለ ማብራሪያ የሚይዝ በመሆኑ ለሀገራችን የህግ ፍልስፍና መዳበር ያለው ሚና ቀላል አይሆንም፡፡

እዚህ ላይ መጠንቀቅ ያለብን ጉዳይ የልዩነት ሃሳብ መሰረታዊ በሆነው ጉዳይ ላይ ላቅ ባለ ክህሎት ካልተፃፈ በአመዛኙ የፍ/ቤትን ክብር እና አመኔታ ሊጐዳም እንደሚችል በመገንዘብ የልዩነት ሀሳብ ስንፅፍ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያለብን መሆኑን ነው፡፡

በኮመን ሎው ሀገራት የሚኖረው ውሳኔ ረዘም ያለ የምርምር እና የህግ አውጪነት ሚናን የተላበሰ ነው። የሀገራችን የፍርድ አፃፃፍ ግን ወደ አንድ መደምደሚያ የሚያደርሱ ምክንያቶችን ብቻ በመዘርዘር የሚቀመጥ ነው። ይህ ማለት አንድ የህግ አውጪ አካል ህግ ለማውጣት በመግቢያ /preamble/ የሚያስቀምጠው አይነት ምክንያት ነው በሀገራችን የፍርድ አፃፃፍ በጭብጥ እና በመደምደሚያው መሀከል የሚቀመጠው።

11.4. የሀገራችን ፍርድ አፃፃፍ አንዳንድ ችግሮች

11.4.1. የፍ/ብሔር ፍርድ አፃፃፍ

በሀገራችን ፍርድ በዘመናዊ መልክ በፅሁፍ መሰጠት የተጀመረው የፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 2/1934 ከወጣ በኋላ ነው። ፍርድ ቤቶች በዚህ ዓመት ከተቋቋሙ በኋላ በ1935 ዓ/ም በወጣው የህግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 3/1935 የሥነ-ሥርዐት ደንብ ወጥቶ በዚሁ የሥነ-ሥርዐት ደንብ መሠረት መመራት ጀምረዋል። ከአዋጅ ቁጥር 2/1934 በፊት ይሰጡ የነበሩ ፍርዶች የሚሰጡ በቃል ሲሆን ፍርዶችም ህግ በማውጣት መንፈስ ዓይነት የሚሰጡ ነበሩ።

ለምሳሌ ፡-

- በኢትዮጵያ የቀድሞ ፍርዶች ውስጥ ከተፈረዱት መሀከል "If any women divorced from her husband takes her child with her and marries another, she may not afterwards request the father of the child to pay her the cost of bringing up of the child" **የሚለው ወደ አማርኛ ሲተረጎም «አንድ ከባሏ በፍች የተለየች ሴት ልጇን ይዛ ሌላ ወንድ ብታገባ ከቀድሞ ባሏ ለልጇ ማሳደጊያ ወጭ መጠየቅ አይገባትም።»** በማለት የተሰጠ ፍርድ አለ። ይህ ፍርድ ሕግ የማውጣት ይዘት ያለው እንጂ የወጣን ሕግ የመተርጎም ባህሪ ያለው አይመስልም።

ፍ/ቤቶች በ1934 ዓ/ም ከተቋቋሙ በኋላ ግን ፍርድ በፅሑፍ መስጠት ተጀምሯል። ይሁን እንጅ በዚህ ጊዜ ለእያንዳንዱ ፍርድ መዝገብ ሳይከፈት በአንድ ጥቅል ባህረ መዝገብ ፍርዱ በፅሁፍ ይሰጥ ነበር። ይህንን የውሳኔ አሰጣጥ በዘመናዊ መልክ የቀየረው በ1958 የወጣው የፍ/ብሐር ሥነ-ሥርዓት ህግ ነው። ይሁን እንጅ ህጉ ከወጣም በኋላ እስካሁን ድረስ የፍርድ አፃፃፍ ሥርዓት በአግባቡ ሳይፈፀም እንመለከታለን። ለዚህም እንደ ምክንያት የሚቀመጡት፡-

- የመጀመሪያው ምክንያት የሥነ-ሥርዓት ህጉ ስለፍርድ አፃፃፍ የያዛቸው አናቅጽ ዝርዝር እና የተሟላ የፍርድ አፃፃፍን የማያመላክቱ መሆናቸው ነው።
- በፍርድ አፃፃፍ ውስጥ ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱትና ይዘቱን የሚወስኑት ፍርድ፣ ውሳኔ፣ ትዕዛዝ እና/ወይም ብይን ናቸው ። ሥነ-ሥርዓት ህጋችን ፍርድ፣ ውሳኔ እና ትዕዛዝ ለሚሉት ቃላት ትርጉም ይሰጣል። ይሁን እንጅ ትርጉሙ በራሱ ሎጅካል ያልሆነ አደናጋሪ ከመሆኑም በላይ በዝርዝር ድንጋጌ ላይ አንዱ ለሌለው ጥቅም ላይ ሲውል ይስተዋላል።
- በሌላ በኩል በህጉ የተለያዩ ቦታዎች ላይ (ምሳሌ ፡- በትርጉም ውስጥ፣ቁጥር 181/2/፣ 466) «**ብይን**» የሚለው ቃል ሥራ ላይ የዋለ ቢሆንም ትርጉሙ ግልፅ አይደለም። ይሁን እንጅ የቃላቱ አጠቃቀም ግልፅ ባለመሆኑ በውሳኔ አፃፃፍ ላይም ተመሳሳይ ችግር ሲያስከትል ይስተዋላል።

  <u>ለምሳሌ</u>፡-

  - ክስን የመሰረዝ ባህሪ ያለው መደምደሚያ **ትዕዛዝ**፣ **ብይን** እና **ውሳኔ** በሚል ሲፃፍ እንመለከታለን፣
  - ክስን የመሰረዝ ባህሪ የሌለው መደምደሚያ **ትዕዛዝ** እና **ብይን** አልፎ አልፎም **ውሳኔ** እየተባለ ይፃፋል፣
  - ይግባኝ የማይባልበት መደምደሚያ ሁሉ **ትዕዛዝ** እየተባለ ይፃፋል፤
  - ይግባኝ የሚባልበት መደምደሚያ /ቁ. 244,166/ **ትዕዛዝ** እና **ብይን** እየተባለ ይፃፋል፣
  - በከፊል ይግባኝ የሚባልበት መደምደሚያ **ትዕዛዝ** ወይም **ብይን** /ምሳሌ፡- ቁጥር 324,6/ እየተባለ ይፃፋል ፣
  - በማናቸውም ጊዜ ይግባኝ የማይልበት ውሣኔ /ምሳሌ ቁጥር 6/ **ትዕዛዝ** እየተባለ ሲፃፍ እንመለከታለን።

ህጉ በግልፅ ለቃላቱ ትርጉም አለመሰጠቱ በአፃፃፍ ላይም ተመሳሳይ ውጤት እንዲኖረው አድርጓል። በዚህም መሰረት፡-

- ለሚሰጠው መደምደሚያ የምንጠቀምበት ቃል የተለያየ እና ወጥ ያልሆነ በመሆኑ የሚፃፈው ፍርድ ሳቢ እንዳይሆን ያደርገዋል።
- አንባቢም ሆነ ባለጉዳይ ከቃሉ መረዳት እና መማር የሚገባውን ቁም ነገር በአግባቡ እንዳይረዳና በንባብ ጊዜውን እንዲያባክንም ያደርገዋል።

- በሌላ በኩል በተደረሰበት መደምደሚያ ላይ ይግባኝ የማይባልበት መሆኑን ለማወቅ ከርዕሱ ሳይሆን ከይዘቱ ብቻ እንድንረዳ አድርጐናል፡፡
- አልፎ አልፎም ይግባኝ የሚባልበት ትዕዛዝ በትዕዛዝ ስም የሚሰጥ በመሆኑ ርዕሱን ብቻ በመመልከት «የትዕዛዝ ይግባኝ የለም» በማለት ይግባኙን ተቀባይነት የሚያሳጣ ትዕዛዝ ሲሰጥ ተመልክተናል፡፡

ሌላው በፍ/ብሔር ክርክር ውስጥ የውሳኔን ውበት ከመቀነሱ በላይ ባለጉዳይን ለወጪና ኪሣራ የሚዳረገው በልማድ የተከተልነው አሰራር ነው፡፡ በሥነ-ሥርዓት ህጉ ውስጥ ትዕዝዝ ወይም ብይን ለመስጠት የግራ ቀኙ የፅሁፍ ወይም የቃል ክርክር የሚደረግባቸው እንዳሉ ሁሉ ክርክር ማድረግ የማያስፈልጋቸውም አሉ፡፡

<u>ለምሳሌ</u>፡-

- በክስ ላይ አላግባብ የተመለከተን ተከሳሻ ከክስ ለማስወጣት ፍ/ቤቱ የግድ ማከራከር አይጠበቅበትም፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 40(2) መሠረት ፍ/ቤቱ ይህንን በራሱ አስተያየት መፈፀም ሲችል ያላግባብ ባለጉዳይን ካከራከረ በሚሰጠው ትዕዛዝ ላይም አላስፈላጊ ነገሮች እንዲፃፉበት ያደርጋል፡፡
- በሌላ በኩል በፍ/ቤት በተያዘ ክርክር ውስጥ ጣልቃ ልግባ የሚል ጥያቄ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 41 መሠረት የቀረበ እንደሆነ በክርክሩ ተካፋይ እንዲሆን ፍ/ቤቱ የሚፈቅደው ተከራካሪ ወገኖች አስተያየት ሳይሰጡበት ነው፤ ነገር ግን ተከራካሪዎች አስተያየት እንዲሰጡበት ከተደረገና ባለጉዳዮች እንዲከራከሩበት ከተደረገ በባለጉዳዮች ላይ አላስፈላጊ ወጭና ኪሳራ ከማስከተሉ በተጨማሪ ፍ/ቤቱ በሚሰጠው ትዕዛዝ ላይ አላስፈላጊ ነገሮች እንዲፃፉበት ያደርጋል፡፡
- በተመሳሳይ መልኩ የቀረበ ክስ ይሻሻል የሚል ትዕዛዝ በፍ/ቤቱ በራሱ አስተያየት ወይም በአንደኛው ተከራካሪ ወገን ማመልከቻ መነሻነት ሊሰጥ ይችላል እንጅ በቀረበው ማመልከቻ ላይ ባለጉዳዮችን ማከራከር አስፈላጊ አይደለም፡፡ በተለምዶ ግን በቀረበ ማመልከቻ ላይ ማከራከር ይታያል፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች የባለጉዳይን ወጪና ጉልበት ያላግባብ የሚያባክኑ ከመሆናቸው በተጨማሪ የሚፃፈው ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ በቅርጽ ደረጃ አስፈላጊ ያልሆኑ ፍሬ ነገሮችን እንዲያካትት ያደርገዋል፡፡

በሀገራችን የፍርድን አፃፃፍ ሥርዐት ውስጥ የሚፃፈው ውሳኔ ሳቢ እንዳይሆን ከሚያደርጉት ነጥቦች ውስጥ ሌላው ነጥብ ትዕዛዝ፣ ውሳኔ... በወቅቱ የማይሰጥ ሲሆን ነው፡፡

<u>ለምሳሌ</u>፡-

- በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 244/1/ መሠረት በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ የሚሰጥ ውሳኔ በፍሬ-ነገሩ ላይ አስረጅ የሆኑት ምስክሮች ከመስማታቸው ወይም ሌላ ማስረጃ ከመመርመሩ በፊት መሰጠት እንዳለበት በአስገዳጅነት ተደርግጓል፡፡ ነገር ግን ፍ/ቤቱ ነገሩን ሰምቶ ለመወሰን ስልጣን የለውም የሚል መቃወሚያ ቀርቦ በህጉ መሠረት ወዲያውኑ ለብቻው ብይን የማይሰጥበት በመሆኑ የተከራካሪ ወገኖችን ጊዜ፣ ጉልበት እና ወጪ፣ የፍ/ቤትንም ጊዜ፣ ጉልበት እና ወጪ ከማባከኑም በላይ በይዘቱ በስተመጨረሻ በሚሰጠው ፍርድ ላይ እንዲካተት የሚያደርገው በመሆኑ የፍርድን ቅርፅ ያለግባብ ያዛባል፡፡ የፍርድ እድምተኛ ትኩረቱ በተለያዩ ነጥቦች ላይም እንዲሆን ስለሚያደርገው የፍርዱን ተነባቢነት እንዲቀንስ ያደርገዋል፡፡
- አልፎ አልፎም በቀርበ መቃወሚያ ላይ ፍ/ቤቱ በፍርድ ደረጃም ቢሆን ውሳኔ ሳይሰጥበት የሚያልፍበት አጋጣሚ በመኖሩ፡-
  - ጉዳዩ በይግባኝ ቀርቦ ሲሻር አፍራሽ ውጤቱ ከሁሉ የከፋ ይሆናል፡፡
  - ጉዳዩ በይግባኝ ደረጃ ሲቀርብ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ማስረጃንና ህግን ያገናዘበ ለመሆኑ መመርመር የሚገባው በመሆኑ **«ይግባኙ መልስ ሰጭን ያስቀርባል ብለናል»** በማለት ትዕዛዝ በበርካታ መዝገቦች ላይ የሚሰጥ በመሆኑ የትዕዛዙ ይዘት ግልፅነት የጐደለው እንዲሆን ያደርገዋል፡፡
  - መልስ ሰጭ በምን ነጥብ ላይ አተኩሮ መልስ መስጠት እንዳለበት አይረዳም፡፡
  - ውሳኔ የሚሰጠው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤትም በምን የተለየ ነጥብ ላይ ማተኮር እንዳለበት ስለማይረዳ በስተመጨረሻም በድፍኑ የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ፀንቷል በማለት ውሳኔ ሲሰጥ ይታያል፡፡

11.4.2. <u>የወንጀል ጉዳይ ፍርድና ውሳኔ አፃፃፍ</u>

በሀገራችን እንደ ፍትሃ ብሄር ፍርድ ሁሉ የወንጀል ጉዳይ ፍርድም በዘመናዊ መልክ በፅሁፍ መሰጠት የተጀመረው የፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 2/1934 ከወጣ በኋላ ነው፡፡ ከዚህ አዋጅ በፊት ክርክሩም በአብዛኛው በቃል ቀርቦ በቃል ውሳኔ

ይሰጥበት የነበር ነው፡፡ ከዚህ ጊዜ በኋላ እስከ 1954 ድረስ ያሉ የተለያዩ ውሳኔዎች በተመሳሳይ መልኩ ተመሳሳይ የአፃፃፍ ዘይቤንና ቅርፅን ተከትለው እናገኛቸዋለን፡፡

የሆነው ሆኖ በጥቅሉ በህጉም ውስጥ ሆነ በልማድ ፍርድ እና ትዕዛዝ በግልፅ ትርጉም ተሰጥቷቸው አናገኝም፡፡ በመዝገቦቹ ላይ በግልፅ ተፅፈው የምናገኛቸው ፍርድ፣ ትዕዛዝ እና ቅጣት የሚሉትን ቃላት ሲሆን **ተወስኖባቸዋል፣ ተበይኖባቸዋል** የሚሉትም በፖራግራፍ ማሰሪያ ላይ ቢገኙም በአፃፃፍ ርዕስነት እምብዛም አናገኛቸውም፡፡ በዚህ ጊዜ የሚፃፉ ፍርዶችም በጣም በአጭሩ የሚፃፉ ሲሆኑ በፍርዶች ውስጥም ከክስ በላይ ውሳኔ፣ ከማስረጃ በላይ ትችት፣ የጭብጥ አለመያዝ እና የመሳሰሉት ጉድለቶች ጐልተው ይታዩባቸው የነበሩ ናቸው፡፡

የወንጀል የፍርድ አፃፃፍ በአብዛኛው በቃል የሚነገረው ወደ ፅሁፍ እየተቀየረ ልማዱን ይዞ እስከ 1954 ድረስ ከሞላ ጐደል ተመሳሳይ ይዞታ ይዞ ቆይቷል፡፡ ሆኖም ግን የወንጀል ምርመራ ተግባር በወረዳ ፍርድ ቤት ይከናወን ስለነበር በፖሊስ የምርመራ መዝገብ ውስጥ ስለሚፃፉ ክሶች፣ በዐ/ህግ ስለሚሰጡ የተጨማሪ ምርመራ ትዕዛዞች እና ስለሚጠየቁ መሪ ትዕዛዞች ወዘተ... የተገኘ ማስረጃ የለም፡፡

ኢትዮጵያ ህጐቿን ዘመናዊ በማድረግ ለማጠቃለል ከሞከረችባቸው ጊዜያት ውስጥ ተጠቃሎ በኮድ መልክ በ1954 ዓ/ም የወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ህግ ይገኝበታል፡፡ በዚሁ ህግ መሠረት በዐ/ሕግ እና በፍ/ቤት ዘንድ የሚሰጡ ውሳኔዎች በፅሁፍ ከመሆኑም አልፈው ይዘታቸው ምን መምሰል እንዳለበትም ተደንግጓል፡፡ በዚህም መሰረት ዐ/ሕግ ማስረጃውንና ህጉን መርምሮ ክስ ለመመስረት የወሰነ እንደሆነ ክሱን ለፍርድ ቤት በፅሁፍ አዘጋጅቶ የሚያቀርብ ሲሆን ፍ/ቤቱም ክሱን ከተቀበለበት ጊዜ አንስቶ የመጨረሻ ፍርድ እስከሚሰጥበት ጊዜ ድረስ ልዩ ልዩ ደረጃዎችን ያልፋል፡፡

በሥነ-ሥርዓት ህጉ ላይ እንደተመለከተው ፍ/ቤት ደረጃዎችን የሚያልፈው ፍርድ፣ ውሳኔ እና ትዕዛዝ በሚሉት ቃላት አማካኝነት ነው፡፡ በህጉ ላይ ፍርድ /judgment/፣ ውሳኔ /decision/እና ትዕዛዝ /order/ የሚሉ ቃላት በስፋት የሚገኙ ቢሆንም ለአንዳቸውም የህግ ትርጉም አልተሰጣቸውም፡፡ ብይን የሚለው ቃል ደግሞ ቀደም ሲልም ሆነ አሁን ሲሰራበት ብንመለከትም ቃሉ ግን በህጉ ላይ ሰፍሮ አናገኘውም፡፡ ስለሆነም በወንጀል ክርክር የውሳኔ አፃፃፍ ላይ በፍ/ቤት ዘንድ ብይን የሚለው ቃል ጥቅም ላይ መዋል ያለበት ነው ለማለት አያስደፍርም፡፡ ቀሪ ቃላት ትርጉም

ያልተሰጣቸው ከመሆኑ በላይ በተለዋዋጭነትም ጥቅም ላይ ሲውሉ ይታያል። ከሥነ-ሥርዓት ህጉ ዝርዝር ድንጋጌዎች ለመረዳት እንደሚቻለው ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት ክስ ከቀረበለት ዕለት አንስቶ በየዕለቱ ውሳኔ እየሰጠ ጉዳዩን እንደ አግባቡ ለፍርድ ያደረሳል። ይህ በየጊዜው የሚሰጠው የፍ/ቤት ውሳኔ ግን እንደሁኔታው በትዕዛዝ፣ በውሳኔ ወይም በፍርድ ሊገለፅ ይችላል።

- የፍርድ ቤት ውሳኔ በትዕዛዝ የሚገለፅባቸው አብነቶች፣
  - ክስ እንደቀረበ ክሱ የሚሰማበትን ቀን በቁጥር 123 እና 124 ወስኖ በቁጥር 125 *መሠረት* **በትዕዛዝ** ይገለፃል፣
  - በክስ ተቃውሞ ላይ ማስረጃ መሰረት በማድረግ ውሳኔ መስጠት ሲያስፈልግ ማስረጃ ያስፈልጋል የተባለበት ውሳኔ **በትዕዛዝ** ይገለፃል። / ቁጥር 131/
  - ዐ/ሕግ ክሱን ለማስረዳት ያቀረበው ማስረጃ የተከሳሽን መከላከያ መስማት ሳያስፈልግ ተከሳሹን በነፃ ለማሰናበት የሚያበቃው ሲሆን ይህ የፍ/ቤት ውሳኔ **በትዕዛዝ** ይገለፃል። /ቁ.141/
  - ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት በማሰብ ተጨማሪ ምስክር ቀርቦ እንዲሰማ ፍርድ ቤት ሲወሰን ይህ ውሳኔ ለተባሉት ተጨማሪ ምስክሮች **በትዕዛዝ** ይገለፃል፣
  - ተከሳሽ ተይዞ እንዲቀርብ የሚሰጥ ውሳኔ **በትዕዛዝ** ይገለፃል /ቁ.120/
  - ተከሳሹ በሌለበት ጉዳዩ እንዲታይ የሚሰጥ ውሳኔ **በትዕዛዝ** ይገለፃል /ቁ.121/
  - የጥፋተኛነት ፍርድ እና የቅጣት ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ አፈፃፀሙ የሚገለፀው በሚሰጠው **ትዕዛዝ** ነው፣ በዚህ መሰረት የሞት ፍርድ፣ እስራት፣ የገንዘብ ቅጣት፣ ስለንብረት፣ አካል መጠን ስላላደረሱ ወጣቶች፣ ወዘተ የሚሰጡ ውሳኔዎች አፈፃፀማቸው የሚገለፀው **በትዕዛዝ** መልክ ነው። /ቁ.203 እና ተከታዮች/።
  - በክስ ላይ ለሚቀርብ ተቃውሞ ተቃውሞውን ለመቀበል ወይም ውድቅ ለማድረግ የሚሰጥ ውሳኔ የሚገለፅ **በትዕዛዝ** ነው። /ቁ.131/2/
  - አንድ ማስረጃ ሊቀርብ አይገባም፣ ይገባል፤ ለምስክር የቀረበ ጥያቄ ተገቢ ነው አይደለም የሚል ክርክር በዐ/ሕግ እና በተከሳሽ መካከል የተነሳ እንደሆነ ፍ/ቤቱ በጉዳዩ ላይ ያለው አስተያየት **በትዕዛዝ** ይገለፃል /ቁ.146፣98/ቀ/

- በርካታ ተከሳሾች ባሉበት መዝገብ በህግና ፍሬ-ነገሩ ላይ ተከሳሾች የሚያደርጉትን ንግግር ተራ ለመወሰን ፍ/ቤቱ የሚሰጠው አስተያየት **በትዕዛዝ** ይገለፃል፡፡

- የፍ/ቤት ውሳኔ «**ውሳኔ**» በሚል ርዕስ ከሚገለፅባቸው ውስጥ፣
  - ተከሳሽ ክሱ ከተነበበለት በኋላ ሙሉ በሙሉ ወንጀሉን መፈፀሙን ያመነ እንደሆነ የጥፋተኝነት ውሳኔ ይሰጥና ቅጣቱ **በውሳኔ** ይገለፃል፡፡/ቁ.134፣ 135፣/
  - በፍርድ ውስጥ የሚፃፍ ቅጣት ራሱን ችሎ **ውሳኔ** በሚል ርዕስ ስር ይፃፋል /ቁ.149(5)፣ 177/
- የፍርድ ቤት ውሳኔ «**በፍርድ**» የሚገለፀው ፣
  - ክርክር ተጠናቆ ተከሳሽ የሚቀጣበት ውሳኔ ወይም በነፃ የሚለቀቅበት ውሳኔ **በፍርድ** የሚገለፅ ነው/ቁ. 138፣149/
  - ዐ/ሕግ እና ተከሳሹ ክርክር ስለተደረገበት ጉዳይ እና ህጉ የመሰለቸውን የመጨረሻ ንግግር ካደረጉ በኋላ ፍ/ቤት ነገሩን የሚቋጭበት ውሳኔ በፍርድ ተዕፎ ይገለፃል፡፡/ቁ. 149/
- በአጠቃላይ፡-
  - ፍርድ እና ውሣኔ የሚሉትን ቃላት በተቻለ መጠን ህገ-መንግሥቱ ላይ እንደተመለከተው ለመጨረሻ ውሣኔ መጠቀም የሚበጅ ሲሆን ከዚህ በቀደሙት ላይ ትዕዛዝ የሚለውን መጠቀም ይበጃል፡፡
  - በመጨረሻም ጉዳዩ ከተቋጨ በኋላ ዐ/ሕግ ወይም ተከሳሽ ስላላቸው የይግባኝ መብት በፍ/ቤቱ ይነገራቸዋል፡፡ ይህ ንግግር መሠረት የሚያደርገው የፍ/ቤትን የይግባኝ መብት ውሳኔ ሳይሆን አግባብ ባለው ህግ የተወሰነውን የይግባኝ መብት ነው፡፡

11.5. <u>የውሣኔ አፃፃፍ በፍርድ ቤቶች ደረጃ</u>

የውሣኔ አፃፃፍ ይዘት በጥቅሉ የተመሳሰለ ቢሆንም ከጉዳይ ጉዳይ ግን ይለያያል፡፡ በዚህም መሰረት በወንጀል ጉዳይ የሚፃፈው ውሣኔ በይዘቱ እና በቅርፁ በፍትሐብሔር ጉደይ ከሚፃፈው ይለያል፤ በፍ/ብሔር ጉዳይም በተፋጠነ ሥነ ሥርዓት የሚቀርበው በመደበኛው ሥርዓት ከሚቀርበው ይለያል፤ እንዲሁም በመደበኛ ከሚቀርበው ውስጥ

አከራካሪ ጉዳይ ያለው እና ጭብጥ የሌለው ልዩነት አላቸው፤ ጭብጥ በሌላቸው ውስጥም ቢሆን የውሣኔ አፃፃፍ በተለይ በውሣኔ ሰጭ ጥራት እና ትጋት ሊለያይ ይችላል፤ እንዲሁም በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሚፃፈው ፍርድና ውሳኔ በይግባኝ ፍ/ቤት ከሚፃፈው ፍርድና ውሳኔ ይለያል፡፡ በዚህም ምክንያት ልዩነቱ ማቆሚያ አይኖረውም፡፡ የሆነው ሆኖ ለአሁኑ ሥልጠናችን ይረዳን ዘንድ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቶች የሚጻፉ ውሳኔዎችና በይግባኝ ፍ/ቤቶች የሚጻፉ ውሳኔዎች የሚኖራቸውን ልዩነት እናያለን፡፡

11.5.1. <u>የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሣኔ አፃፃፍ</u>

የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቶች በተለይ የማስረጃ እና የፍሬ ነገር ክርክር በስፋት የሚካሄድባቸው እና የሚመዘገብባቸው በመሆኑ በእነዚህ ፍ/ቤቶች የሚፃፉ ውሣኔዎች በይዘታቸው እንደቅደም ተከተሉ፣

- የጉዳዩ ዓይነት
- ፍሬ ነገሮችን
- ጭብጥ /ጭብጦችን /
- የሕግትንታኔ እና ምክንያት
- ማጠቃለያ /ውሳኔ/ ሊይዙ ይገባል፡፡

ሀ) <u>የጉዳዩ ዓይነት</u>

ይህ የውሣኔ ክፍል ፍርድ እየተባለ ርዕስ ተሰጥቶት ከሚፃፈው ሥር በመጀመሪያ የሚሰፍረው ነው፡፡ ጉዳዩ የምን እንደሆነ፣ ያለፈበት አስፈላጊ ታሪክ፣ በጉዳዩ ላይ ፍ/ቤት ያለው ሥልጣን፣ ፍ/ቤቱ ሊወስን የሚገባውን ጉዳይ እና ተከሳሹ የሚጠየቅበትን ሁኔታ የሚይዝ ነው፡፡

<u>ለምሳሌ</u>፡-

- ጉዳዩ የመሬት ክርክርን የሚመለከት ቢሆን በጉዳዩ ላይ የመሬት አስታራቂ ወይም አስማሚ ሸማግሌዎች ያደረጉት የማስታረቅ ወይም የማስማማት ጥረት ውጤት አለማስገኘቱንና ጉዳዩ በሕግ መሠረት በፍርድ ማለቅ የሚገባው በመሆኑ ከሣሽ መሬቱን ለመረከብ ጥያቄ ማቅረቡ ይገለጽበታል፡፡

ለ) <u>ፍሬ ነገር</u>

ፍሬ ነገር ስንል በተከራከካሪ ወገን ማስረጃ ሊረጋገጡ ወይም ሊፈርሱ የሚችሉ ሕግ ነክ ያልሆኑ ክርክሮች ማለታችን ነው፡፡ በዚህም መሰረት ውሳኔ የሚጽፍ ዳኛ ውሳኔ በሚጽፍበት ጊዜ ተገቢ የሆኑትን የፍሬ ነገር ክርክሮች ብቻ መርጦ መመዝገብ ይኖርበታል፡፡

ተከራካሪ ወገን እና አንባቢ በውሣኔው ተስቦ በቀላሉ እንዲያነበው እና እንዲረዳው ውሳኔ በሚጻፍበት ጊዜ ፍሬ ነገሮችን ባለፈ ጊዜ መግለፅ ይኖርበታል፡፡ ጊዜን መጥቀስ አስፈላጊ ሲሆንም ፍሬ ነገሮች እንደቅደም ተከተላቸው ቢገለፁ ይመረጣል፡፡ በተጨማሪም የውሣኔው ፀሐፊ ውሳኔውን በሚፅፍበት ጊዜ ተከራካሪ ወገኖች እና/ወይም ሌላው አንባቢ ከፍሬ ነገሩ በይበልጥ የሚፈለገውን በሚያካትት መልኩ መፃፍ ይኖርበታል፡፡

<u>ለምሳሌ</u>፡-

- በመሬት ጉዳይ ከፍ/ቤት ክርክር አስቀድሞ በእርቅ ጉዳዩ መፈታት አለመቻሉ ቢገለፅ በቂ ሲሆን
- በውል ክርክር ጊዜ ውሉ የተፈፀመበት፣ የፈረሰበት ወዘተ ጊዜ እንደ ቅደም ተከተል እየጐላ መጠቀስ ያስፈልገዋል፡፡

የጊዜ ቅደም ተከተል ያለባቸው ጉዳዮች በሐተታ መልክ ወይም በመዘርዘር ሊገለፁ ይችላሉ፡፡

<u>ለምሳሌ</u>፡-

- ተከሳሹ ጎዳር 21 ቀን 2002 የተፈረመውን ውል ባለማክበር በውሉ ላይ የተመለከተውን መቶ ኩንታል ጤፍ በውሉ ላይ በተጠቀሰው ቀን ባለማስረከቡ ጥር አጋማሽ 2002 ዓ.ም ውሉ ፈረሰ ብሎ መፃፍ እንደሚቻለው ሁሉ፣
- 1.ጎዳር 21/2002 ውል ተፈፀመ
  2.በጥር አጋማሽ 2002 ውሉ ፈረሰ ተብሎ ሊቀመጥ ይችላል፡፡

ዳኞች ፍሬ ነገርን በውሳኔያቸው ውስጥ በሚያስፍሩበት ጊዜ፡-

- የይዘት ለውጥ እንዳይኖረው ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡
- በተቻለ መጠን በክርክሩ ቋንቋ መቀመጥ ይገባዋል፡፡

ዳኞች ህግን የመተርጎም ሥልጣን ያላቸው ሲሆን ፍሬ ነገርን ግን ከመመዝገብ ያለፈ የመተርጎም ሥልጣን የላቸውም፡፡

<u>ለምሳሌ</u>፡-

- ከሣሽ ጥር አ/ማሽ ውሉ ፈረስ ቢል ውሣኔ ሲፃፍ ጥር 15/2000 ተብሎ መጠቀስ አይኖርበትም፡፡

ፍሬ-ነገርን መተርጎም አንባቢን የማሳማን ኃይልን መቀነስ ከመሆኑም በላይ ፍሬ ነገርን የመመርመር ሥልጣናቸው /ኃላፊነታቸው/ እየቀነሱ የሚመጡ የበላይ ፍ/ቤቶችም በጉዳዩ ላይ የተዛባ ውሣኔ እንዲያሳርፉ በር የሚከፍት ስለሆነ በጥንቃቄ መፃፍ ይኖርበታል፡፡ ፍሬ-ነገር በጥንቃቄ መፃፍ አለበት ሲባል የተከራካሪ ወገን የፍሬ ነገር ክርክር እንዳለ መስፈር አለበት ማለት አይደለም፡፡

<u>ለምሳሌ</u>፡-

- ልጅነት ይረጋገጥልኝ የሚል አቤቱታ ከቀረበ መስፈር ያለበት አባትነትን ሊያረጋግጡ የሚችሉ ፍሬ ነገሮች እንጂ አባት የተባለው ሰው የዘር ግንድ ቢዘረዘር መስፈር አለበት ማለት አይደለም፡፡

አግባብ ያለውን ፍሬ ነገር መምረጥ ከፍተኛ ጥበብን፣ ዕውቀትንና ልምድን ይጠይቃል፡፡ ፍሬ ነገርን መርጦ ድምዳሜ ላይ መድረስም በተመሳሳይ መልኩ ጥንቃቄን የሚጠይቅ በሀገራችን የዳኛ ብቻ የሆነ ሥራ ነው፡፡ እዚህ ድምዳሜ ላይ ለመድረስም መነሻው ማስረጃ ብቻ ነው፡፡

<u>ለምሳሌ</u>፡-

- አባትነትን ለማስረዳት ከቀረበው ማስረጃ ውስጥ ፍ/ቤቱ ተከሣሽ አባት የተባለው፣ ከወ/ሮ.../እናት/ ጋር ጋብቻውን በ14/1/1970 መፈፀሙ ተረጋግጧል፡፡ የሚል የፍሬ ነገር መደምደሚያ ላይ ሊደረስ ይቻላል፡፡ ይህ የፍሬ ነገር መደምደሚያ በራሱ ትርጉም የሌለው በመሆኑ ወደ ሕግ መደምደሚያ መቀየር ይኖርበታል፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ ፍሬ ነገር በጉዳዩ ላይ ለተያዘው ጭብጥ እልባት የሚያሰጥ ይሆናል፡፡

በአንድ ውሳኔ ውስጥ በርካታ ፍሬ ነገሮች ይኖራሉ፡፡ ይህ ማለት ግን በፍሬ ነገር እና መደምደሚያ መኖር ሁል ጊዜ ጭብጥ ያስፈልጋል ማለት አለመሆኑን ማስታወስም

ይገባል፡፡ ፍሬ ነገሮች ክስ ላይ ለተመለከቱ ጉዳዮች መረጃ የሚሰጡ፣ በተከሳሹ የታመኑ፣ በማስረጃ የተረጋገጡ፣ በተከሳሹ የተካዱ ጭብጦች፣ ወዘተ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

<u>ለምሳሌ</u>፡-

- ክስ የተመሠረተበት ቀን፣ የከሣሽ ቀበሌ፣ የከሣሽ ችሎታ በእነዚህ ዝርዝር ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ እነዚህ ፍሬ ነገሮች ውሣኔ እስከተደመደም ድረስ ሊጠቀሱ የሚችሉ ሲሆን አስፈላጊ ካልሆኑ /non essential/ እና አግባብነት ከሌላቸው /immaterial/ ፍሬ ነገሮች መለየት ያለባቸው ናቸው፡፡

በአጠቃላይ በውሳኔ ውስጥ ከጭብጥ በፊት፣ ከጭብጥ በኋላ እና ከጭብጥ ጋር የተያያዙ ፍሬ ነገሮች ሊገለፁ ይችላሉ፡፡ የሚፃፉ ፍሬ ነገሮች በማስረጃ ቃል የተቀመጡ፣ የተመረጡ፣ አስፈላጊ ብቻ የሆኑ፣ በቅደም ተከተላቸው የተቀመጡ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

ዳኛ ውሣኔውን በሚጽፍበት ጊዜ የሚፅፈው ውሳኔ ከዚህ በላይ የተገለፁትን ነጥቦች መያዙን በቼክ ሊስት ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ምንም እንኳን ዳኛው ያለው ጊዜ እና የጉዳዩ ብዛት የሚወስነው ቢሆንም የውሣኔውን ይዘት በዚሁ ቼክ ሊስት ማረጋገጥ፣ ማርቀቅ፣ መከለስ፣ ማንበብ፣ወዘተ የመሳሰሉትን መፈፀም ይጠቅማል፡፡ በመጨረሻም ተደጋግሞ መገለጽ ያለበት ውሣኔው በራሱ ገላጭና አስረጅ መሆኑንም ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ እንደሌሎች መፃሐፎች በዲክሽነሪ፣ በማጣቀሻ መፃሐፍ፣ በግርጌ ማስታወሻ፣ ወዘተ እንዲሁም በንባብ ወዲህና ወዲያ የሚያንገላታ አለመሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

ሐ) <u>ጭ ብ ጥ</u>

ጭብጥ ተከራካሪ ወገኖች ያልተስማሙበትና የፍርድ ቤቱን ውሣኔ የሚጠይቅ ነጥብ ሲሆን የፍሬ ነገር ወይም የሕግ አለዚያም የሁለቱም ጥያቄ ሆኖ የሕግ ምላሽ የሚጠይቅ ነው፡፡ ስለዚህ እንደ ሌሎች ፅሑፎች ሁሉ ጭብጥም በግልጽ ቋንቋ መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

ጭብጥ አንደየዳኛው አገላለጽ የሚቀመጥ ሆኖ፡-

- በጥያቄ መልክ ወይም
- ስለመሆን / አለመሆኑ /
- ስለመኖር / አለመኖሩ ወዘተ... በሚል ዐረፍተ ነገር ሊቀመጥ ይችላል፡፡

<u>ለምሳሌ</u> ፡-

- በፍ/ቤቱ ሊመረመር የሚገባው ጭብጥ
  - ⇒ «የከሣሽ ክርክር በይርጋ ቀሪ ሊሆን ይገባል?» ወይም
  - ⇒ «የከሣሽ ክርክር በይርጋ ቀሪ ስለመሆን አለመሆኑ ነው፡፡» ተብሎ ሊመዘገብ ይችላል፡፡ በዚህ ጊዜ ምላሽ የሚያስፈልገው ጭብጥ የሕግ እና የፍሬ ነገር ሆኖ መቋጫው የሕግ ጥያቄ የጊዜ ውጤትን የተመለከተው ይሆናል፡፡

ጭብጥ በርካታ ሊሆን ይችላል፡፡ የሕግ እና የፍሬ ነገር የተቀላቀለበት እንዲሁም በአንድ ጭብጥ ውስጥ ንዑስ ጭብጦች የተካተቱበት ይሆናል፡፡

<u>ለምሳሌ</u>፡-

1. ከሣሽ እና ተከሣሽ የፀና የጋብቻ ውል አላቸው?
   1.1. ካላቸው ጋብቻው የተፈፀመበትን ቀን መቼ ነው?
2. ጋብቻው ሊፈርስ አይገባውም በማለት ተከሣሽ ያቀረበው ክርክር የሕግ መሠረት አለው?
3. ጋብቻው በፍርድ የሚፈርስ ከሆነ ፡-
   3.1. የታርጋ ቁጥር...የሆነው መኪና የተከሣሽ የግል ነው?
   3.2. የቤት ቁጥር...የሆነው የከሣሽ እና ተከሣሽ የጋራ ንብረት ነው?

እየተባለ ሊቀመጥ ይችላል፡፡

የጭብጥ አቀማመጡም ቅደም ተከተል ይህንና ጊዜን መሠረት ማድረግ ይኖርበታል፡፡ የሕግ ጭብጦች በመጀመሪያ ምላሽ ቢያገኙም ይመረጣል፡፡ እያንዳንዱ ጭብጥ ዋና እና ንዑስ ጭብጦችን የያዘ ነው፡፡ ሆኖም ግን እንደ ሁኔታው ሁሉም ምላሽ ላያስፈልጋቸው ይችላል፡፡

<u>ለምሳሌ</u>፡-

- ከላይ በተገለፀው ምሳሌ ላይ «ከሣሽና እና ተከሣሽ የፀና ጋብቻ የላቸውም» የሚል መደምደሚያ ላይ ፍ/ቤቱ ከደረሰ ቀሪ ጭብጦችን በመተቸት በውሣኔ ላይ መፃፍ እና ጊዜ ማጥፋት አያስፈልግም፡፡

መ) <u>ሕግ እና ምክንያት</u>

በውሣኔው ላይ ጭብጥ ከተገለፀ በኋለ የሚከተለው ለጭብጡ ምላሽ ለመስጠት አግባብ ያለው **ሕግ** እና ሕጉ ከጭብጡ ጋር ያለውን ግንኙነት የሚያሳይ **ምክንያት** ነው፡፡ ሕጉን እንዳለ መገልበጥ ሁልጊዜ አያስፈልግም፡፡

<u>ለምሳሌ</u>፣-

- የኢትዮጵያ ሕግ «**ክርክሩ በ2 /ሁለት/ ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ ቀሪ ይሆናል**፡፡» በማለት ይደነግጋል ተብሎ ሊገለጽ ይችላል፡፡

የሚጠቀሰው ሕግ የተሻረ ካልሆነ በስተቀር ሕግ ምንጊዜም በአሁን ጊዜ መገለጽ አለበት፡፡ በሕግ ጥያቄ የሚደረስበት መደምደሚያ የፍሬ ነገርን መደምደሚያ መሠረት ያደረገ ነው፡፡ በፍሬ ነገር ላይ የሚደረስበት ድምዳሜ በዳኝነት ነፃነት ላይ የተመሠረተ ሳይሆን የቀረበን ማስረጃ መሠረት ያደረገ ነው፡፡ ይህ በራሱ የመጨረሻ የሚሆን ሳይሆን ለሕግ ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት መነሻ ነው፡፡

የሕግ ጥያቄ ምላሽ በሚሰጥበት ጊዜ የተባለውን ሕግ ሙሉ ቁጥር /አንቀጽ/ መገልበጥ ላያስፈልግ ይችላል፡፡ ልዩ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ መልኩ ሕጉ ባይገለበጥ ይመረጣል፡፡ የፍሬ ነገር ጥያቄ ትርጉም ያለው የሕግ ውጤት የሚኖረው በዚህ ጊዜ ነው፡፡ ህግ የተከራካሪ ወገኖች መብት ውሣኔ የሚያገኝበት በመሆኑ ከፍሬ ነገር ጋር ትስስሩ በግልጽ ተመልክቶ ነገር ግን በአንድ ዓረፍተ ነገር ከፍሬ ነገር በነፃ መልኩ መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

<u>ለምሳሌ</u>፡-

- የፍሬ ነገር መደምደሚያ
  - ተከሣሽ የውሉን እንቁላል በጥር አጋማሽ 2000 አላስረከበም፡፡
- የህግ መደምደሚያ
  - ጥር አጋማሽ 2000 ባለማስረከቡ ውል አፍርሷል፡፡

ፍ/ቤቱ የሕግ መደምደሚያው ላይ ሲደርስ ፍሬ ነገሩን መሠረት በማድረግ ለጉዳዩ ተገቢ ነው ያለውን ሕግ ሲፈልግ ለጉዳዩ በጥቅሉ እና ለተያዘው ጉዳይ በተለይ የሚፈፀም መሆኑን መርምሮ ነው፡፡ ይህ ሰፊ ሥራ የሕግ ጥናትን የሚጠይቅ ነው፡፡

በመጨረሻም የሕግ እና ምክንያት ትንተና ከተቋጨ በኋላ የፍርድ ቤቱ ውሣኔ ይገለፃል። ውሣኔ በተቻለ መጠን፡-

- አጭር እና ለአፈፃፀም የሚመች መሆን አለበት።
- ግልጽ እና ምጥን ቃል የሚጠቀም መሆን አለበት።
- ሁሉም ወገኖች የሚገባቸውን እና የማይገባቸውን በቀጥታ የሚናገር መሆን አለበት።

<u>ለምሳሌ</u>፡-

- ከፍ ሲል በተገለፀው መሠረት **ከሣሽ ክሱን ያቀረበው ውሉ ከፈረሰ ከሁለት ዓመት በኋላ በመሆኑ ክስ የማቅረብ መብት የለውም** ተብሎ ሊፃፍ ይችላል።
- የበለጠ የሚገልፀውም ከሆነ **ከሣሽ ክሱን ያቀረበው ውሉ ከፈረሰ ከሁለት ዓመት በኋላ በመሆኑ ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል** ሊባል ይችላል።

ከውሣኔው ጋርም ተያይዞ ተፈፃሚ መሆኑ የሚገባቸው ጉዳዩች ሊካተቱ ይችላሉ።

<u>ለምሳሌ</u>፡-

- ከሣሽ አላግባብ ክስ በማቅረቡ ተከሣሽን ለወጭ እና ለኪሣራ ለዳረገበት ..... ካሣ ይክፈል፣
- በዚህ ውሣኔ ቅር የተሰኘ ወገን የይግባኝ መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው፣
- መዝገቡ የተዘጋ በመሆኑ በቋሚነት ስለሚቀመጥበት ቦታ ሊወሰን ይችላል። ይህ ውሣኔ ብዙውን ጊዜ ትዕዛዝ በሚል ርዕስ ስር ሲቀመጥ እንመልከታለን።

11.5.2.<u>ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት</u>

በፍ/ቤቶች አወቃቀር የበላይ የሆኑ ፍ/ቤቶች ዋነኛ ተግባራቸው በሥር ፍ/ቤት የታዩ ጉዳዮችን በይግባኝ መመልከት ነው። በወረዳ ፍ/ቤቶች የቀጥታ ክስ ክርክሮች የሚበዙ ሲሆን በበላይ ፍ/ቤቶች በይግባኝ የሚታዩት ጉዳዩች እየበዙ ይመጣሉ። ይህ ማለት ግን በወረዳ ፍ/ቤት ይግባኝ አይታይም በጠቅላይ ፍ/ቤቶች ደግሞ ቀጥታ ክስ አይታይም ማለት አይደለም። መጠኑ እና የሚጠበቀው ውጤት ይለያያል እንጂ በሁሉም ፍ/ቤቶች ይግባኝ ይታያል።

ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት አንድን ጉዳይ በይግባኝ በሚመለከትበት ጊዜ በዋነኛነት የክለሳ ተግበር ያከናውናል፡፡ በዚህም መሰረት፡-

- የሥር ፍ/ቤት የሥነ ሥርዓት ሕጉን በአግባቡ መፈፀሙን፣
- መሠረታዊ ሕጐች አለመጣሳቸውን፣
- ማስረጃ በአግባቡ መመዘኑን ያረጋግጣል፡፡

ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የመጨረሻ በሆነ ጊዜ ወይም ጉዳይን በሰበር የሚያይ ከሆነ ይህ ፍ/ቤት፡-

- የሕግ ስህተት አለመፈፀሙን ያረጋግጣል፡፡
- አትኩረቱ በሕግ ጥያቄዎች ላይ ሆኖ
  - ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌዎች አለመጣሳቸውን
  - ፖሊሲዎች እና ሌሎች ሕጐችም በመሠረታዊነት አለመጣሳቸውን በማረጋገጥ በክልሎች ወይም በሀገሪቱ ተመሳሳይ እና ተገማች የሆነ የሕግ ሥርዓት መኖሩን የማረጋገጥ ተጨማሪ ከባድ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት እነዚህን ተግባሮች ለመፈፀም በአብዛኛው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትን የመዝገብ ግልባጭ /record/ ይመረምራል፡፡ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የዳኝነት ተግባሩን በአብዛኛው በንብረት የሚያከናውን ይሁን እንጂ በሀገራችን የውሣኔ አፃፃፍ ሥርዓት የፍ/ቤት ውሣኔ የምንለው በአንድ ዳኛ ተጽፎ በችሎቱ ላይ በተሰየሙት በሁሉም ዳኞች የሚፈረምበት ነው፡፡ በዚህም መሰረት ውሣኔውን የሚጽፈው ዳኛ፡-

- የራሱን ብቻ ሳይሆን የሥራ ባልደረቦቹ ሊያደርጉ የሚፈልጉትን ጥንቃቄ መረዳት ይኖርበታል፡፡
- ፅሁፉ የአንድ ዳኛ ውሣኔ ሳይሆን ከፍሬ ነገርም ይሁን ከሕግ የተጨመቀ የጋር የአእምሮ ውጤት መሆኑን ማሳየት ይገባዋል፡፡

በሌላ በኩልም በውሣኔው የሚስማማ ነገር ግን የተለየ ምክንያት መቀመጥ ይገባዋል የሚል ሃሳብ ሊኖር ይችላል፡፡ እነዚህ ልዩነቶች፡-

- መፃፋቸው ለዳኝነት ሥርዓቱ አቋም መጠናከር አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ቢፃፉ ይመረጣል፡፡
- ሲፃፉም አብዛኛውን ዳኛ በግል የሚመለከቱ ሁነው ሳይሆን የችሎትን ውሣኔ ብቻ በሚመለከት መሆን አለባቸው፡፡

- ሲፃፉ ትችት እና ወቀሳ ያዘሉም መሆን የማይገባቸው ሆኖ በክርክሩ ላይ የተሰማውን ጭብጥ ብቻ ማዕከል ያደረጉ መሆን አለባቸው፡፡
- ሲፃፉ በተቻለ መጠን ልዩነቱን የሚያሰፍር ዳኛ ልዩነቱን ብቻ ሳይሆን ቢቻል ምጥን ባለ አገለላጽ ከሌሎች ባልደረቦቹ ጋር የሚስማማባቸው ነጥቦች እንዳሉ እነዚህን ነጥቦች ጭምር ቢገልፅ ይመረጣል፡፡

የአንድ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ዋና ተግባር በሥር ፍ/ቤት የውሣኔ አሰጣጥ እና አካሄድ ላይ የተከሰቱ ስህተቶችን ማረም ነው፡፡ በዚህ ረገድ በሥር ፍ/ቤቶች በርካታ ስህተቶች ተፈጽመው ሊገኙ ይችላሉ፡፡ የተወሰኑት ተከራካሪ ወገኖች ላይ ጉዳት የማያደርሱ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

<u>ለምሳሌ</u>፡-

- ከሣሽ 10X10 =100 ብር ይገባኛል በማለት የጠየቀውን ፍ/ቤቱ 5x20 = 100 ብር ይገባዋል ብሎ ቢወስን እንደማለት ነው፡፡

የዚህ ዓይነት ስህተቶች በተለይ ከሀገራችን የሙግት መብዛት ጋር ተያይዞ ፍትህን የማያዛቡ ሊሆኑ ስለሚችሉ በይግባኝ ላይታረሙ ይችላሉ፡፡ ለዚህም ነው ብዙ ጊዜ የይግባኝ ፍ/ቤቶች ውሳኔ ሲወስኑ ስህተት አልተፈፀመም፣ ስህተት ቢፈፀምም ጉጂ አይደለም፣ ስህተት ቢፈፀምም በመሰረታዊነት መብትን የሚጋፋ አይደለም ... ወዘተ በማለት ሲወስኑ የሚታዩት፡፡

ሆኖም ግን ስህተቱ ግልጽ እና አንድ ፍ/ቤት በመሠረቱ ሊከተለው የሚገባውን አቅጣጫ የሳተ ሆኖ ሲገኝ መታረም ግድ ይለዋል፡፡

<u>ለምሳሌ</u>፡-

- ከሳሽ 10X10=100 ብር ይገባኛል በማለት የጠየቀውን ፍ/ቤቱ 10X100= 1000 ይገባዋል ብሎ ቢወስን ይህ ስህተት መታረም ያለበት ነው፡፡

የይግባኝ ውሣኔ ይዘት ከፀሐፊ ፀሐፊ ሊለያይ ቢችልም በጥቅሉ

- የጉዳዩ ዓይነት
- ጭብጥ
- ፍሬ ነገር
- የተገኘው ስህተት /የሕግ ትንታኔ፣ ምክንያት/

- ማጠቃለያ /disposition/ ይኖረዋል፡፡

የይግባኝ ውሳኔ ይዘት የሆኑት የጉዳዩ ዓይነት፣ ጭብጥ፣ ፍሬ-ነገር፣ የህግ ትንታኔ እና ምክንያት የሚባሉት በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሚፃፉበት ሥርዓት ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው ናቸው፡፡ ሆኖም ግን በዚህ ክፍል ውስጥ የሚገኘው ማጠቃለያ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ላይ ከሚፃፈው ማጠቃለያ የተለየ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በዚህም መሰረት፡-

- በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348/1/ መሰረት ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በይግባኝ የቀረበለትን ውሣኔ ለማጽናት፣ ለማሻሻል፣ ለመለወጥ፣ ወይም ለመሻር መቻሉ
- በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 341 እና 343 መሠረትም ጭብጥ አስተካክሎ ወይም ክርክር ተደርጐ ውሣኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን ለበታች ፍ/ቤት መመለስ መቻሉ
- በተመሳሳይ መልኩ የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 195 መሠረት ይግባኙን የማጽናት፣ ጉዳዩን ሌላ ፍርድ ቤት እንዲመለከተው የማዘዝ፣ ውሣኔውን ሙሉ በሙሉ የመሻር፣ ቅጣትን የመጨመር፣ ቅጣትን የማጽናት፣ ቅጣትን የመቀነስ ሥልጣን የተሰጠው መሆኑ የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ይግባኙን ከመረመረ በኋላ አቋሙን የሚገልጽበት ማጠቃለያ እንደሆነ ያሳየናል፡፡

በአጠቃላይ በየትኛውም ፍ/ቤት የሚሰጥ ፍርድና ውሳኔ ሊይዛቸው የሚገቡ ነገሮች፡-

- የመዝገቡን ገፅ፣
- የመዝገቡን ቁጥር፣
- ፍርዱና ውሳኔው ይፋ የተደረገበትን ቀን
- ጉዳዩ የታየበትን ቀን፣
- የዳኞችን ስም፣
- የከሳሹን ማንነት፣
- የተከሳሹን ወይም የጠበቃውን ስም፣
- ፍርድ፤ በፍርድ ሥር ሊኖሩ የሚገባቸው ጉዳዮች፡-
  - የከሳሽ ክስ ወይም አቤቱታ በአጭሩ
  - ክሱን ወይም አቤቱታውን ለማስረዳት የቀረቡ ማስረጃዎች ጠቅለል ተደርገው
  - ተከሳሽ ለቀረበበት ክስ ወይም አቤቱታ የሰጠው መልስ
  - ክሱን ወይም አቤቱታውን ለመከላከል ያቀረባቸው ማስረጃዎች ጠቅለል ተደርገው
  - ክሱ ወይም አቤቱታው በተሰማባቸው ቀኞች የተደረጉ ልዩ ልዩ ክርክሮች
  - የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ቀርቦ በሱ ላይ የተሰጠ ብይን ወይም ውሳኔ ካለ እሱን በአጭሩ

- ❖ ጭብጥ
- ❖ ማስረጃዎችን መመርመር
  - ⇒ ማስረጃው ተቀባይነት ያገኘበት ምክንያት፣
  - ⇒ ማስረጃው ተቀባይነት ያላገኘበት ምክንያት፣
- ❖ ፍርዱ መሠረት ያደረገውን የህግ ቁጥር፣
- ❖ ጥፋተኛ ያስኘውን ህግ፣
- ❖ ቅጣትን ለማክበድ እና ለማቅለል የተሰጡ አስተያየቶች፣ /በወንጀል ጉዳይ/
- ❖ ይህንኑ ለማስረዳት የቀረበ ማስረጃ፣

➢ ውሳኔ /ቅጣት/፤ በውሳኔ ሥር ሊኖሩ የሚገባቸው ጉዳዮች፡-

- ❖ በውሳኔ ላይ ሊፈፀም የሚችል ነገር በአጭሩ የሚገለፅበት ነው፡፡
- ❖ በፍትሃ ብሄር ጉዳይ የተከራካሪ ወገኖች መብትና ግዴታ ይገለፃል፡፡
- ❖ በወንጀል ጉዳይ የተጣለው የቅጣት ዓይነት ይገለፃል፡፡
- ❖ ወጭና ኪሳራ ተጠይቆ ከሆነ በውሳኔ ላይ ይገለፃል፡፡

➢ ትዕዛዝ፤ በትዕዛዝ ሥር ሊኖሩ የሚገባቸው ጉዳዮች፡-

- ❖ አስተዳደራዊ የሆኑ ትዕዛዞች በትዕዛዝ መልክ ይቀመጣሉ፡፡
  - ⇒ የጊዜ ገደቡን ጠብቆ ይግባኝ ለጠየቀ ወገን ይግባኙ ተገልብጦ ይሰጠው፡፡
  - ⇒ መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡
- ❖ በወንጀል ጉዳይ ላይ ስለቅጣቱ አፈፃፀም

➢ በመጨረሻም ምንም ዓይነት ርዕስ ሳይሰጠው

- ❖ የይግባኝ መብት ያለ መሆኑ መፃፍ አለበት፡፡/ቁጥር 149/
- ❖ ፍርድና ውሳኔ የሰጡት ዳኞች ፊርማ

12. <u>በፍ/ቤቶቻችን በሚሰጡ ፍርዶች ላይ የሚታዩ ችግሮች</u>

በፍ/ቤቶቻችን በስፋት የሚሰጡ ፍርዶችን ስንመለከት፡-

➢ ለውሣኔ የሚሰጡ ስያሜዎች ወጥ ያለመሆን፣

- ❖ ውሳኔ ብሎ ጀምሮ መጨረስ
- ❖ ፍርድ ብሎ ጀምሮ መጨረስ
- ❖ ውሳኔ ብሎ ጀምሮ ትዕዛዝ ብሎ መጨረስ
- ❖ ፍርድ ብሎ ጀምሮ ትዕዛዝ ብሎ መጨረስ

❖ ፍርድ ብሎ ጀምሮ ውሳኔን አስከትሎ በትዕዛዝ መቋጨት... ወዘተ

- በሕጉ ላይ ያልተመለከቱ ቃላትን መጠቀም፣

  <u>ለምሳሌ</u>፡-

  ❖ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህጉ ላይ **ብይን** የሚል ቃል ሳይኖር በሁሉም ፍ/ቤቶች ማለት ይቻላል ተከሣሽን ተከላከል ወይም አትከላከል በማለት የሚሰጡ ውሣኔዎች በሙሉ **በብይን** ይፃፋሉ፡፡

- አንድ ፖራግራፍ አንድ ዐ/ነገር የሆነበት አጋጣሚ ብዙ ነው፡፡ በአጭር ዐረፍተ ነገር የመፃፍ ልምድ አይታየባቸውም፡፡ መንዛዛት ይበዛባቸዋል፡፡
- ግልጽ ያልሆኑና የውጭ ቋንቋን የሚጠቀሙ፣
- በስሜት የሚፃፉ፣
- በአጭሩ የተቀመጡትም ሆነ ያለግባብ የረዘሙት ውሣኔዎች በውሣኔያቸው መዳሰስ ያለበትን ነጥብ ሁሉ ያልዳሰሱ መሆን ይታይባቸዋል፡፡
- ታዋቂ ያልሆኑ ምዕረጻ-ቃላትን መጠቀም

  <u>ለምሳሌ</u>፡-

  ❖ ማ/ቤት (ማዘጋጃ ቤት ወይስ ማረሚያ ቤት?)

  ❖ የመ/ምስክርን ወይም የመ/ም (የመከላከያ ምስክር ወይስ የመልስ ሰጭ ምስክር?)

  ❖ ወ/ል (...?)

  ❖ የተ/ጠበቃ ወይም የተ/ጠ (የተማሪ ጠበቃ፣ የተከላካይ ጠበቃ ወይስ የተከሳሽ ጠበቃ?)

- በራስጌያቸው የፍርድ ቤቶችን ስም በግልጽ አለማሳየት፣
- አንዳንዶቹ ወደ ጥፋተኛነት ያጋደሉ፣ በግልጽ የውስጥ ስሜት የተንፀባርቀባቸው መሆናቸው፣
- አጥፊን ከማስረጃ በላይ የሚኮንኑ፣ በሕጉ ከተቀመጠው ቃል በላይ የሚሳደቡ፣ ስብዕናንና ክብር የሚጐንጡ መሆናቸው፣

  <u>ምሳሌ</u>፡-

  ❖ በአንድ ጉዳይ ተከሳሹ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁጥር 656(ሀ) እና 658(መ) ላይ የተመለከተውን ተላልፎ በእጁ የገባውን የቀበሌ የህብረት ሱቅ ቼክ የኃላፊውን ፊርማ በማስመሰል ፈርሞ ገንዘቡን አውጥቶ ለግል ጥቅሙ አውሎታል ተብሎ በማታለል ወንጀል ተከሶ ተመስክሮበታል፡፡ ፍ/ቤቱ

በፍርዱ ውስጥ ክሱንና ማስረጃውን የተከሳሹን ዕምነት ከገለፀ በኋላ ሀተታውን ሲያሰፍር ተከሳሹ የህብረት ሱቁን ኃላፊ ፊርማ አስመስሎ ማውጣቱ ማታለል ነው ቢባልም አድራጎቱ ሲታይ ግልፅ ዘረፋ እንጅ የተለየ ትርጉም የሚሰጠው አልሆነም፡፡ ተከሳሹ በቀበሌው ተቀጥሮ የሚሰራ ሲሆን የሚኖረውም በዚሁ ቀበሌ ውስጥ መሆኑን አረጋግጦ ሲሆን የቀበሌው ኗሪ ህዝብ መገልገያ የሆነውን የህብረት ሱቅ ማራቆቱ ሲታይ የፈፀመው ጥፋት ገንዘብ አጭበርብሮ መውሰዱ ብቻ ሳይሆን የቀበሌው ህዝብ ከህብረት ሱቁ የሚገኘውን ፈጆታ እንዳያገኝ ችግር ላይ የጣለ ለራሱ የዕለት ደስታ ብቻ የቆመ፣ ራሱን ወዳድ፣ የአጥፊዎች አጥፊ ቢባል ከእውነት የራቀ አይደለም፡፡ ይህ ተከሳሽ ክሱ ደርሶት ሲጠየቅ ገንዘቡን ከጓደኞቹ ጋር ጨፈርኩበት በማለት በችሎቱ ሲናገር ሀፍረት ያልተሰማው ... የቀበሌው ኗሪ ህዝብ ተስፋ ቆርጦ በፍታብሄር በኩል የተከሳሽን ንብረት እንዳይፈልግ ተስፋ ለማስቆረጥ ሆን ብሎ የተናገረው ቃል ነው የሚልንም ጥርጣሬ የሚያሳድር በመሆኑ መንግስት ከቀበሌው ኗሪ ጎን በመቆም ተከሳሹ ገንዘቡን ያዋለበትን ተግባር ሊከታተለው እንደሚገባ ፍርድ ቤቱ ይጠቁማል... ተከሳሹ ያቀረበውን የማስመሰያ ፊርማ ባንኩ በሚገባ ሳያመሳክር ክፍያ መክፈሉ ኃላፊነቱንና ግዴታውን አልተወጣም ያሰኘዋል፡፡

- በፍርዶች ውስጥ በግልጽ ምላሽ የሚያስፈልገው ተብሎ የተለየ ጭብጥ ተይዞ አለመታየት፣
- ጭብጥ ተብሎ ተመዝግቦ የሚታየው የዐ/ህግ ምስክሮች እና የተከሣሽ የመከላከያ ምስክሮች የሚያስረዱት ፍሬ ነገር ብቻ ነው፣
- በግልጽ ቋንቋ ከመጠቀም ይልቅ በሕግ ቋንቋ ማደናገር ይታያል፡፡

  <u>ለምሳሌ</u>፡-

  - በወ/መ/ሕ/ቁ 85፣ 86 79/1/ሀ/፣ 40፣ 205፣ 207 ወዘተ መሠረት ተብሎ ብቻ ቅጣቱ ሲወሰን ይታያል፣
- የቀልድ፣ የምፀት፣ የስድብ እና ወገንተኝነትን የሚያሳዩ አባባሎችን መጠቀም፣

<u>የመወያያ ጥያቄ</u>

ቀጥሎ ያለውን የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ልጁን አስገድዶ ደፍሯል የተባለንና በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በ17 ዓመት ጽኑ እሥራት እንዲቀጣ የተፈረደበትን ይግባኝ

ባይ በነፃ እንዲሰናበት ሲወስን ያሰፈረውን ትችት ካነበባችሁ በኋላ ፍርዱ ያሉበትን ችግሮች አውጡ።

ፍ/ቤቱ ለክርክሩ ምላሽ የሚያስፈልጋቸው ሁለት ጥያቄዎችን ሲያወጣ ተበዳይ ነኝ ባይዋ ለፍ/ቤት ያስመዘገበችው ምስክርነት የሚታመን ነውን? ተከሣሹ በፍ/ቤት ያስመዘገበው ቃል እውነት ነውን? የሚሉት ጥያቄች መመለስ እንዳለባቸው ገልፆል። ለጥያቄዎቹ መልስ ሲሰጥም

«... ተበዳይ ነኝ ባይ መጀመሪያ የተደፈረችው በ1988 ዓ.ም መሆኑን እንዴት አወቀች? በኃይል የደፈራት መሆኑን እንዴት ተረዳች? አስገድዶ መድፈር ካለ መጮህ አለ፣ መጮህ ካለ ከውስጥም ከውጭም ሰው ይሰማል፣ ሰው ከሰማ ግርግር ይፈጠራል። ይህ ያልተከሰበት ምክንያት ምንድን ነው? ለእናቷ የመደፈሯን ነገር ያላሳወቀቻት እናት የደም ግፊት ሕመም ስላለባት ነው ብላለች። ለዚህ ማረጋገጫው የት አለ? ሁለቱ ሴት ልጆቹ ተበዳይ ነኝ ባይዋ ጭምር ዘወትር የሚተኙት ከእኔ ከአባታቸው ጋር ነበር ሲል ይግባኝ ባዩ አረጋግጧል፤ ተበዳይ ነኝ ባይዋ ፍርድ ቤት ፊት ቀርባ ስትመሰክር ግን «ተከሣሹ በተደጋጋሚ ወሲብ ይፈጽምብኝ የነበረው ወደ እኔ መኝታ ቤት እየመጣ ነበር ብላለች» የማንን አነጋገር ያምናል? የይግባኝ ባዩ አነጋገር ሐሰት ነው ያለ ተከራካሪም ሆነ ተመልካች የለም። «...የተከሣሽ ብልግና በድብቅ ለሦስት ዓመታት ያህል ሲፈፀም ቆይቶ ይፋ የወጣውና ሊገለጽ የቻለው ማህፀኔን ሲያመኝ ጊዜ ለእናቴ እህት ለአክስቴ ስለነገርኳት ነው» በማለት ተበዳይ ነኝ ባይዋ መስክራለች። በመጀመሪያው ቀን ሩካቤ ሥጋ ሲፈጽምባት ማኅፀኗን ለምን አላመማትም? የማህፀኗ መታመም የተከሰተው ተከሣሹ ስለደፈራት ነው? ወይስ በሌላ ምክንያት? ይችን ሰው ይግባኝ ባዩ አባቷ ይቆጣጠራት እንደነበር ተነግሯል። ይህም አልተካደም። ጥብቅ ቁጥጥር ያደርግባት የነበረው ማህፀን ከሚያሳምም ክፉ በሽታ ላይ የሚጥል የዋልጌነትና የብልግና ተግባር ትፈጽማለች ብሎ ጠርጥሮ ከሆነስ? እየተቆጣጠረ ከሚያስቸግረኝ መላ ልፈልግና እርሱን ወደ ከርቼሌ ሸኝቸ እኔ በነፃነት ልመላለስ ብላ አስባ እንደሁ ማን ያውቃል? የምትኖርበት ቤት ከአንድ መጠጥ ቤት ጋር የያያዘ መሆኑ ተበዳይ ነኝ ባዩዋ ራሷ አረጋግጣለች። አልፎ ተርፎም ተበዳይ ነኝ ባይዋ በ1988 ዓ.ም ዐ/ሕግና ተበዳይ ነኝ ባይ እንዳሉት የ14 ዓመት ሣይሆን የአሥራ አምስት ዓመት ወይዘሪት ስለነበረች ይህ የዕድሜ ደረጃ ላይ የሚገኙ ወጣቶች የሚሠሩትን የሚያሳጣቸው እሳት በጉያቸው ሸጉጠው እንደሚከንፉ የታወቀ ነው። ተቆጣጣሪና መካሪ ዘካሪ ካላገኙ ወይ ካላደመጡ።

በዚህ ሁሉ መሀል ያሻትን አድርጋ «ቤተሰቦቼ የቁጣ መዓት ከሚያወርዱብኝ ነጋ ጠባ አጥብቆ የሚቆጣጠረኝና የሚነዘንዘኝ አባቴ ደፈረኝ ብል ይህ ጥሩ ዘዴ ነው» የሚል ሐሳብ አእምሮዋ አርግዞ ወልዶ እንደሆነስ? እንዲህ ያለውን ከባድ ... ለእናቷ መንገር ነበር የሚቀልለው? ወይስ ለአክስቷ? ወሲብ ... ማህፀኗ የታመመው ከሦስት ዓመት በኋላ ያውም የወሲብ ተግባርን ያለስቃይ ማስተናገድ ተለማምዶ ሣለ አባቴ ወሲብ ይፈፀምብኝ ስለነበር አሁን ማህፀኔን አመመኝ ብላ ለአክስቷ ተናገረች ቢባል ይህ የሚታመን ነውን? የዚች ተበዳይ ነኝ ባይ ሴት ምስክርነት የሚጠረጠር ብቻ ሳይሆን ጨርሶ የሚታመን አይደለም እንላለን፡፡

ሁለተኛውንና የመጨረሻውን ጥያቄ እንመርመር ... ተከሣሹን በፖሊስ ጣቢያ ውስጥ ደብድቦና አሰቃይቶ ያልሆነውን ሆነ ያሰኘው መርማሪ ወደ ፍ/ቤት ተከትሎት መጥቶ በዓይን ጥቅሻ እና በከንፈር ንካሽ ልክ ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ በነገርከኝ ዓይነት ለፍ/ቤት ባታስመዘገብ ወዮልህ! ትገባታለህ! አይለውም አይባልም፡፡ መርማሪው ተከሣሹን ተከትሎ ፍርድ ቤት መቅረቡ አልተስተባበለም፡፡ ተከሣሹ ብርቱ ማስጠንቀቂያ ከመርማሪው ተቀብሎ እያለ፣ መርማሪው በችሎቱ ተገኝቶ ከተከሣሹ ጋር እየተያዬ ከንፈሩን እየነከሰበት ሣለ የሚያስታውሰው በፖሊስ ጣቢያ ውስጥ የተፈፀመበትን ሰቆቃ እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም፡፡ አሁንም ፍ/ቤት ውስጥ በፍርሃትና በሥጋት ተሞልቶ ያላደረገውን አድርጌያለሁ የማይልበት ምክንያት አይኖርም አይባልም፡፡ የተከሣሹን ቃል የሚመዘግቡት ዳኛ የሚመለከቱት ተከሣሹንና የሚጽፉበትን ወረቀት እንጂ ተከሣሹን የመረመረውን ወታደር አይደለም፡፡ ስለሆነም መርማሪው በዓይን ጥቅሻ በከንፈር ንክሻ ተከሣሹን ሲያስፈራራው ሊመለከቱት አይችሉም የሚል እምነት አለን፡፡ ፍ/ቤቱ የተከሣሹን ቃል ሲመዘግብ መርማሪውን አግልሎ በዝግ ችሎት ቢሆን ምንኛ መልካም ነበር፡፡ ይህ መፈፀሙን የሚገልጽ አንዳች ነገር አልቀረበም፡፡ ተከሣሹ ለፖሊስ የሰጠው ቃል እና ለፍርድ ቤት ያስመዘገበው ቃል በእጅጉ ተመሣሣይነት አለው፡፡ የቃላት ልዩነት እንኳ ብዙ የለበትም፡፡ ይህም መርማሪው ተከሣሹን «በጣቢያ የሰጠኸውን ሳትጨምር ሳትቀንስ ለፍ/ቤቱ ባትነግር ትገባታለህ» ሲል ዝቶበታል መባሉን ይበልጥ እንድናምን የሚያደርግ ነው፡፡ ... ዳኛ ፊት የተናገረው ሁሉ ትክክልና እውነት ነው ብሎ መቀበል የዋህነት ይመስለናል፡፡ ስለሆነም የሥር ፍ/ቤት ... ተከሣሹ ለፍርድ ቤቱ ያስመዘገበውና በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 35 መሠረት ተሰጠ የተባለው ቃል እውነት አይደለም ብለናል ፡፡... ይግባኝ ባዩ ጥፋተኛ እንዲባልና በ17 ዓመት ጽኑ እሥራት እንዲቀጣ መሠረት የሆኑት የዐ/ህግ ማስረጃዎች ባዶ ሆነው ስላገኘናቸው፣ በአጠራጣሪ ማስረጃ ላይ የተመሠረተ

ፍርድ ከመፍረድ አንድ ሺህ ወንጀለኞች ሳይፈረድባቸውና ሳይቀጡ ቢታለፉ ይሻላል ብለን ስለምናመን የሥር ፍ/ቤትን ... መሠረት ሸረናል፡፡ ቅጣቱንም ሠርዘናል፡፡ ... ሁነኛ ማስረጃ አልቀረበበትም ብለን በነፃ ... በማለት አትቷል፡፡

(ከወንበር መጽሔት የተወሰደ)

- አንድን ሐሳብ በበርካታ ቃላት ለመግለጽ መሞከር

  ምሳሌ፡-

  - በደንብ መታየት፣ መመርመር፣ መጣራትና መመዝን ያለበት ጉዳዩ
- የግል ግንዛቤ ከማስረጃ በላይ በፍርድ በጉልህ ጥቅም ላይ ሲውል ይታያል

  ምሳሌ፡-

  - በማስረጃነት የቀረበን ማስረጃ ፍ/ቤቱ አስቀድሞም ቢሆን ዋጋ የሌለው መሆኑን ያወቀ መሆኑን በውሳኔው ላይ መመዝገብ
- ማስረጃ የተመዘገበበት አግባብ ግልጽ አለመሆን፣
- የሰነድ ማስረጃ እያለ ሳይተች ማለፍ፣
- የተከሣሹ ስም፣ ማዕረግ ... ወዘተ አለመመዝገብ / አቶ ፣ ወ/ሮ፣ መቶ አለቃ... /
- አንድን ሰው በተለያየ መልኩ መግለፅ

  ምሳሌ፡-

  - አንዱ «ብለዋል» ሌላ ጊዜ «ብሏል»፣
  - አንዱ «የዐ/ሕግ ምስክር» ሌላ ጊዜ «የሕግ ምስክር»
- አብዛኛው ውሳኔ ከክስ አንስቶ ማስረጃ የሚገለበጥበትና የመዝገብ ምትክ የሚመስል መሆኑ፣
- የማስረጃ እና የህግ ትንታኔ የሚያንሳቸው መሆን፣
- ክሱን በአግባቡ መርምረናል ከሚሉ በቀር ምርመራውን በቅደም ተከተል የማያሳዩ መሆን፣
- የቅደም ተከተል ችግር ያለባቸው መሆን፣
- በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቶች የሚፃፉ ውሣኔዎች አልፎ አልፎ በማጠቃለያ ላይ መስፈር ያለባቸው ጉዳዮች በመንደርደሪያ ላይ ሰፍረው መገኘታቸው፣

  ለምሳሌ:-

- ❖ አንድ ፍ/ቤት በፍርዱ መንደርደሪያ ላይ መፃፍ ሲጀምር የቀረቡትን ሁለት መቃወሚያዎች አልተቀበልናቸውም፤ ምክንያቱም ... በማለት ፅሁፉን ቢጀምር ማጠቃለያው ከመንደርደሪያውና ከሌሎች ተከታይ ነገሮች ቀድሞ ተገኘ ማለት ነው፡፡
  - ⇒ ይህ የውሣኔ አፃፃፍ አንባቢ ንባቡን መቀጠል ያለበት መሆን አለመሆኑን ለመለየት የሚጠቀም ቢሆንም ተመራጭ አይደለም፡፡
  - ⇒ ምክንያቱም አንባቢ ሙሉውን የፍ/ቤት ውሣኔ የማንበብ ፍላጐት ከሌለው ይህንኑ በስተመጨረሻ ያለውን ጹሑፍ በማንበብ የውሳኔውን አጠቃላይ ሀሳብ ሊያገኘው ይችላል፡፡
  - ⇒ አፃፃፉም ፍ/ቤቱ ውሣኔ ሰጥቶ ምክንያት ብቻ የፈለገ የሚያስመስል በተገላቢጦሽ ውሣኔው በፍሬ ነገር እና ትንተና ላይ ያልተመሠረተ የሚያስመስል ነው፡፡
  - ⇒ ስለሆነም የዚህ ዓይነት የውሣኔ አፃፃፍ የሚመረጥ አይደለም፡፡

- ➢ ሃሳብ ተደጋግሞ የሚመዘገብባቸው፤
- ➢ የፊደላት ተስተካክሎ አለመፃፍ፣ የቦታዎች አለመመዝገብ፣ የሰዎች በትክክል አለመመዝገብ፣
- ➢ ክሱ ላይ ከሰፈረው በቀር በውሳኔው ላይ ወንጀል የተፈፀመበትን ቦታ አለመግለፅ፣
- ➢ የዐ/ህግ ምስክርነት፣ የተከሣሽ ምስክርነት እየተባለ ለክርክሩና ለአካባቢው ግድየለሽ በሚያስመስል መልኩ መመዝገብ
- ➢ ሰነዶች በአግባቡ አለመጥቀስ

<u>ለምሳሌ</u>፡-

- ❖ በአስገድዶ መድፈር ጉዳይ የቀረበን የሕክምና ማስረጃ ማን እንደሰጠው፣ ምን እንዲሚያስረዳ፣ ደብዳቤው ወጭ የሆነበትን ቀን፣ ቁጥር፣ የሰነዱን ይዘት አለመግለፅ
- ❖ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁጥር 35 የተሰጡ የዕምነት ቃሎች መኖራቸው በፍርዶቹ ውስጥ ቢጠቀስም ማን እንደተቀበላቸው እና፣ መቼ እንደተሰጡ አለመግለፅ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

11. <u>ውሣኔ አፃፃፍ እና ሥነ ምግባር</u>

ውሣኔ ሰጭዎች ሕግን የመተርጉም እና ሕግን የመፈፀም ተግባራቸውን ገለልተኛ፣ ፍትሐዊ እና ግልጽ በሆነ መንገድ መወጣቸውን እንዲሁም በሕግ አውጭው እና በሕብረተሰቡ ያለባቸውን ተጠያቂነት ከሚወጡበት መንገድ አንዱ በአሳማኝ ምክንያት ላይ የተደገፈ ውሣኔ መፃፍ ነው፡፡ ጥሩ ውሣኔ ለመፃፍ ከሚያስፈልጉ ቁምነገሮች ውስጥ አንዱ የሥነ ምግባር ደንቦች በውሣኔ ፅሁፍ ውስጥ በአግባቡ መጠበቃቸውን ማረጋገጥ ነው፡፡ ይህንን ለመፈፀም በመጀመሪያ ደረጃ የፅሁፉ ታዳሚ /audience/ ማን እንደሆነ ለይቶ ማወቁ ያስፈልጋል፡፡

ዳኞች ውሣኔ ሲጽፉ ውሣኔውን በማንበብ የሚታደሙ በርካታ እና የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች እንደሆኑ ልብ ማለት ይገባቸዋል፡፡ የአንድ ውሣኔ ታዳሚ ሊሆኑ ከሚችሉት ውስጥ፡-

- ውሣኔውን የሚጽፈው ዳኛ ራሱ፣
- የውሣኔው ፈራሚ ዳኞች፣
- የሥራ ባልደረባ ዳኛ / ዳኞች /
- የሙያ /የሕግ/ ማኅበር፣
- የሕግ ትምህርት ቤቶች፣ ሥልጠና ማዕከላት፣
- በጉዳዩ ላይ ያገባናል የሚሉ ወገኖች፣ / ምሳሌ ሴቶች ማኅበር /፣
- ሕብረተሰቡ በአጠቃላይ፣
- ሕግ አውጭውና የመንግሥት አካላት፣
- አገር አቀፍ እና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች፣
- ሚዲያዎች፣
- ኤምባሲዎች፣
- የመላው ዓለም በኢንተርኔት ዌብ ሳይት ወዘተ የሚታደሙት መሆኑን ማስተዋል ተገቢ ነው፡፡

ውሣኔ ሰጭዎች ሥነ ምግባራቸውን ሊጠብቁ የሚገባው በፍ/ቤት እና ከፍርድ ቤት ውጭ በንግግራቸው፣ በአኳኋናቸው እና በፅሁፋቸው ነው፡፡ ዳኞች የሚፅፉት ውሣኔ ሊታመን የሚችለው ውሳኔውን የሚፅፈው ዳኛ ገለልተኛ ስሜት ያለው፣ ክብሩን የጠበቀ፣ ጉዳዩ ከሚፈጥረው ስሜት የራቀ መሆኑን በሚፅፈው ውሳኔ ማረጋገጥ ሲችል ነው፡፡

የዳኞች የመጨረሻ ተግባር አለመግባባትን በውሣኔ መቋጨት ነው፡፡ በሀገራችን የፍትህ ሥርዓት ክርክሮች እና አለመግባባቶች በፍ/ቤት ሲቋጩ በፅሁፍ መሆን እንዳለባቸው ህጐቻችን በአስገዳጅነት ደንግገዋል፡፡ የፍ/ቤት ውሣኔ በፅሁፍ መስፈሩ የፍ/ቤቶች የግንኙነት አድማስ ከሁሉም የሕብረተሰብ ክፍሎች ጋር የሚሆንበትን ዕድል ያሰፋል፡፡ በሁሉም ግንኙነቶች የዳኞች ውሣኔ በባለጉዳዮች እንዲሁም በሕብረተሰቡ ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድረው የተደረሰበት መደምደሚያ ብቻ ሳይሆን ውሣኔዎች እንዴት እንደተፃፉም ጭምር ነው፡፡ ከፍ/ቤት ውጭ ያለ ታዳሚ ዳኞችን የሚዳኙቸው በውሣኔያቸው ላይ በሚያሰፍሩት በዚሁ ፅሁፍ ነው፡፡

በጥሩ ሥነ ምግባር የታነፀ ዳኛ ጥሩ ውሣኔ ሊጽፍ ይችላል፡፡ ይህ ማለት ግን ጥሩ ሥነ ምግባር ያለው ዳኛ ሁልጊዜ ጥሩ ውሣኔ ይጽፋል ማለት አይደለም፡፡ ምክንያቱም ውሳኔውን የሚፅፈው ዳኛ ጥሩ ሥነ-ምግባር ያለው ሆኖ በውሳኔ አፃፃፍ በኩል በቂ ዕውቀት ከሌለው ጥሩ ውሳኔ ላይፅፍ ይችላል፡፡

ውሣኔ በሚፃፍበት ጊዜ በውሣኔው ሊስማማ የማይችል አካል ሊኖር ይችላል፡፡ በክርክሩ የተሸነፈ ጠበቃ፣ የጠበቃ ማኅበር፣ በክርክሩ የተሸፈነ ተከራካሪ ወገን፣ ሌላ ዳኛ፣ የበታች ወይም የበላይ ፍ/ቤት ወዘተ በተሰጠው ውሣኔ ላይ ላይስማሙ ይችላሉ፡፡ በተለይ ክርክሩን በሽንፈት ያጣ ተከራካሪ ወገን በውሣኔው እንዲስማማ ለማድረግ አግባብ ያለው የፍሬ ነገር ክርክር ሳይዛባ በታማኝነት ማስፈር የሚያስፈልግ ሲሆን፣ ቢቻል ከፍሬ ነገሮች ውስጥ ፍርድ ቤቱ ከተስማማባቸው ነጥቦች የተወሰኑትን መግለፁ ጥሩ ይሆናል፡፡ ይህም ፍ/ቤቱ ውሣኔ ሲሰጥ ለተከራከረሪ ወገኖች ክርክር እኩል ክብደት የሰጠ ታማኝ መሆኑን ለማሳየት ይጠቅማል፡፡ ለተክራካሪ ወገኖች ክርክር ታማኝ መሆን ማለት ግን ተከራካሪ ወገኖች ያቀረቡትን ክርክር ሙሉ በሙሉ በውሣኔው ላይ ገልብጦ ማስፈር ማለት አይደለም፡፡

በአጠቃላይ ውሣኔ በሚፃፍበት ጊዜ ከሙያው የሚጠበቀው ሥነ ምግባር፡-

- ገለልተኝነትን ማሳየት፣
- የህግ የበላይነትን መጠበቅ፣
- ውሣኔ የመስጠት ብቃትን ማዳበር፣
- የታዳሚ ክብርና ሙገሳ ሊቸረው የሚገባ መሆን፣

- የፍ/ቤትን ክብር የጠበቀ መሆን፣ እና
- የመሳሰሉትን የሥነ ምግባር መርሆዎች ያከበረ መሆኑን ማረጋገጥ ይገባል።

12. ጥሩ የውሳኔ አፃፃፍ ዘይቤ

ጥሩ የአፃፃፍ ዘይቤ የሚከተሉትን ነጥቦች ከሞላ ጎደል አካቶ ይይዛል።

- ውሣኔው በተቻለ መጠን አጭር እና ግልፅ /Precise, Concise/ መሆን አለበት። /የውሳኔው አጭር መሆን እንደ ጉዳዩ አይነት ይለያያል።/
- ዐረፍተ ነገሮች ቀላል መሆን ይገባቸዋል። ፓራግራፎችም በተቻለ መጠን ቢያጥሩ ይመረጣል። ይህንን ለመፈፀም በተቻለ መጠን እንደ **ወይም**፣ **እና**፣ **ማለትም** ... የመሳሰሉ አርዛሚ አያያዥ ቃላትን አለመጠቀም ይመረጣል፣
- የግድ እስካልሆነ ድረስ ከሥራ ቋንቋ ውጪ ያለን ሌላ ቋንቋ መጠቀም አያስፈልግም።
- የተገለባበጠ እና የተዘበራረቀ ውሳኔ መፃፍ የለበትም፣
- ውሳኔው ከፍሬ ነገር የወጣ መሆን የለበትም
- በውሳኔው የተከለከሉትንም ሆነ የተፈቀዱትን ጉዳዮች በአግባቡ ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት።
- ውሳኔውን የሚያነቡ አካላትን አጢኖ መፃፍ ይገባል።
  - ተከራካሪ ወገኖች
  - የአካባቢው ህብረተሰብ፣
  - የሌላ ክልል ህብረተሰብ ወይም
  - የሌላው ዓለም ማህበረሰብ
- የሚያግባቡ/Common/ ቃላትን ብቻ መጠቀም ያስፈልጋል።

  ምሳሌ :-

  - መስከር **ዕኩይነት** ነው ከማለት መስከር **አግባብ አይደለም** ማለት ይመረጣል።
- የቀልድ፣ የምፀት፣ የስድብ አባባሎችን ማስወገድ ተገቢ ነው።

<u>ምሳሌ</u> ፡-

- ❖ **ተደበደብኩ ባይ፣ የተከበሩ ከሣሽን፣ ተደፈርኩ ባይ የ12 ዓመት ወይዘሪት፣ ተበዳይ ነኝ ባይ ...** የሚሉት አግቦ እና ምፀት ያዘሉ አፃፃፎች በመሆናቸው ሊወገዱ ይገባል፡፡
- ❖ **ብረት ለበሱ የዐ/ሕግ ማስረጃ፣ ሾካካው የተከሳሽ/ከሳሽ ማስረጃ፣ ምጣድ ላይ እንዳረፈ ቅቤ ሙሽሽ የሚለው የተከሳሽ/ከሳሽ ማስረጃ፣ ተከሣሹ እንኳን ሊቀጣ በተገላቢጦሽ ሊሸለም ይገባው ነበር** የሚሉ አፃፃፎች ሊወገዱ ይገባል፡፡

- ➢ በሁሉም ተከራካሪ ወገን የተነሣ ጭብጥ በሙሉ ምላሽ ማግኘት ይገባዋል፡፡
- ➢ የሚያመላልሱ እና ተከራካሪ ወገንን በአግባቡ የማይጠሩ ቃላትን ማስወገድም ያስፈልጋል፡፡

<u>ለምሳሌ</u>፡-

- ❖ **«ከበደ የተባለው ተከራካሪ ወገን»**፣ /ከበደ ከሳሽ ይሁን ተከሳሽ መሆኑን ለማስታወስ አልፈነው ወደ መጣነው ንባብ እንድንመለስ የሚጋብዝ ነው፡፡/
- ❖ **«ከላይ ወይም ከፍ ሲል እንደተገለፀው»**፣
- ❖ **«ወደፊት እንደሚገለፀው»**፣ ወዘተ...

- ➢ በርካታ ጥቅስ መደርደርም ላያስፈልግ ይችላል፡፡ አስፈላጊ ከሆነ ጉዳዩን በአግባቡ የሚያስረዳ አንድ ይበቃል፡፡
- ➢ የምስክር ቃልንና የሰነድ ማስረጃን በተጠየቀው አግባብ እንደተሰጠው መልስ ከማስቀመጥ ለፍርድ አስፈላጊ የሆነውን ክፍል ብቻ በክለሳ መልክ ማስቀመጥ ይገባል፡፡
- ➢ የሰነድ ማስረጃ ሲጠቀስ ቀንና ቁጥር፣ አውጭው እና ሌሎች ገላጭ ነገሮች ሊካተቱበት ይገባል፡፡
- ➢ ክስና መልስን እንዳለ መገልበጥ አያስፈልግም፣
- ➢ እጅግ በጣም ረዥም ውሳኔ ካልሆነ በስተቀር በውሣኔው ውስጥ ፍሬ ነገር፣ ጭብጥ፣ ህግ፣ ድምዳሜ የሚሉ ርዕሶችን መጠቀም አያስፈልግም፡፡
- ➢ ተመሳሳይ ቃልን ለተመሳሳይ ተግባር መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

<u>ለምሳሌ</u> ፡-

- ❖ ከሳሹ መምህር ቢኒያም እውነቱ ቢሆን በፍርዱ ውስጥ አንዱ ከሳሹ፣ አንዱ መምህር፣ አንዱ ቢኒያም እውነቱ፣ አንዱ ደግሞ መምህር ቢኒያም እውነቱ

እያሉ በማፈራረቅ ሰውዬውን መጥቀስ ትክክል የዕሁፉን ውበት ከመቀነሱ በተጨማሪ አንባቢንም የሚያደናግር ነው።

- ለክርክሩ ሁሉ እኩል ክብደት መሰጠቱን ማሳየት ይገባል።
  - ከሳሽ ካልን ተከሳሽ፣
  - ክሱን በጥቅሉ ካስቀመጥን መልሱንም በጥቅሉ ማስቀመጥ
  - የከሳሹን ማስረጃ በአጭሩ ስናስቀምጥ የተከሳሽንም የመከላከያ ማስረጃ በአጭሩ ማስቀመጥ ይገባል።
- በጥናታዊ ፅሁፎች ላይ እንደምንመለከተው ዓይነት አንድን ቃል ወይም ሐረግ አጉልቶ ለማሳየት የምንጠቀምበትን ኢታሊክስ፣ ማስመር፣ ማጉላት፣ በትምህርት ጥቅስ ለይቶ ማስቀመጥ የመሳሰሉትን የአፃፃፍ ስልቶች ማስወገድ ይገባል። ምክንያቱም በውሳኔ ውስጥ ያለ ቃል ወይም ሀረግ ጐልቶ መታየት ያለበት በትንተና እና በምክንያት መሆን ይገባዋል።
- አላስፈላጊ ዝርዝር ነገርን ማሰወገድ ይገባል።

  <u>ለምሳሌ</u>፡-
  - አስፈላጊ ያልሆነ ፍሬ ነገር፣ ህግ፣ የግርጌ ማጣቀሻ፣ ዋቢ መጽሐፎች....መጥቀስ አያስፈልገውም ።
- ዳኛ በጉዳዩ ላይ ሊጠቀሱ የሚገባቸውን ጉዳዮች በሙሉ ከመረመረ በኋላ አግባብ ያለውን ብቻ በመምረጥ አንባቢን ማሳመን ይገባዋል፤ ምክንያቱም የውሳኔ አንባቢ ተግባር ሁሉንም ጉዳይ መመርመር መሆን የለበትም።
- አግላይ ቋንቋ መጠቀም አያስፈልግም። አስፈላጊ እስከ ሆነ ድረስ ለሁሉም ህፃናት፣ ለሁሉም ሴቶች ወይም ለሁሉም ሰዎች የሚጠቅም ቃል መጠቀም ያስፈልጋል።

  <u>ለምሳሌ</u> ፡-
  - አንድ ምክንያቲያዊ ወንድ ከማለት አንድ ምክንያታያዊ ሰው ማለት ይመረጣል።

- በቋንቋ አጠቃቀም ግልፅ ስህተትን ማስወገድ ይገባል። ይህ እንደየ ቋንቋው ባህሪም የሚወሰን ነው።

  <u>ለምሳሌ</u>፡-
  - በአማረኛ ለሚፃፍ ውሳኔ አንተ፣ እርስዎ የሚሉትንና ሌሎች የማዕረግ ስሞችን በአግባቡ መጠቀም ያስፈልጋል።
- ለሁሉም ተከራካሪ ወገኖች የሚገባውን ክብር የሚሰጥ ቃል መጠቀም ያስፈልጋል።

- በፍርዱ ውስጥ አስፈላጊ ሆኖ የአንድ ፀሀፊ ሥራ መጥቀስ የሚያስፈልግ በሆነ ጊዜ የፀሀፊው ሥምና ፅሁፍ፣ የታተመበት ቦታና ዘመን በሚገባ መጠቀስ አለበት፡፡ በደፈናው «አንድ የህግ ምሁር እንዳሉት» ወዘተ... የሚል አገላላፅ መወገድ አለበት፡፡
- አግባብነት ያለውን ህግ መጥቀስ ተገቢ ነው፡፡ ተከራካሪ ወገኖች በክርክራቸው ውስጥ የሚያነሷቸው ህጎች በየበኩላቸው ይጠቅሙናል የሚሏቸውን ስለሆነ ፍ/ቤቱ በዚያ ህግ እንዲወሰን የሚያደርገው አይደለም፡፡ ስለዚህ ፍ/ቤቱ ፍርዶችን በሚሰጥበት ጊዜ በተከራካሪ ወገኖች ተጠቀሰም አልተጠቀሰ ለጉዳዩ አግባብነት አለው የሚለውን ህግና የህግ ቁጥር በትክክል ሊጠቅስ ይገባል፤ ምክንያቱም ለተያዘው ጭብጥ ተገቢውን ህግ መፈለግ የፍ/ቤቱ ተግባር ነውና፡፡
- የተገራና ለስለስ ያለ ቋንቋ መጠቀም (Language to be sober and temperate) አስፈላጊ ነው፡፡
  - ፍርድ የሚፃፍበት ቋንቋ የሚያጋንን፣ ልቅና አንዱን ከፍ አንዱን ዝቅ የሚያደርግ መሆን የለበትም፡፡
  - በፍርዱ ውስጥ ያለው አገላለፅ ዳኛው መጀመሪያውኑ አ ቋም ይዟል የሚያሰኝ መሆን የለበትም፡፡
  - በፍርዱ ውስጥ ያለው አገላለፅ በሙሉ ዳኛው ገለልተኛ ሆኖ ጉዳዩን ከህጉ አነፃር ብቻ የተመለከተው መሆኑን ማሳየት አለበት፡፡
- ፍርዱ የመዝገቡ ምትክ መሆን የለበትም፡፡
- ቁጥርና ሐረግ ያላጣጣመ አገላለፅን ማስወገድም ያስፈልጋል፡፡

  <u>ለምሳሌ</u>፡-
  - ከሳሾች እንደገለፀው **(ስህተት)**.....ከሳሾች እንደገለፁት **(ትክክል)**
  - ከሳሽ ተከሣሽ ጣልቃ ገብ **(ስህተት)**.....ከሳሽ፣ ተከሳሽ እና ጣልቃ-ገብ **(ትክክል)**

    ፍ/ቤቱ ክሱን ላለመቀበል አይችልም **(ስህተት)**.....ፍ/ቤቱ ክሱን አልተቀበለውም **(ትክክል)**
  - ብር 5000 ይገባኛል በማለት ክስ በከሳሽ ቀርቧል **(ስህተት)**.....ከሳሽ ብር 5000 ይገባኛል በማለት ክስ መስርቷል **(ትክክል)**
- ፍ/ቤቱ ስለከሳሹ፣ ተከሳሹ ወይም ምስክሮች ወይም ተደረገ ስለተባለው ጉዳይ የሚሰጠው የመግለጫ ቃል በቀረበው ማስረጃ መሰረት የተረጋገጠውን መሆን አለበት፡፡

  <u>ለምሳሌ</u>፡-

❖ በቸልተኝነት ሰው ገደለ ተብሎ የተመሰከረበትን ተከሳሽ ነፍስ ገዳይ ብሎ መግለፅ ተገቢ አይደለም፡፡

<u>የጥሩ ፍርድና ውሳኔ አጻጻፍ ምሳሌ</u>

<u>ቀጥሎ የቀረበውን የክስ እና የመልስ ፍሬ-ነገር እንዲሁም በግራ ቀኝ ተከራካሪ ወገኖች የቀረበውን ማስረጃ በመመርመር አንድ ጥሩ ፍርድና ውሳኔ መያዝ ያለበትን ቅርጽና ይዘት ግምት ውስጥ በማስገባት ፍርድና ውሳኔ ጻፍ፡፡</u>

<u>የክስ ፍሬ ነገር</u>

- አቶ ከበደ ዓለማየሁ ታርጋ ቁጥሩ አ.ማ 00507 የሆነ ባጃጅ ተሽከርካሪ ባለቤት ናቸው፡፡
- ይህችን ባጃጅ የአብክመ የህግ ማስልጠኛ ማዕከል ለሰራተኞቹ ሰርቪስ እንድትሰጥ በቀን ብር 100.00 /አንድ መቶ ብር/ ተከራይቷታል፡፡
- መስከረም 30 ቀን 2003 ዓ.ም ባጃጇ ለሰራተኞች በውሉ መሰረት ሰርቪስ ለመስጠት ወደ ማስልጠኛ ማዕከሉ በመጓዝ ላይ ሳለች የጎን ቁጥሩ አማ 00037 የሆነ አይሱዙ መኪና ባጃጇን በመግጨት አደጋ አድርሶባታል፡፡
- በዚህ አደጋ ምክንያት ባጃጇ ያለሥራ ለአስር ቀናት ለጥገና በመቆየቷ፡-
  - ለጋራዥ ብር 3000.00 /ሶስት ሺህ ብር/
  - ለሰራተኛ ደመወዝ ብር 300.00 /ሶስት መቶ ብር/ - ለአስር ቀናት በቀን ብር 30.00 /ሰላሳ ብር/ ሂሳብ
  - ባጃጁ ቢሰራ ኖሮ በቀን ያገኝ የነበረው ብር 100.00 /አንድ መቶ ብር/ በአስር ቀናት ተባዝቶ ይገኝ የነበረውን ብር 1000.00 /አንድ ሺህ ብር/
    - ⇒ በድምሩ ብር 4300.00 /አራት ሺህ ሶስት መቶ ብር/ የጉዳት ካሳ

<u>ከሳሹ በማስረጃነት</u>

- የባጃጁን ሊብሬ
- ከሥልጠና ማዕከሉ ጋር ስምምነት ያደረጉበትን የውል ሰነድ
- አደጋው የደረሰ በአቶ ተሾመ ይሁኔ አይሱዙ መኪና ምክንያት መሆኑን የሚያስረዳ የቴክኒክ ማስረጃ
- አደጋው ሲፈፀም የተመለከቱ የሶስት ምስክሮችን ስም ዝርዝር
- ገንዘብ የተከፈለባቸው ልዩ ልዩ ደረሰኞች አቅርቧል፡፡

<u>የተከሳሽ መልስ</u>

- አደጋው በእርሱ መኪና አማካኝነት መድረሱን አምኗል፤ ሆኖም በመከራከሪያነት፡-

- ለማስጠገኛ ወጣ የተባለው ወጭ የተጋነነ ነው፤
- በከሳሽ የቀረበው የውል ሰነድ ህጋዊነትን የጠበቀ አይደለም፤
- አደጋው ከመድረሱ አንድ ሳምንት በፊት መኪናዬ ባልታወቀ ሰው ተሰርቆ ስለነበር ለደረሰው ጉዳት ጥፋትና ኃላፊነት የለብኝም የሚሉ ነጥቦችን አንስቷል፡፡

<u>ተከሳሹ በማስረጃነትም</u>

- ተከሳሹ መኪናው ካቆመበት ቦታ የጠፋ መሆኑን ለ4ኛ ፖ/ሊስ ጽ/ቤት ያመለከተ መሆኑን የሚገልፅ ደብዳቤ
- የመኪናውን ሊብሬ አያይዞ አቅርቧል፡፡

ገጽ 06

የፍ/ብ/መ/ቁ 13254

ቀን 13/03/2003 ዓ.ም

የባህር ዳር ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት

ዳኛ... አቶ ዘነበ ተረፈ

ከሳሽ ..... አቶ ከበደ ዓለማየሁ

ተከሳሽ ... አቶ ተሾመ ይሁኔ

መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረው መርምሮ ተገቢውን ፍርድና ውሳኔ ለመስጠት ስለሆነ መዝገቡን መርምሬ የሚከተለውን ፍርድና ውሳኔ ሰጥቻለሁ::

<u>ፍ ር ድ</u>

ከሳሽ ህዳር 12 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ የታርጋ ቁጥሩ አ.ማ 00037 የሆነ የተከሳሹ የጭነት አይሱዙ መኪና መስከረም 30 ቀን 2003 ዓ.ም ከቀኑ በ6:00 ሰዓት ላይ ታርጋ ቁጥሯ አ.ማ. 00507 የሆነች ባጃጅ ተሽከርካሪዬ ለአብክመ የህግ ማሰልጠኛ ማዕከል ሰራተኞች ሰርቪስ ለመስጠት ወደ ማሰልጠኛ ማዕከሉ በመጓዝ ላይ ሳለች

ከአብክመ ገጠር መንገዶች ባለስልጣን መ/ቤት ፊት ለፊት ካለው አደባባይ ላይ ባጃጇን ቀድሞ ለማለፍ ሲሞክር በመግጨት ጉዳት አድርሶባታል። ባጃጇ በደረሰባት አደጋ ምክንያት ለጥገና ለአስር ቀናት የቆመች ሲሆን ለማስጠገኛ ወጭ ያደረሱት ብር 3000.00 (ሶስት ሺህ ብር)፣ በቀን ብር 30.00 (ሰላሳ ብር) ሂሳብ ለአስር ቀናት ለባጃጇ ሾፌር ደመወዝ የከፈልኩት ብር 300.00 (ሶስት መቶ ብር)፣ ከአብክመ የህግ ማስልጠኛ ማዕከል ጋር የሰርቪስ አገልግሎት ለመስጠት በነበረኝ ውል መሰረት በቀን አገኘው የነበረ ብር 100.00 (አንድ መቶ ብር) በአስር ቀናት ተባዝቶ ባጃጇ ባለመስርታ ምክንያት የቀረብኝ ብር 1000.00 (አንድ ሺህ) እና ለአቤቱታ ማስፃፊያ ያወጣሁት ብር 300.00 (ሶስት መቶ ብር) በድምሩ ብር 4600.00 (አራት ሺህ ስድስት መቶ ብር) ከህጋዊ ወለድ ጋር ታስቦ ይከፈለኝ በማለት ሲያመለክት ይህንንም ያስረዱልኛል ያላቸውን የሶስት ምስክሮች ስም ዝርዝር፣ የባጃጁን ሊብሬ፣ ከሥልጠና ማዕከሉ ጋር ስምምነት ያደረጉበትን የውል ሰነድ፣ አደጋው የደረሰ በአቶ ተሾመ ይሁኔ አይሱዙ መኪና ምክንያት መሆኑን የሚያስረዳ የቴክኒክ ማስረጃ እና ገንዘብ የተከፈለባቸው ልዩ ልዩ ደረሰኞችን ከአቤቱታ ጽሁፉ ጋር አያይዞ አቅርቧል።

ፍ/ቤቱም የከሳሽን የክስ አቤቱታ ከፍ/ቤቱ መጥሪያ ጋር አያይዞ ለተከሳሹ ሲልክ መልሱን ለጥቅምት 27 ቀን 2003 ዓ.ም ከጧቱ 3:00 ሰዓት ይዞ እንዲቀርብ ባዘዘው መሰረት ተከሳሹ በተባለው ቀን ለቀረበበት ክስ መልሱን ይዞ ቀርቧል። በመልሱም ላይ አደጋው የደረሰ መሆኑን በማመን ለማስጠገኛ ወጣ የተባለው ወጭ የተጋነነ መሆኑንና በከሳሽ የቀረበው የውል ሰነድ ህጋዊነትን የጠበቀ አለመሆኑን በመቃወም አደጋው ከመድረሱ አንድ ሳምንት በፊት መኪናው ባልታወቀ ሰው ተሰርቃ ስለነበር ለደረሰው ጉዳት ጥፋትና ኃላፊነት የሌለበት መሆኑን በመግለፅ የተከራከረ ሲሆን ይህንንም ለማስረዳት መኪናው ካቆመበት ቦታ የጠፋ መሆኑን ለባህር ዳር ከተማ 4ኛ ፖሊስ ጽ/ቤት ያመለከተ መሆኑን የሚገልፅ ደብዳቤና የመኪናውን የባለቤትነት ደብተር አያይዞ አቅርቧል።

ክሱ በሚሰማበት ቀን ተከራካሪዎች የቃል ክርክር ሲያደርጉ ተከሳሹ በመቃወሚያነት ባቀረባቸው ነጥቦች ላይ ከሳሽ መልስ ሰጥቷል። መልሱንም ሲሰጥ ለጥገና የወጣው ወጭ ተጋኗል መባሉ ሀሰት ነው፤ እንዴውም ባጃጇን ወደ ጋራዥ ከማስገባቴ በፊት በተሸለ ዋጋ ሊጠግን የሚችል ጋራዥ የትኛው እንደሆነ አስቀድሜ ጥናት በማድረግ በዋጋ ደረጃ በርካሽ የጥገና አገልግሎት ለሚሰጠው ጋራዥ አቅርቤ ተከራክሬና ተደራድሬ ነው ያስጠገንኩት፤ ስለዚህ ዋጋው የተጋነነ ነው ሊባል አይገባም። የሰነዱን ህጋዊነት በተመለከተ ሰነዱ ማንኛውም በህግ ፊት ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችል የውል ሰነድ ሊይዛቸው የሚገቡ ጉዳዮችን የያዘ ስለሆነ ህጋዊነቱን የጠበቀ ነው ሲል ተከራክሯል።

ፍ/ቤቱም ወደ ዋናው ፍሬ ነገር ከመግባቱ በፊት ለማስጠገን ወጣ የተባለው ወጭ የተጋነነ ነው እና በከሳሽ የቀረበው የውል ሰነድ ህጋዊነትን የጠበቀ አይደለም በሚሉት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ላይ ብይን ሰጥቷል፤ በዚህም መሰረት ወጭው የተጋነነ መሆንና አለመሆኑን እንዲያጣሩ ባለሙያዎች በፍ/ቤቱ ታዝዘው ባጣሩት መሰረት ለማስጠገኛ የወጣው ወጭ ያልተጋነነ መሆኑን በማረጋገጣቸው ፍ/ቤቱ ለማስጠገኛ ወጣ የተባለው ወጭ ያልተጋነነ መሆኑን በይኗል። በተጨማሪም ከአብክመ የህግ ባለሙያዎች ማስልጠኛ ማዕከል ጋር ውል የተደረገ መሆኑን የሚገልፀው የውል ሰነድ ህጋዊነትን የጠበቀ ነዎይ ብዬ ስመረምረው ውሉ ችሎታ ባላቸው ሰዎች መካከል የተደረገ መሆኑን፤ እርግጠኛ፣ የሚቻልና ህጋዊ መሆኑን፤ ውሉ በጽሁፍ ሆኖ በተዋዋይ ወገኖች የተፈረመበትና በአራት ምስክሮች ፊት የተረጋገጠ መሆኑን ከቀረበው

የውል ሰነድ በማረጋገጫ የውሉ ሰነድ ህጋዊነትን የጠበቀ ነው በማለት ብይን ሰጥቼ አልፈያለሁ::

በመቃወሚያነት በቀረቡት ጉዳዮች ላይ ብይን ከሰጠሁ በኋላ በዋናው ፍሬ ነገር ላይ ውሳኔ ለመስጠት ያመቼኝ ዘንድ "መኪናው አደጋው ከመድረሱ አንድ ሳምንት በፊት ተሰርቆ ነበር?" "መኪናው ተሰርቆ ነበር የሚለው መከራከሪያስ ተከሳሹን ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ አያደርገውም?" የሚሉትን ጭብጦች መስርቻለሁ::

ምንም እንኳ ከሳሽ አደጋው መድረሱን ያውቁልኛል በማለት ሶስት የዓይን ምስክሮችን ዝርዝር ከአቤቱታ ጽሁፋቸው ጋር አያይዘው ያቀረቡ ቢሆንም ተከሳሹ የአደጋውን መድረስ ያልካደና የደረሰው አደጋ በተከሳሹ አይሱዙ የጭነት መኪና መሆኑን የሚያስረዳ የቴክኒክ ማስረጃ ተያይዞ የቀረበ ስለሆነ በዚህ ጉዳይ ላይ የዓይን ምስክሮችን መስማት የፍ/ቤቱን ሥራ ከማብዛትና ጊዜና ጉልበት ከማባከን ውጭ ለተያዘው ጉዳይ የሚሰጠው ፋይዳ የጎላ ስላልሆነ ፍ/ቤቱ የቀረቡትን የዓይን ምስክሮች ሳይሰማ በማለፍ የቀረቡትን የሰነድ ማስረጃዎች ከተያዙት ጭብጦች ጋር በማዛመድና ከተገቢው የህግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ መርምሯል::

በዚህም መሰረት በመጀመሪያ መኪናው አደጋው ከመድረሱ አንድ ሳምንት በፊት ተሰርቆ ነበር? የሚለውን ጉዳይ ለማጣራት ከባህር ዳር ከተማ 4ኛ ፖሊስ ጽ/ቤት የመጣውን የጽሁፍ ማስረጃ መርምሬያለሁ:: ይህ ከፖሊስ የመጣው ማስረጃ የሚስረዳው ተከሳሹ መኪናውን ካቆመበት ቦታ የጠፋው መሆኑን ለፖሊስ ስለማስታወቁ የሚገልፅ ደብዳቤ እንጅ መኪናው ስለመጥፋቱ የሚያስረዳ ማስረጃ አይደለም:: ማመልከቻው ለመኪናው መጥፋት በራሱ በቂ ማስረጃ ነው ቢባል እንኳ ተከሳሹ የመኪናውን መጥፋት ለፖሊስ ያመለከተ አደጋው ከመድረሱ ከአንድ ሳምንት በፊት ነው:: ይህ ማለት ደግሞ አደጋው በደረሰበት ሰዓት መኪናይቱ ተመልሳ በተከሳሽ እጅ ላለመግባቷ እንደዋስትና የሚሆን አይደለም::

በመቀጠልም መኪናው ተሰርቆ ነበር የሚለው መከራከሪያ ተከሳሹን ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ አያደርግም ወይ? የሚለውን ጭብጥ ስመረምር የፍ/ብ/ህ/ቁ 2081(2) እንደሚደነግገው አደጋው በደረሰ ጊዜ መኪናው የተሰረቀበት ለመሆኑ ማስረዳት የቻለ እንደሆነ ባለሀብቱ ኃላፊነት የለበትም ይላል:: ሆኖም ግን ተከሳሹ መኪና ተሰርቆብኛል ብሎ ቢከራከርም እንኳ ከባህር ዳር ከተማ 4ኛ ፖሊስ ጽ/ቤት ያቀረበው ማስረጃ መኪናው የተሰረቀ እንደሆነ የሚያስረዳ ሳይሆን መኪናዬ ጠፍቶብኛል ብሎ ለፖሊስ ያመለከተ መሆኑን የሚገልፅ ደብዳቤ ነው፤ ይህ ማለት ደግሞ ተከሳሹ መኪናው የተሰረቀ ስለመሆኑ በበቂ ሁኔታ አላስረዳም ማለት ነው:: ስለዚህ በፍ/ብ/ህ/ቁ 2081(1) መሰረት አደጋው የደረሰ መኪናውን ለመንዳት ባልተፈቀደለት ሰው ቢሆን እንኳ የመኪናው ባለቤት በመኪናው አማካኝነት ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ እንደሆነ ይደነግጋል:: በዚህ መሰረት ተከሳሹ የመኪናው ባለቤት በመሆኑ ብቻ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ ነው ብያለሁ::

<u>ው ሳ ኔ</u>

በዚህም መሰረት ተከሳሹ ለከሳሹ:-

1. *ባጃጇን ለማስጠገን ለጋራዥ ያወጣውን ብር 3000.00 /ሶስት ሺህ ብር/*
2. *ለአስር ቀናት ለሾፌር ደመወዝ የከፈለውን ብር 300.00 /ሶስት መቶ ብር/*

3. ባጃጂ ለአስር ቀናት ለጥገና ያለሥራ በመቆሙ ምክንያት ከሳሹ ያጣውን ብር 1000.00 /አንድ ሺህ ብር/
   ⇒ በድምሩ ብር 4300.00 /አራት ሺህ ሶስት መቶ ብር/ እንዲከፍል ወስኛለሁ::
4. ለአቤቱታ ማስጻፊያ ተከፈለ ለተባለው ብር 300.00 /ሶስት መቶ ብር/ ከሳሽ ማስረጃ ስላላቀረበ ለከፈል አይገባም ብያለሁ::
5. የባንክ ወለድ ጥያቄን በተመለከተ በካሳ ጥያቄ ላይ ወለድ ታስቦ እንዲከፈል ማድረግ ከወጭና ኪሳራ አከፋፈል ዓላማ ዓይን ሲታይ ተገቢ መስሎ ስላልታየኝ ሊከፈል አይገባም ብዬ ወስኛለሁ::

ት ዕ ዛ ዝ

- የጊዜ ገደቡን ጠብቆ ይግባኝ ለጠየቀ ወገን ይግብኙ ተገልብጦ ይሰጥ::
- መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ::

ዘነበ ተረፈ

ዳኛ

ዋቢ ጽሁፎች

I. መጽሀፍት

1. አበበ መላት እና ሳሙኤል ተሻለ፣ ***የፍርድ አሰጣጥና አዳዳፍ በኢትዮጵያ***፣ (ያልታተመ)
2. ውብሸት ሽፈራው፣ ***የውሳኔ አዳዳፍ እና ህገ-መንግስቱ***፣ (ያልታተመ)፣ ጥቅምት 2001 ዓ.ም
3. ፊሊጶስ ዓይናለም፣ ***የውሳኔ /ፍርድ/ አሰጣጥና አዳዳፍ ዘዴ በኢትዮጵያ፣ የአብክመ ጠቅላይ ፍ/ቤት ዝክረ-ህግ መጽሔት***፣ ቁጥር 1፣ 1999

II. ህጎች

1. የኢፌዴሪ ህገ-መንግስት፣ 1987 ዓ.ም፣ አዋጅ ቁጥር 1፣ ***ነጋሪት ጋዜጣ***፣ 1ኛ ዓመት፣ ቁጥር 1
2. የኢትዮጵያ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ፣ 1958 ዓ.ም፣ ***ነጋሪት ጋዜጣ በተለይ የወጣ***፣ 25ኛ ዓመት፣ ቁጥር 3
3. የኢትዮጵያ የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ፣ 1954 ዓ.ም፣ ***ነጋሪት ጋዜጣ በተለይ የወጣ***፣ ቁጥር 1
4. የኢፌዴሪ የወንጀል ህግ፣1996፣ አዋጅ ቁጥር 414

III. **ሌሎች**

1. ልዩ ልዩ የፍ/ቤት ውሳኔዎች
2. ስለውሳኔ አጻጻፍ በተሰጠ ትምህርት ላይ የተያዙ የክፍል ውስጥ የደብተር ሌክቸሮች

የጥሩ ፍርድ አፃፃፍ ማነፃፀሪያ ዝርዝር (Checklist)

1. 14 ውሳኔዎች ከፍርድ ቤቱ ሙሉ መዝገቦች ጋር ለልምምድ የቀረቡ ሲሆን እነዚህን ውሳኔዎች በሚከተለው የማነፃፀሪያ ዝርዝር መሰረት ይተቹ።

የጉዳዩን ፍሬ ነገር በተመለከተ፣

- **አግባብነት ያለው ፍሬ ነገር**
- **ግራ ቀኙን የሚያከራክረው ጭብጥ፣**
- **ሕጉ**
- **የውሳኔ ምክንያት**
- **መደምደሚያ**
- **ትእዛዞች**

ከግልጽነት አንጻር፣

- **ለተራው ሰው የሚገቡ የቃላት አጠቃቀም**
- **አጫጭር አረፍተነገሮች**

አቀራረቡ፣

- **እጥር ምጥን ያለ**
- **በፓራግራፍ የተከፋፈለ**
- **አጫጭር ፓራግራፎች**
- **አንድን ሀሳብ ብቻ የሚያንጸባርቁ ፓራግራፎች፣**
- **አርእስት የተሰጣቸው ክፍሎች**
- **ውበት ያለው የቋንቋ አጠቃቀም**
- **ቅኔ፣ አግቦ የተለምዶ አባባሎችን ያላዘሉ**
- **የተመዛዘነ**

- ስሜታዊ ያልሆነ
- በማስረጃ ብቻ የተደገፈ፣

14ቱን ውሳኔዎች ትችቱን መሰረት በማድረግ በድጋሚ ይፃፉቸው።።